# የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ

## ባጭር ቃል የወጣ



አለቃ ታየ ገብረ ማርያም

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ

## ባጭር ቃል የወጣ

አለቃ ታየ ገ/ማርያም

አዲስ አበባ።

# ማውጫ

መግቢያ ........ 5

መቅድም........ 11

ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ዘር ከምን ትውልድ እንደ ሆነ ልዩ ልዩ ዓይነት ሕዝቦችም በውስጥዋ እንዳለበት የሚያሳይ ........ 12

፩ ነገደ አሪት ........ 13

፪ ነገደ ካም........ 13

፫ ነገደ ቅማንቶች........ 15

፬ ነገደ ወይጦ........ 16

፭ ነገደ ሽናሽ ........ 17

፮ ነገደ ዮቅጣን ........ 19

፯ የትግሬ ሕዝብ ታሪክ ........ 21

፰ የአማራ ሕዝብ ታሪክ ........ 22

፱ የነገደ እሥራኤል መምጣት ........ 26

፲ ነገደ አገው........ 30

፲፩ ነገደ አስማከህ ........ 31

፲፪ ነገደ ፈላሻ........ 32

፲፫ ነገደ ጋፋት ........ 34

፲፬ ነገደ አሮሞ ........ 36

፲፭ የቦረን ልጆች........ 38

፲፮ ነገደ እናሪያ........ 39

፲፯ ነገደ እስላም ........ 42

፲፰ ነገደ ወረሲህ ........ 44

፲፱ ነገደ ጉራጌ ........ 48

፳ ከምጥዋ እስከ መተማ በኢትዮጵያ ዳር ለዳር በቆላው ስለ አሉ ሕዝብ ........ 48

፳፩ ከሐረርጌ እስከ ምጥዋ ወሰን ስላሉ ሕዝብ ........ 49

፳፪ የሐረርጌ ሕዝብ ........ 49

፳፫ የኢትዮጵያ ወሰንና ደግ አገር እንደ ነበረች። ........ 51

አባሪ ፩ ........ 52

ከልደት በኋላ በኢትዮጵያ የነገሡ ነገሥታት ዘመነ መንግሥት ........ 52

አባሪ ፪ ........ 54

ዘመነ ክርስትና በኢትዮጵያ ........ 54

አባሪ ፫ ........ 58

አባሪ ፬ ........ 58

አባሪ ፭ ........ 59

አባሪ ፮ ........ 62

አባሪ ፯ ........ 63

የስሞች መጠቁም ........ 64

## ምስጋና

ይህ መጽሐፍ ለኅትመት ለማዘጋጀት በተነሳሁበት ጊዜ ትብብራችሁ ያልተለየኝን ወዳጆቼን ሞገስ ሞላ፣ ዶር. ጌታኹን ሽብሩ እና እንዲሁም የመካነ ኢየሱስ ቤተ መጻሕፍትን ከልብ አመሰግናለሁ።

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

*መግቢያ*

«የመምህር አፍ ከመጽሐፍ ይበልጣል።»

አለቃ ታየ ገብረ ማርያም።

የዚህች አነስተኛ መጽሐፍ ደራሲ ስለሆኑት አለቃ ታየ ገብረ ማርያም ብዙ ሰዎች ጽፈዋል። ከብዙዎቹም በጥቂቱ ኃይሉ ከበደ በሕይወት ታሪካቸው ላይ ለቢ.ኤ የመመረቂያ ጽሑፍም ጉስታቭ አረን የተባሉ የስዊድን ሚስዮናዊ ፕሮቴስታንስ በኢትዮጵያ ስለ አስተዋወቁ የወንጌል መልእክተኞች በአዘጋጁት መጽሐፋቸው፣ ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት ለዚሁ መጽሐፍ ሃምሳኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ መግቢያው ላይ ያቀረቡት፣ እና ዓለሜ እሸቴ በጣልያኑ የኢትዮጵያ ምርምር መጽሔት Rassegna di Studi Etipici ላይ የጻፉት ጎልተው ይጠቀሳሉ።

አለቃ ታየ ገብረ ማርያም ጎንደር ክፍለ ሃገር ልዩ ስሙ ከመከም ወይም ቃሮዳ በተባለ ቦታ ይፋግ ውስጥ በመጋቢት 21 ቀን 1853 ዓመተ ምሕረት በዘመነ ሉቃስ በአጤ ቴዎድሮስ ጊዜ ተወለዱ። አባታቸው ወደ ሸዋ ጠቅላይ ግዛት ሄደው በቀሩበትና ምንም ስለ እርሳቸው ሳይሰማ በቀረበት ጊዜ እናታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። ስለዚህም ነበር አጎታቸው ወደ እሚኖሩበት ምፅዋ ያመሩት። ነገር ግን እዛ ሲደርሱ አጎታቸው ወደ ቦምቤይ ሕንድ ተጓዙ ተረዱ። ወደቡ ላይ ስለ ስዊድን ወንጌላውያን ሚስዮን የወንዶች ትምህርት ቤት ሰሙ። በዚህም ሁኔታ ሉንደሃል በተባለ ግለሰብ፣ ምፅዋ አጠገብ ምንኩሉ የሚባል ቦታ ልይ ሲንቀሳቀስ ከነበረው የስዊድን ሚስዮን ጋር ለመጀመርያ ጊዜ በ1880 እ.አ.አ ተገናኙ። በሚቀጥለው ዓመት ቤቴል ብለው ስዊድኖቹ ከሚጠሩት ማኅበር አባል ሆኑ። ከዓመት በኋላ በጣም ዝነኛ ከሆኑት የሃገራቸው ገዳማት ቅኔ እና የስነ ጽሑፍ ቅርሶችን ለማጥናት ወደ ትውልድ ቦታቸው ቤጌምድር ተመለሱ። ከዚህም በተጨማሪ ስለ ወንጌል የገባቸውን ለሃገራቸው ሰዎች ለማካፈል ጓግተው ነበር። የወንጌል ስብከቱ ሥራ ግን አልተሳካላቸውም። ወጣት መሆናቸው በቁም ነገር እንዳይወሰዱ አደረጋቸው። ተስፋ ቆርጠውም ቅኔ ወደ መማርና፣ ጥንታዊ መጻሕፍት ያሉባቸውን ታዋቂ ቦታዎችን በመጎብኘት በሃይማኖትና ባሕል ላይ፣ የሃይማኖት ቀኖና ሥራዎችን እና የቤተ ክርስቲያን ታሪክን በጥንቃቄና በጥልቀት ማጥናት ብቻ ዞሩ።

በታኅሣሥ 1878 ዓመተ ምሕረት ወደ እምኩሉ ተመልሰው በመምህርነት፣ በተርጓሚነት እና ሰባኪነት ተቀጠሩ። «ይህ የአማራ የሃያ ሁለት ዓመት ወጣት፣ ለአሥራ አምስት ዓመታት አገልግሎ በፈንጣጣ ሕይወቱ ያለፈችውን አባ ሉንደሃልን ላጣው

የቤቴል ማኅበር ዋና ዋጋ ያለው ንብረት ሆነ።» ይለናል ጉስታቭ አረን። ሉንደሃል በቅዱስ ዮሐንስ ወንጌል ላይ ማብራርያ ይሠራ ነበር። አለቃ ታየ፤ የሚቹን ባለቤት ወ/ሮ ኤሚሊ ሉንደሃልን ረቂቁን በማጠናቀቅ አግዘው፣ ከኦነሲሞስ ነሲብ እና ከእርሷ ጋር በመሆን ደግሞ አግዘው ለኅትመት አብቅተዋል። ከእዛ በጉዟቸው ወቅት ካመጧቸው ጥቂት ጥንታዊ የግዕዝ የብራና መጽሐፍት አንዱ የሆነውን መጽሐፈ ሰዋሰውን፤ በአማርኛ መፍቻ አድርገው አዘጋጅተው፤ የመጀመርያ ሥራቸውን በ2.000 ቅጂዎች ምንኩሉ በሚገኘው ማተሚያ በ1897 እ.አ.አ ለኅትመት አብቅተዋል። ይህም ሥራ ሚዛን ደፍቶ በስፋት ተቀባይነት በማግኘቱ የአለቅነት ማዕረግ አሰጥቷቸዋል።

በተከታዩ ዓመት ተቃውሞ ያስነሳባቸውን የወንጌል ስብከት ለመጀመር ወደ ትውልድ ሃገራቸው ቃሮዳ ሄዱ። በሃይማኖት ከአመለካከታቸው ምክንያትም ተከስሰው በወቅቱ የቤጌምድር ገዢ ከነበሩት ራስ መንገሻ አቲከም ፊት ቀረቡ። ከሳሾቻቸውንም በክርክር ረቱ። ከዚህም ሌላ ተርጉመው ያዘጋጁትን መጽሐፈ ሰዋሰው ተመልክተው ይሁን ከአለቃ ታየ የተረገሙትን ራስ መንገሻ ወደ ዳግማዊ አጤ ምኒልክ ላኳቸው። ታየ ከዳግማአዊ ምኒልክ ጋር ሲገናኙ መጽሐፋቸውን አቀረቡ። ምንም እንኳን ንጉሡ ነገሥቱ ለብዙ ጊዜ አጠገባቸው ባያቆዩአቸውም፤ ሃይማኖቱን መርምረን ምንም ጥፋት አላገኘንበትም ብለው፤ ማንም እንዳያስቸግራቸው የሚገልጽ ደብዳቤ ሰጥተው ወደ በጌምድር አሰናበቷቸው።

የጀርመን መንግሥት በ1897 ዓ/ም በምሥራቅ የጥናት ክፍል አማርኛ እና ግዕዝ የሚያስተምርላቸው ሰው አጤ ምኒልክን በጠየቋቸው ጊዜ፤ አለቃ ታየን መርጠው፤ ከጀርመን መንግሥት ተልከው የመጡት ሰዎች በጎጃም አድርገው ወደ ምፅዋ እየሄዱ ነበረና ከእነሱ ጋር አብረው እንዲሄዱ በደብዳቤ አዘዟቸው። በሰላ ላይ ከነበሩት ወንጌላውያን ጓደኞቻቸው ጋር በሚስዝ ኤልሲ ቪንኪፊት አማካኝነት መሠረታዊ የጀርመንኛ ቋንቋ ትምህርት ከተሰጣቸው በኋላ በግንቦት 15 1897 ዓ/ም ጉዞ ጀምረው በ18 የስዊዝ መተላለፊያ፣ በ22 ኔፐልስ ጣልያን፣ በ25 ማርሴይ የፈረንሣይ የወደብ ከተማ፣ በ29 ሊዝቦን ፖርቱጋል፣ በሰኔ 2 ሆላንድ፣ በ6 የጀርመኗ የወደቧ ከተማ ሃምቡርግ ደርሰው፤ በሚቀጥለው ቀን በርሊን ገቡ።

እዛም በአዩባቸውም የከተማው ሕንጻዎች፣ ሐውልቶች እና ሰው ሠራሽ ፏፏቴዎች በጣሙን ተገረሙ። ሙዝየሞችንና የስዕል ዓውደ ርዕዮችን ጎብኝተዋል። በተከታዮቹ ቀናት የከተማውን ጉብኝታቸውን ቀጥለው የበርሊን ዩኒቨርሲቲን ከኢትዮጵያ የተወሰዱ በቀላሉ የማይገኙ የግዕዝ መጻሕፍትን ተመለከቱ። በመስከረም ወር ወደ ቴአትር ቤት

ሄደው በአዩት ትዕይንት እንዴት እንደተደመሙ በዕለት ማስታወሻ ደብተራቸው ላይ በሰፊው ገልጸውታል።

ከሁለት ዓመታት ቆይታ በኋላ በ1901 ዓ/ም ወደ ሃገራቸው ሲመለሱ ወደ ጀርመን ከተወሰዱት የኢትዮጵያ ጥንታዊ የብራና መጻሕፍት ውስጥ 130 ያህሉን ለአጤ ምኒልክ እንደ አመጡላቸው ታውቋል። እንደ ተመለሱም ለአገልግሎታቸው ኒሻን ሲሸለሙ፤ ይፋግን እንዲያስተዳድሩ ተሾሙ። የአጤ ምኒልክንም የሕይወት ታሪክ እንዲጽፉ ታዝተው ነበር። በጊዜው የቤጌምድር ገዢ የነበሩት ራስ ወልደ ጊዮርጊስ አቦዬ ፊት በፀረ ማርያምነት ተከስሰው በመቅረባቸው ግዛታቸውን ተነጠቁ። ቀድሞም ከንጉሠ ነገሥቱ እንዳይነኩ የሚል ደብዳቤ ይዘው ሲመለከቱ፣ በትትክል ሳይመረምሯቸው ነው የላኳቸው ብለው ተቃዋሚዎቻቸው አመልክተው ነበር። አሁን ግን በፊት ራስ መንገሻ አቲከም ጋር ከሳሾቻቸውን በክርክር እንደረቱት ሳይሆን፤ ወዳጃቸው የነበሩት መሸሻ ወርቁ የተባሉ ግለሰብ በችሎት ፊት የማርያምን ምስል አውጥተው ተሳለም ሲሏቸው፤ መጽሐፍ ቅዱስን ጠቅሰው ምስል አታምልክ በሚለው ክርስትያኖች ተከልክለዋል በማለት እምቢ አሉ። በችሎት የተገኘው የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ሁሉ አጉረመረመ። አንዳንዶች ጎራዴያቸውንና ሽጉጣቸውን መዘዙባቸው። አዲስ አበባ ወደ አቡነ ማቴዎስ ተልከው ለአንድ ዓመት ያህል ለመታሰርም በቁ። አጤ ምኒልክ ታምመው ስልጣኑ በብልኋ እቴጌ ጣይቱ እጅ ስለ ነበረም ደጋፊ አላገኙም። ከጣይቱ በኋላ ብዙ ተቃውሞ አልገጠማቸውም። በልጅ ኢያሱ ጊዜ እንዲያውም እንደተሸለሙ ይታወቃል። ራስ ተፈሪ የሌሎቹን እምነት እና አመለካከት ሳያዩ በመንግሥቱ ሥራ እንዲያገለግሏቸው የበረታቱ ስለ ነበረ፤ አለቃ ታየ የአልጋ ወራሹ የፖለቲካ አማካሪነት ሥራ ተሰጥቷቸው ነበር። ከጥር 1901 እስከ ነሐሴ 1916 ዕለተ ሞታቸው ድረስም አገልግለዋል።

አለቃ ታየ ፀሐይቱ ከተባለች ጋር ትዳር መሥርተው ነበር። ከባለቤታቸው ሞት በኋላ የጆን ፓርኪንስን ልጅ ወ/ሮ ጥሩነሽን አግብተዋል። ከሁለተኛው ጋብቻቸው ስድስት ወራት በኋላም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። ከሁለቱም ጋብቻቸው ምንም ልጅ አልወለዱም።

ቤተሰቦቻቸውም በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ለመቅበር ሲሞክሩ ተከልክለዋል። ከንግሥት ዘውዲቱም አስፈቅደው ቢመጡም ሳይሆን በመቅረቱ፤ በአጤ ምኒልክ ለውጭ ሃገር ዜጎች መቀበርያ ከከተማ ውጭ ጴጥሮስ ወ ፓውሎስ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ባለው የካቶሊኮች መካነ መቃብር ሥርዓተ ቀብራቸው ተፈጽሟል።

በቀብራቸውም ላይ የአዲስ አበባ ከንቲባ ፊታውራሪ ነሲቡ ዛማኔል እና ሌሎች ታላላቅ ሰዎች ተገኝተዋል። ከስዊድናዊው ወንጌላዊ ካርል ሰደርኪቪስት ጎንም ተቀብረዋል። የእንጀራ ልጃቸው የወ/ሮ ጥሩነሽ ፓርኪንስ ልጅ ወ/ሮ ደስታ ሽምጥር ሥርዓተ ቀብሩን አስፈጽመዋል።

አለቃ ታየ ብዙ ሥራዎችን ያፈለቁ ደራሲ ነበሩ። ከደረሷቸው መጻሕፍት ግን ጥቂቶቹ ብቻ ናቸው ለኅትመት የበቁላቸው። ዳግማዊ አጤ ምኒልክ የኢትዮጵያ ታሪክ ከሥር ጀምረው እስከ እርሳቸው ጊዜ ያለውን እንዲጽፉ አዝዘዋቸው ነበር። እርሳቸውም የኢትዮጵያ መንግሥት ታሪክ በሚል ርዕስ ጻፉት። ይህ የአሁኑ መጽሐፍ ከዚህ ትልቅ ድርሰት ውስጥ ስምንተኛ ምዕራፍ ነው። ሌሎች - መዝገበ ቃላት በመባል የሚታወቀው እርሳቸው ግን ርዕስ አልባ የተዉት ረቂቅ፣ ጸወነ ነፍስ፣ ወንጌለ ዘዮሐንስ፣ መዝሙረ ክርስቶስ ወመልክአ ኢየሱስ እና ከላይ የተጠቀሰው መጽሐፈ ሰዋሰው ናቸው። መዝገበ ቃላት የተባለው የሃይማኖት መጽሐፍ ባይታተምም በከፊል በ1963 ዓ/ም ጀምሮ በየወሩ በሚወጣ የምሥራች ድምፅ የተባለች ትንሽ የመካነ ኢየሱስ መጽሔት ላይ በተከታታይ ወጥቷል።

ምንም እንኳን የዘመናዊ የታሪክ አጻጻፍ መስፈርቶችን ባያሟላም ይህ መጽሐፍ በኢትዮጵያ ከተጻፉት የመጀመርያዎቹ ዘመናዊ የኢትዮጵያ የታሪክ መጻሕፍት አንዱ ነው።

የኢትዮጵያን በግዕዝ የተጻፉትን የነገሥታት ገድል ከእነሱም ተተርጉመው በአዲስ መልክ በአማርኛ የታተሙትን ታሪኮች በጠቅላላ ተረት ናቸው። እያሉ የሚያጥላሉ ብዙዎች እንዳሉ እናውቃለን። ብዙ ርቀት ሄደውም በዩኒቨርሲቲ ያለውን የታሪክ የትምርት ክፍል ለረጅም ጊዜ እንዳዘገሙ እናውቃለን። በሌላ ጎን ደግሞ ከተከናወኑ ብዙ ምዕተ ዓመታትን ያለፉቸውን የእነሱን ታሪክ አውሮፓውያኑ ከእየሰዉ እያጠያየቁ የጻፉትን እና እየሰሙ ያደረጉትን አፈ ታሪክ እንደ እውነተኛ አድርገው ሲቀበሉ እናያለን።

እንኳንስ በጽሑፍ የሰፈር፤ አፈ ታሪኮችም በዓለም ዙሪያ በጽሑፍ ሰፍረው እየተጠኑ እንደ ታሪክ ምንጭነት እና መመሳከርያነት እያገለገሉ ናቸው። በዚህ መስክ ጥናት ያደረጉ ስለ ጠቀሜታው እንደዚህ ብለዋል «ያለ ታሪክ ስለ አለፈው ጊዜ፤ የዓለም ሰፊ ክፍል እጅግ በጣም ትንሽ ነበር የምናውቀው። ከውስጥም አናውቅም ነበር።» ከዚህ በታች የቀረበውም በምዕራባውያን የተከናወነ ድርጊት ዓይነተኛ ማስረጃ ይሆናል ብዬ አምናለሁ።

በ1759 እ.አ.አ የፈረንሣይ እና የብሪታኒያ ግጭት አሜርካ ሜይን ውስጥ የአገሪቷን ቀደምት ኗሪዎች የሆኑትን የአቤናኪ ነገዶች አሳትፎ ነበር። በጽሑፍ የሰፈረው የሁለቱ አውሮፓውያን ሃገራት የጦርነት ታሪክ፤ ብዙ ተቃርኖዎች ነበሩበት። ከእነዚህም ውስጥ አንዱን፤ እስከ 1869 እ.አ.አ በጽሑፍ ያልሰፈረው የአቤናኪዎቹ አፈ ታሪክ ሊፈታው ችሏል። እንዲሁም የዓፄ ዘርዓያዕቆብ ገድል (1426 -60) ከንጉሥ ነገሥቱ ጋር ያበረ የሐድያ መሪ የሆነ ባሞን ታሪክ ይጠቅሳል። ሌላ የሐድያ አፈ ታሪክ ቦያሞን ከአሥራ ሦስት እስከ አሥራ ሰባት ትውልድ በፊት አስቀምጦ ከንጉሥ ነገሥቱ ዘርዓያዕቆብ ጋር የነበረውን ግንኙነት ያወሳል። የግዕዙ ጽሑፍ ስለ ሐድያ ሕዝብ አኗኗር ትንሽ ሲነግረን፤ ዕይታው ውስን እና ትክክል እንኳን ባይሆን የሐድያው አፈ ታሪክ ምንም የጽሑፍ ታሪክ ያልገለጸውን ልዩ ስዕል ይዘት እና ቃና ይሰጠናል።

ይህ መጽሐፍ መጀመርያ ከታተመ 94 ዓመት ሆኖታል። በነዚህም ዓመታት ውስጥ ለስድስት ያህል ጊዜም ተደጋግሞ ታትሟል። በ1987 እ.አ.አ ስዊድን ሃገርም ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ

Jan Vansina, Oral tradition as history, The university of Wisconsin press, 1985 pp. 198

ማሁ፤ ገጽ 188፣ 198

ተገርጉሞ ከእነ አማርኛው ለኅትመት በቅቷል። ተደጋግሞ መታተሙም የመጽሐፉን ተፈላጊነት አጉልቶ ያሳየናል። በእርግጥም ብዙ ቁም ነገሮችን ያስጨብጠናል። ለምሳሌ ያህል በውስጡ ከያዛቸው አንዱን እንኩና ብንጠቅስ፤ የወፋ ውጊያ የተባለውን እርስ በእርስ እየተዋጉ ለቆሌ ግብር ደም በማፍሰስ የሰብል ምርት እንዲበዛ እናደርጋለን የሚሉን የሕብረተሰብ ወገኖች ከእነዚህ እኩይ ተግባራቸው በአዋጅ እንዲገቱ አጤ ምኒልክ እንዳደረጉ፤ አዋጁንም ጥሰው በድብቅ የሚዋጉትንም ሰዉ በሞተበት ጊዜ ቅጣት በመጣል ጨርሶም እንዳስተውአቸው ይነግረናል። በዛን ጊዜ የነበሩ የሰሜን ሰው ግን አለቃ ታየን እያሞገሱ አጤ ምኒልክን «ሕዝቡ ለምን አይውደዳቸው ባለህበት እርጋ» ብለውት እያሉ ጣፋጭ የመሰለ ውስጡ ግን እሬት የሆነ የጥላቻ መጽሐፍ ላይ ውሸት ጽፈው ነበር። አጤ ምኒልክ በእየ አባትህ እርጋያሉት ከርስትህ አትነቀልም ለማዕከላዊው መንግሥት ግን ግብር ታስገባለህ ያሉትን በመውሰድ ነው። እንዲሁም አለቃ ታየ ጀርመን ሃገር በነበሩበት ጊዜ በአዩት የምዕራባውያን ስልጣኔ በመደነቅ እኛ ወደ ኋላ የቀረንበት ምክንያት የዕደ ጥበብ ባለሙያዎቻችንን በተለያየ

መጥፎ ስም በመጥራት ተንቀው እንዲኖሩ በማድረጋችን ነው ብለው፤ ይህውም መጥፎ ልማድ በአዋጅ እንዲከለከል ለአጤ ምኒልክ በማሳሰብ በግንቦት 1890 ዓ/ም ደብዳቤ ቢጽፉላቸው፤ ከስምንት ወራት በኋላ በጥር 1900 ዓ/ም አዋጅ ወጥቷል። ንጉሠ ነገሥቱ ለኢትዮጵያ ብዙ በፊት ያልነበሩ አዳዲስ ነገሮችን ሊሠሩ ያቀዱ ሳይሆን በተግባር ያስተዋወቋት፤ ከሩስያዊው ታላቁ ጴጥሮስ ጋር በሃገር አቅኚነት የሚተካከሉ፤ ለጠላቶቻቸው አብዝተው ርኅሩኅ እና ደግ ነበሩ።

በዚህ ጥፋጭ - እሬት - መጽሐፍ ውስጥ..... አንካሳ እንኳን ወታደር ነኝ እያለ.... ወታደር በዛ በደሞዝ የሚተዳደር የተወሰነ ብቻ ያስፈልጋል ይሉናል። አዎ ያስፈልጋል። ከብዙ ጊዜ በፊት አጤ ቴዎድሮስ ሞክረውት ሁሉ ነበር። ማንስ እንግሊዝን እየመራ አምጥቶ እንዳሰናከላቸው መቼ አጡትና! በዝቷል የተባለው ጦር በሰላም ጊዜ አርሶ በላ ነበር። አንኳን በዛን ጊዜ አሁን ዘመናዊዎቹ ሃገሮች በብሔራዊ ውትድርና የአካል ጉዳት ከአሌው በቀር ሕዝባቸውን አሰልጥነው የተቀመጡ አይደሉም? እንደ ዓይነት አውሮፓዊቷን ስዊዘርላንድን እንኳን ብንጠቅስ፤ የሰለጠኑት በሙሉ የጦር መሣሪያቸውን ይዘው ወደ ቤታቸው ስለሚሄዱ ሕዝቧ እንዳለ የታጠቀ ነው። ከሕዝባችን ከአሥር አንዱ ብቻ ተዋጊ ስለ ሆነ ለሽንፈት ተዳረግን ብለው አባ ባሕርይ የጻፉትን፤ መቼም እንደጻፉት እንዲያስታውሱ፤ ደርሶ በአድናቆት ድክም ድክም ለሚሉት እና ለአንፋሽ አጎንባሹ ጭምር አሳስባቸዋለሁ።

ይህ የአሁኑ ኅትም ከአንዳንድ የተተዉ የቀድሞ ስሞች ለውጥ በስተቀር በቀጥታ በ1914 የታተመዉን እንዳለ የያዘ ነው። እንባቢውን የሚያግዙ የበፊት ጊዜ የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ የሚያሳዩ ካርታዎች እና በፊደል ተራ የገቡ የስሞች መጠቁምንም አካትቷል።

ዋቢ

Gustav are’n, Envoys of the Gosphel in Ethiopia, Evangelical pioneers, 1898 – 1936 Stockholm, 1999

Aleme’ Eshete’ Aleqa Taye Gabra Mariam (1861 – 1924) Rassegna di studi Etiopic, Vol. 25 (1971 -72), pp 14 -30

ታደሰ ታምራት፣ ተጨማሪ መቅድም ስለ አለቃ ታየ እና ሥራቸው ባጭሩ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ፣ አዲስ አበባ 1964

ካርታ 1፣ 2 እና 3 Tadesse Temarat, Church and state in Ethiopia 1270 – 1527 Oxford University press, 1972, pp. 10, 133 and 298

ካርታ 4 እና 5 Sven Rubenson, The Survival of Ethiopian independence, Addis Ababa, 1991, pp. 216, 316

# መቅድም

የኢትዮጵያ ሕዝብ መንግሥት የነገሥታቱም ታሪክ በአጭር ቃል የሚነገር። የኢትዮጵያ ሕዝብ መንግሥት የነገሥትቱም ታሪክ ከረጅም ባጭሩ ከብዙ በጥቂቱ አሁን ከተጻፈው አዋጥተን ዋና ዋና ነገሩን በ፯ ክፍል ከፍለን በዚህ እናሳያለን።

ይህንንም ታሪክ ስናወጣው ከልብ አንቅተን ከኅሊና አውጥተን ልብ ወለድ የጻፍነው አይደለም። ከመጽሐፍት ቅዱሳት ከቀድሞው ሰዎች ታሪክ፤ ከመሀከለኞች ከኋለኞችም ሊቃውንት፤ የታሪክ መጽሐፍት ተመልክተን፣ አርመንና አስማምተን ያወጣነው ነው እንጂ።

የዚህ ታሪክ የሚገኝባቸው ከቅዱሳን መጽሐፍ ፩ ነገ ፲ ፩-፲፫። ፪ ዜና ፱፥ ፩-፲፫። ፲፩ ፩። ፪ነገ ፲፱ ፱። ኢሳ ፴፯ ፱። ፪ነገ ፲፱ ፴፭ -፴፯። ፪ዜና ፴፪፥ ፲፱ -፳፫። ኢሳ ፴፯፥ ፴፫ -፴፰። ፪ዜና ፳፩ ፲፮ ፲፯። ኤር ፴፰፥ ፯-፲፫፥ ፴፱ ፲፮፥ ፵፮፥ ፱ ፲ ሕዝ፴፰ ፩-፲። ዳን ፲፩ ፵፫። ናሆም ፫ ፯-፱። ዘፍጥ ፪፥ ፲፫። ዘኁል ፲፪፥ ፩-፲። ሰፎን ፫፥ ፫፥ ፲። መዝ ፷፰፥ ፴ ፴፩፥ ፸፪፥ ፱ ፲፤ ፸፬ ፲፬፤ ፹፯፥ ፬-፭። የሐዋ ፰ ፳፯ -፴፱። ልብ አድርገህ ተመልከት።

ይህን ሁሉ ምዕራፉንና ቁጥሩን እያወጣህ ልብ አድርገህ ብትመለከት ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብና ነገሥታት በዚያ የተናገረውን ታገኛለህ ትረዳለህ። ከቀድሞ ሰዎች ታሪክ ያልነው ከሙርታድ፣ ከግብጽና ከዙሮቴጥ ነው።

ከሊቃውንት ታሪክ መጽሐፍት ያልነው ከብዙዎች በጥቂቶች ከግሪክ ፕሮፌሰሮች፣ ከአማሪካና ከሔሮድቱስ ከእንግሊዝ ፕሮፌሰር፣ ከምስ ብሩስ፣ ከፈረንሳይ ሊቃውንት፣ ከሻንፖሊዎንና ከሞሪዬ፣ ከጀርመን ሊቃውንት ከኢዮብ ሉዶልፍና ከኢዘንበርግ ከአስትራቦን ከሞሰጀር ቄርነር፣ ከፕሮፌሰር ሊትማን ከኢጣሊያን ሊቃውንት ከዲማርቲኒስ ጄ፣ ከሳምኒ ኤሊ፣ ከሳትራቢሮሲ፣ ከኤሊ ቢዞኒ፣ ከጉዲ ኢግናጥዮስ፣ ከምስር ወይም ከአረብ ሊቃውንት ከአዝርቅይ፣ ከግብጽ ሊቃውንት ከኢይብኮ ይሰሐቅ

ከአበልዝና ከአፈልፈረግ ከየመን ታሪክ፣ ከመጽሐፈ እስክንድር፣ ከዮሐንስ መድብር፣ ከጊዮርጊስ ወልደ አሚድ በዝዋይ ከተገኘ የጥንት ታሪክ፣ ከቀድሞው ክብረ ነገሥት፣ ከዚህም የሚበዛ ልዩ ልዩ ዓይነት ታሪክ ተቀስሞ ተለቅሞ ድርሞ የወጣ ነው።

ታሪክ መማርና ማወቅ ለብዙ ነገር ይጠቅማል። መጀመርያ የድንቁርና ዕውርነት ዓይን ይከፍታል። ሁለተኛ ሰው የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት ፍጥረትም ብዛትና የልዩ ልዩ ወገንንም ዓይነት የዓለምንም ታላቅነትና ስፋት ያይበታል።

ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ እስከ ዘመን የሆነውን ሁሉ ነገር ሲማር ጥንት ተፈጠሩ አስቀድሞ እንደ ነበረ ሆኖ ያቃል።

በዓለም ያሉ ልዩ ልዩ ሕዝብ አገራቸውንና ጠባያቸውን የአምላኮቻቸውን መንግሥታቸውን ሥፋትና አኗኗራቸውን በታሪክ ሲመለከት ሲመረምር ሲያስተውልም በቤቱ ተቀምጦ ዓለም ሁሉ ዞሮ መርምሮ እንዳየ ሰው ይሆናል።

የሰውን ደካማነትና ብርታትን በጎነትንና ክፋትን ስንፍናንና ብልሃትን ሐሰትንና እውነት፣ ቁም ነገርንና ተረትን፣ ተንኮልንና ቅንነትም ያለበት ነገር ሁሉንም አይቶ ያውቃል። ላገሩና ለመንግስቱ የሚጠቅመውንም ለማድረግ ይተጋል። በዓለም የሚደረገውን ከንቱነት ሁሉ ይንቃል። ለበጎ ነገርም ይተጋል። የሰው ጠባይን ደካማነትንም አውቆ ልቡን በማስፋት ይታገሣል። ክፉ ነገርንም እየተወም ለብጎ ነገር ይነሳሳል። በዕለቱም ወደ ፊት በውቀትና በብልሃት በበጎነትም ልቡ ይታደሳል። ሰነፎችንም በምክሩና በትምህርቱ ከድንቁርና ወደ ጥበብ ይመልሳል። እንዲሁም አገሩንና መንግሥቱን ያደራጃልና ያሰፋል።

# ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ዘር ከምን ትውልድ እንደ ሆነ ልዩ ልዩ ዓይነት ሕዝቦችም በውስጥዋ እንዳለበት የሚያሳይ

የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት በዋናው ነገር በአራት ክፍል ይከፈላል። ነገደ አሪት፣ ነገደ ካም ወይም ነገደ ኩሳ፣ ነገደ ሴም ወይም ነገደ ዮቅጣን፣ ነገደ እስራኤል ናቸው።

ይህን ስለ አልን የሕዝቡንና የመንግሥቱን ዋና ዋና የሆነ ዓይነተኛውን ክፍል መናገራችን ነው እንጂ በዝርዝሩ ግን በየዘመኑ ከእስያ እየፈለሱ ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ልዩ ልዩ ዓይነት ሕዝቦች እጅግ ብዙዎች ናቸው።

ከነዚህም በስማቸው የታወቁ በየወገናቸው በአምልኮ በቋንቋ በሥርዓትም የተለያዩ ናቸው።

ደግሞ ጥቂቶች ከምን ዘር እንደሆኑ የማይታወቁ በየጊዜው ገብተው የኋለኖች እያስለቀቅዋቸው በኢትዮጵያ ዳር ለዳር የሚኖሩ አሉ። እነዚህም በጣም ስማቸውና ነገዳቸው ያልታወቁ በመልካቸውና በግብራቸው የካም ዘሮች የከነዓን ልጆች ይመስላሉ።

# ፩ ነገደ አሪት

ከሁሉ በፊት አስቀድመው በመጀመርያ ከእስያ ተነሥተው ወደ ኢትዮጵያ የገቡ አገሪቱን ይዘው የነበሩ ነገደ አሪት የተባሉ ናቸው። የዚህም አባት የክብረ ነገሥት ከገጽ ፵ እስከ ፶ እንዳሳየን ከአዳም ልጆች አንዱ አሪ ወይም አራም የተባለው ነው። እርሱ ከ፩ ሺ ፹ ዓመተ ዓለም ጀምሮ ከነልጅ ልጆቹ ፳፩ ነገሥታት እስከ ፪ሺ ፪፻፶፯ ዓመተ ዓለም ፩ሺ ፪፻፲፫ ዓመት በኢትዮጵያ ነገሡ። በመጨረሻም ንጉሣቸው በሶሊማን ታጊ ጊዜ በኖሕ ዘመን በጥፋት ውሃ ተደመሰሱ አለቁ። የነዚሕን ሕዝብና ነገሥታት ታሪኩ ባዲሱ ነገሥት ከገጽ ፲፻፲፯ እስከ ፲፻፴፫ ተመልከት።

እነዚህ ሕዝብ በማየ አይሂ ከጠፉ ወዲህ የኢትዮጵያ አገር ምድርም ሁሉ ከጥፋት ውሃ እስከ ባቢሎን ግምብ መፍረስ በቋንቋ ተለይተው እስከ ሰዎች መበታተን ፫፻፴፩ ዓመት ከሥር ኢትዮጵያ ሰው የሌለበት ባዶ ነበረች። ከዚህ በኋላ ነገደ ካም መጡና ወረሷት።

# ፪ ነገደ ካም

ካም ከእስያ በባብ አልማንደብ ተሻግሮ መጥቶ በኢትዮጵያ ገባ። ይህን የሆነ በ፪ሺ፯፻፹፯ ዓመተ ዓለም ፪ሺ፯፻፲፯ ዓመት ከጌታችን ከኢየሱ ክርስቶስ ልደት በፊት ነው።

ካም በኢትዮጵያ ፸፰ ዓመት ገዝቶ እንደገና ወደ እስያ ሄዶ ሶርያንም እይዛለሁ ብሎ ከሴም ልጆች ጋራ ተዋግቶ በጦር ሞተ። ልጆቹ ግን ታላቅ ወንድማቸውን ኩግን በላያቸው አንግሠው ኢትዮጵያን ወረሱ። ነገደ ካም እስከ የልጅ ልጆቻቸው ፳፫

ነገሥታት ከ፪ሺ፯፻፹፯ እስከ ፫ሺ፭፻፲፭ ዓመተ ዓለም ፯፻፵፫ ዓመት ነገሡ ኢትዮጵያን ገዙ። ክብር ነገሥት ከገጽ ፫፻፴፫ እስከ ፫፻፵፰ እይ።

በነገደ ካም ወይም በነገደ ኩሳ መንግሥት ዘመን ወደ ኢትዮጵያ ስለ ገቡ ሕዝብ፤

በእነዚህ በንገደ ኩሳ መንግሥት ዘመን መካከል ፫ ነገዶች በየጊዜው ወደ ኢትዮጵያ ገቡ። እነርሳቸውም ነገደ ሻንቅላ፣ ነገደ ቅማንት፣ ነገደ ወይጦ ናቸው። ወንድማቸው ሐማቲ ሁሉም የከነዓን ልጆች ናቸው። የነዚህም ነገዶች ሲኒ፣ አዋርዲ፣ ሳምሪ ናቸው። ፬ተኛ ወንድማቸው ሐሜቱ የሱ ልጆች በኋላ በነገደ አግናዝያን ዘመን ወደ ኢትዮጵያ ገቡ።

ስኒ የሻንቅሎች፣ አርዋዲ የቅማንቶች፣ ሳምሪ የወይጦዎች፣ ሐማቲ፣ የሽናሾች አባቶች ናቸው።

የሲኒ ልጆች በእስያ ሲኖሩ መልካቸው እንደ እስያ ሰዎች ነበሩ። በፊት ወደ አፍሪቃ ከመጡ ሻንቅሎች ጋር ቢቀላቀሉ በመጋባትም በአገሩ አየርም እንደ ሻንቅሎች ጥቁሮች ሆኑ። በታችኛው ኢትዮጵያ በሱዳን በኑቢያ ይኖሩ ነበር። በኋላ ወደ ደጋይቱ ኢትዮጵያ ወጡ።

እኒህ የሲኒ ልጆች ከሻንቅሎች ጋራ በመቀላቀል ነው ጥቁሮች የሆኑ። ካሲዮኒ የኢትዮጵያ ንግሥት በነገሡች በ፫ተኛው ዓመት በ፫ሺ፰፱ ዓመት በ፪ሺ፩፻፷፩ ዓመት ከልደት በፊት ወደ ኢትዮጵያ ገቡ። ብዙ ሕዝብ ሆነው ወጡና ከብታቸውን ይዘው ከጭልጋ አፋፍ እስከ በሽሎ አፋፍ ሆነው ወጡና ከብታችውን ይዘው ከጭልጋ አፋፍ እስከ በሽሎ አፋፍ ሰፈሩ። ሰፈሩ ስንል ቦታ እያዩ ተሰማሩ ማለት ነው እንጂ ከጭልጋ እስከ በሽሎ አፋፍ በአንድነት ሰፈሩ ማለት አይደለም።

እኒህም ሻንቅሎች ከብት ከመጠበቅ ሥጋና የዱር ፍሬ ከመብላት በቀር ቤት መሥራት እህል መዝራት ሌላም የሚጠቅም ሥራ አያውቁም ነበሩ። ዋሻ ታላቅ ደንጊያ ያገኙ፤ ከጥሻ ከደንጊያ ተጠጉ። ያላገኙ የቅጠል ጎጆ አድርገው ተቀመጡ። ከብታቸውን ይዘው ሳር ወደ አለበት እያዩ ሲሰፍሩ ሲያበሉ ሲዞሩ ይኖሩ ነበሩና ለጊዜው ለነገደ ኩሳ መንግሥት ገበሩ። ቀምበር በከበዳቸው ጊዜ ብርቱ ጠብ ተጣሉ ጽኑ ውጊያም ተዋጉ። ድል ሲያደርጉ አንዳንድ ጊዜም ድል ሲሆኑ ሲታረቁ ሲሸፍቱም ሲገብሩ እምቢ ሲሉ ሻንቅሎችንም ነገደ ኩሳንም የኋለኞች ኢትዮጵያ ሕዝብ አባቶች በነገደ ሴም ነገደ ዮቅጣን አግናዝያን ሁሉንም አስለቅቀው ወደ ታችኛው ኢትዮጵያ ቆላ በረሃ እስኪያሳድዷቸው ድረስ። ሻንቅሎች ፩፻፵፯ ዓመት በደጋይቱ ኢትዮጵያ ተቀመጡ። ክብ ነገ በገጽ ፻፲፩ እስከ ፻፲፯ እይ።

# ፫ ነገደ ቅማንቶች

ሖር በነገሠ በ፲፫ ዓመት በ፫ሺ፯ ዓመተ ዓለም ፪ ሺ፬፻፲ ከልደት በፊት የአርዋዲ ልጅ የከንዓን የልጁ ልጅ አይነር የቅማንቶች አባት ተከነዓን አገር ተሰድዶ ወደ ኢትዮጵያ ገባ። የከንዓን ልጅ አርዋዲ ፯ ወለደ። ከ፯ቱ አንዱ የአይነር የተባለው ምሽቱን አንተላን ይዞ ከወንድሞቹ ተለይቶ ወደ ኢትዮጵያ ወጣ። ፮ቱ ወንድሞቹ ግን በእስያና በምድረ ግብጽ ተበታትነው ቀሩ። ወደ ኢትዮጵያ የወጣው አይነር በምድረ እስያ በከነዓን አገር ርሃብ በጸና ጊዜ ከወንድሞቹና ከወገኖቹ ተለይቶ ምሽንቱ እንተላን ይዞ ወደ ኢትዮጵያ ወጥቶ ሰው ሳያየውና ሳያውቀው በክርክር ዱር በረሃ እንስሳ አድኖ የዱር ፍሬ ለቅሞ እየበላ ብዙ ዘመን ተቀመጠ። ሰው ሳያውቀው ብዙ ዘመን በዱር ሰለ ተቀመጠ የቅማንቶችን አባት እንጨት ወለደው፤ የእንጨት ፍሬ፤ ከእንጨት የተገኘ ነው የሚሉ አሉ። ነገር ግን በእዚህ ነገራቸው ከንቱ የሐሰት ተረትን ይጫወታሉ እንጂ የእውነት ነገር አይደለም። የሰው ሁሉ ምንጭና አባት አዳም እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። ዘፍ ፩ ፳፯ - ፲፰ ፬፣ ፩፣ ፳፣ ፩ -፴፪ ተመልከት። ጥቂት ተማርን መጽሐፍት መረመርን የሚሉ ግን ስለ ቅማንቶች ትውልድ ሲተርኩ እንዲህ ይላሉ። በኢያሱ ወልደ ነዌ ዘመን ኢያሱንና የእስራኤልን አለቆች በቅርብ ሳሉ የሩቅ መስለው አታልለው ያማልዋቸው ሰብአ ገባዖን በእሥራኤል ርስት መካከል የነበሩና መሀላ እንዳይፈርስባቸው ሳያጠፉዋቸው ለሕዝቡ ሣር አጫጅ እንጨት ለቃሚ አደረጓቸው። ለልጅ ልጅ የእሥራኤል ዜጎች ሆኑ። ኢያሱ ፱፣ ፫ -፳፯። ከዚህ በኋላ በሰለሞን ጊዜ ቀዳማዊ ምኒልክ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ አብረው የመጡ ናቸው። በጥንተ ግብራቸው ንጉሥ በሚኖርበት ከተማ ዜግነት ሣር እያጨዱ እንጨት እየለቀሙ ኖሩ ሲሉ ይተርካሉ። በጎንደር ዙርያ ዜጎች ሆነው ተሠሩ ይላሉ። ይህንንም ባፍ ብቻ ይተርካሉ እንጂ የተጻፈ ቁም ነገር ታሪክ የለም።

ይህ ሁሉ ግን ይወለደዋል ከተባለ ይመስለዋል ማለት አይገድምና ቀዳማዊ ምኒልክ የሰሎሞን ልጅ ከሆነ ሰብዓ ገባዖን የእሥራኤል ዜጎች ከሆኑ ብሎ በምክንያት ነገር አስመስሎ ማጫወት ነው እንጂ ለልብ የሚረዳ እወነተኛ ታሪክ አይደለም። ምነው ቢሉ እኒህ ቅማንቶች በአምልኮት በቋንቋ በወገን የተለዩ አረማውያን ሕዝብ ከቀዳማዊ ምኒልክ እስከ አጤ ፋሲል መንግሥት ፪ሺ፭፻፷፱ ዓመት ያህል ሲቀመጡ ጎንደር ከተሠራ ፪፻፹፬ ዓመት ነው። ከዚህ በፊት ከኢትዮጵያ አገሮች ነገሥታት በሚከትሙበት አጠገብ የት የት ተሠርተው ነበር ብለን ለመጠየቅ ግድ ነው። የቅማንቶች መኖሪያ በክርክር በጭልጋ በኦሮሞ አገር በቦባ፣ በኮሴጌ፣ በጀኒ፣ ፊንቀራ ለዙርያቸውም ባሉ አገሮች ነው ይህ ሁሉ አገርስ አጤ ፋሲልስ የጎንደርን ከተማ ሳይቆረቁሩ በፊት አስቀድሞ የክርስቲያን

ሕዝብ አልነበረበትምን ወይስ አጤ ፋሲል ክርስቲያን ነቅለው አገሩን ለቅማንት ሰጡትን ብለን ለመጠየቅ ግድ ነው። ለዚህ ጥያቄ አናውቅም ተማለት በቀር ሌላ ምላሽ አይገኝለትም።

እኛ ግን እኒህን አሁን የተቆጠሩትን የቅማንት አገሮች ጥንት ከመሠረት አገራቸው እንደ ነበረ በኋላ ግን በዘመነ ክርስትና የክርሲያን ነገሥታት ቅማንትን የክርስቲያን ዜጋ አድርገው ባላያቸው ሥራ እንደሠሩባቸው ባገራቸውም መሀከል ጉልተኛ ሆኖ ክርስቲአይን እንደ ገባባቸው ባገራቸውም ሁሉ አብያተ ክርስቲያናት እንደ ተሠሩባቸው እናውቃለንና ብዙዎች ታሪክ ጻፎች እንደሚሉ የቅማንቶች አባት አይነር በፊት እንደ መጣ አገርንም ይዞ እንደነበረ ነገራችንን በዚህ እናጸናለን።

አይነር ከምሽቱ ከአንተላ ፱ ወንዶች ፳ ሴቶች ወለደ። ስማቸውም እኒህ ናቸው ክብርዋ፣ አይደረኪ፣ አንግሢ፣ ነዚ ይዛናም በእቲ፣ ዳዮን፣ ሽመኒ፣ ከደሴቲ፣ የሴቶች ስማቸው ይህ ነው። ውሸን፣ እቲቱ፣ ፍርዳቀን፣ ኒማልጊ፣ ይባዕስ፣ እኒህ ፳ቱ ሁሉ ባል ሳያገቡ በድንግልና ሞቱ ይላል። ይባዕስ ከሁሉ የበለጠች ታላቅ ሰው ነበረች ይላሉ።

የክብርዋ መኖሪያ በጃኒ ፊንቀራ ሰራክ ሰገር በሚሉት አገር ነው። አይደረኪ መኖሪያው በክርክር ነው። አይደርኪን ቅማንቶች አከበርነው ብለው አባት እናት የለውም ከሰማይ የወረደ ነው ይሉታል። ነገር ግን ይህ ተረት ይቅርና ያለ ጥርጥር የዓይነት ልጅ ነው።

እንግሢ፣ ነዚ፣ ይዘና፣ ሽመኒ፣ ከደሴቲ፣ የክርክር ቅማንቶች አባቶች ናቸው። ዲዮን የጭልጋ ቅማንቶ አባት ነው። በእቲ የኦሮሞ አገር ቅማንቶች አባት ነው።

አንባቢ ሆይ ኦሮሞ አገር ማለት ኦሮሞ ቤት ሁሉ አይምሰልህ በጭልጋና በጋባ አጠገብ ያለ አገር ነው። ትንክበሊ የበአቲ ልጅ በጋባ የሚኖሩ ቅማንቶች አባት ነው። ቅማንቶች ትውልድ ማዕርግና አምልኳቸው ሥራትና ሕጋቸው እንዴት እንደሆነ ባዲሱ ክብረ ነገሥት ገጽ ፻፲፮ እስከ ፻፴ ተመልከት።

# ፬ ነገደ ወይጦ

ከኩሳ የልጅ ልጆች ሳባ ፩ኛ የሚባል ንጉሥ በነገሠ ፲፭ ዓመት በ፫ሺ፻፴ ዓመተ ዓለም ፪ሺህ፫፻፷ ዓመት ከልደት በፊት ነገደ ወይጦ ወደ ኢትዮጵያ ገቡ። ስማቸው

ባባታቸው ስም ዋቶ ነው። ከዋቶ እያደረ ወደ ወይጦ ተመለሰ። ሰምሪ ዋቶን ወለደ። ዋቶ የወይጦች አባት ነው።

መጀመርያ በ፫ሺ፻፵ ዓመተ ዓለም በምስርና በሱዳን አገር ብርቱ ርሃብ ሆነ። በዚያን ጊዜ የዋቶ ነገድ ወይጦች በአባይ ወንዝ ለወንዝ እየሄዱ አዞውን፣ ጉማሬው፣ ይብራውን፣ ጋጋኖውን፣ ሌሎችንም አእዋፍ ዓሣውንም እየበሉ እስከ ኢትዮጵያ ወጡ። ተከፍለው በጣና ባሕር ዙርያ ተቀመጡ። ተከፍለው ግን ወደ ከፋ ሄዱ። በኦሮሞ አገርም ተቀመጡ። በኦሮሞ አገር በከፋ ያሉት እስከ ዛሬ ባባታቸው በዋቶ ስም ዋቶ ወይም ዋታ ይባላሉ። በጣና ባሕር ዙርያ ያሉ ግን በዘመን ብዛት ዋቶ ተለውጦ ወይጦ ተባሉ። ዳግመኛም በኋለኛው ዘመን ነገደ ዮቅጣን ወይም ነገደ አግዓዝያን ወደ ኢትዮጵያ በገቡ ጊዜ ከሌላው ሕዝብ ተለይተው በአምልኮ የማይቀላቀሉ ያገኙትንም እንስሳ ርኩስና ቅዱስ ሳይለዩ ሁሉን የሚበሉ እንደሆኑ አይተው እኒህ ምን ዓይነት ሕዝብ ብለው ጠየቁ ዋቶ ይባላሉ ያገኙትንም ሁሉ ይበላሉ አሏቸው። ነገደ አግዓዝያንም የኒህስ ስማቸው ዋቶ አይደለም ያገኙትን ሁሉ የሚበሉ የማይጸየፉ ናቸውና ስማቸው ውሂጦ ነው አሉ። ስለዚህም በዚያን ዘመን ውሂጦ ተባሉ። ውሂጦ ማለትም ዋጭ ማለት ነው፡ ከዘመን ብዛት ግን ውሂጦ እያደረ ተለውጦ ወይጦ ተባለ ይላሉ። በፊት እንዳልን ወይጦ የተባሉ በጣና ባሕር ዙርያ ያሉ ናቸው። በኦሮሞና በከፋ ያሉ ግን እስከ ዛሬ ዋታ ይባላሉ።

ሁለተኛ በምስርና በሱዳን አገር ያን ጊዜ ተከፋፍለው ቀርተው የነበሩ ወይጦች ወንድሞቻቸው ደግሞ ከስጋዌ በኋላ በ፯፻፵ ዓመት ዓለም የኢትዮጵያ ንጉሥ በነገሠ በ፲ ዓመት ወደ ኢትዮጵያ መጡና በጣና ባሕር ዙርያ ከሚኖሩ ወንድሞቻቸው ተቀላቀሉ። ከነሱም የእስላሞችን ነቢይ መሐመድን ወሬ ሰምተው መሐመድ የአላህ ነቢይ ነው ብለው ተቀበሉ አመኑም። ስለዚህ እንዴት ዋላችሁ ሲልዋቸው አልሐምዲላ ይላሉ ሙስባሕም ባንገታቸው ያሥራሉ ቁርዓንን ግን አይቀበሉምና እንደ እስላም መስጊድና መጾም ጸሎትም አያውቁም። መሐመድ የአላህ ነብይ ነው ብለው አምነው ቁርዓንን የማይቀበሉበትን ምክንያት ታሪክ ለማወቅ ብትሻ በክብረ ነገሥት ገጽ ፻፴፩ እስከ ፻፴፬ ስለ ነገደ ወይጦ የተጻፈውን አንብብና ተመልከት።

# ፫ ነገደ ሸናሸ

የሸናሸ መጀመርያ አባታቸው ሐማቲ ነው። ሐማቲ ጉማን ዥገትን ጎንጋን ዱራን ወለደ። እኒህም አራቱ ወንድማማቾች የሸናሾች አባቶች በዘመነ አግዓዝያን አይባ ሁለተኛ

ስሙ ሰቢ ፪ኛ የተባለ በነገሠ በ፳፱ ዓመት ወደ ኢትዮጵያ ገቡ። ይህም የሆነ በ፫ሺ፪፻፸፱ ዓመተ ዓለም ያዕቆብ ወደ ምስር በገባበት ዘመን ፩ሺ፳፮ ዓመት ከልደት በፊት ነው።

እኒህ የነገደ ሸናሽ አባቶች ከምድረ ከነዓን ርስትን በአጡ ጊዜ ከዚያ ተሰድደው ወደ ምድረ ግብጽ ገቡ። በምድረ ግብጽም እጅግ ሀብታሞች ሆኑ። የግብጾችንም ጥበብ ያስማትንም ነገር ሁሉ ተማሩ። ይህ ሳይቀር በዚያ አንድ ቃዳ የሚሆን መሬት አልነበራቸውምና ለከብታቸው መሰማሪያ ስፍራ አጡ። አርሰው ዘርተው እህል አግብተው የሚበሉት መሬትም አላገኙም። ስለዚህ በግብጽ ሰዎችና በተነሣቸው መህከል ሁልጊዜ ጠብ ክርክር ሁከትም ሆነ። ስለዚህ ነገደ ሸናሻ በጠብና በርሃብ ምክንያት ከምድረ ግብጽ ተሰድደው ብዙ ሠራዊት ሆነው አባይ ላባይ ወንዝ ለወንዝ ወጥተው በዳሞትና በኲታይ ባሞሩ መህከል በአባይ ወዲህ ማዶና ወዲያ ማዶ ሰፈሩ። ከደጋው ኢትዮጵያ ተሰድዶ በአባይ ወንዝ ለወንዝ ከቆላው ተቀምጦ የነበረውን ሻንቅላ ተዋግተው ድል አደረጉትና አጠፉት። አገሩንም ያዙት። ከሞት የተረፈውን ሻንቅላ እስከ ዛሬ የልጅ ባሪያ አድርገው ገዙት። አገሩን አራቱ ነገድ ተካፍለው የአባታቸው ስም ጠሩት። የጉማ ልጆች የተካፈሉትን አገር ባባታቸው ስም ጉማ አሉት። የዠገት ልጆችም ባባታቸው ስም ዠገት አሉት። የጎንጋ ልጆችም ባባታቸውም ስም ጎንጋ አሉት። በአገው ምድርና በነርሳቸው መለያያ ባለው ታላቅ ወንዝ ዳር ያሉ የዱር ልጆችም ወንዙን ባባታቸው ስም ዱራ አሉት። ይህም ዱራ የተባለ ወንዝ ያገው ምድርና የሸናሽ የሻንቅላ መለያያ ነው።

ሸናሾች ቀደሞ በየነገዳቸው የተማ ልጆች ተማ፤ የዠገት ልጆች ዠገት፤ የጎንጋ ልጆች ጎንጋ፤ የዱራ ልጆች ዱራ ይባሉ ነበር። ሸናሽ ወይም ሸናሻ የሚሉ የጥልቅ ስም አልነበራቸውም። አሁን በቅርቡ የአማራ ሕዝብና ቋንቋ ከሰለጠነ እጅግ በዝተው ቀድሞ ሻንቅላን ያጠፉትና አቅንተው የያዘት አገር አልበቃቸ ብሎ ደግሞ ወደ ላይ ወጥተው አገውን ዳሞትን ይወጉ ይዘርፉ ነበርና ከዕለት አንድ ቀን ጩኸት ሽብር ሆነ። ምን ጩኸትና ሽብር ነው ብለው የዳሞት ሰዎች እርስ በርሳቸው ቢጠያየቁ እጅግ ብዙ ሸናሽ የሆነ ሕዝብ ለጦርና ለዘረፋ መጣብን አሉ። ስለዚህም እነዚህ ሕዝብ ሸናሽ ማለትም በአማርኛ ቋንቋ እጅግ ብዙ ማለት ነው።

ሸናሾች አረማውያን ናቸው። ዛሬ ግን በዳሞት ድምበር በጉመር አጠገብ በማቢቢል በኮሌ ያሉ ክርስቲያኖች ከሆኑ ብዙ ጊዜያቸው ነው። ከዱራ ወዲያ ማዶና በአባይ ዙርያ ያሉት እስከ ዛሬ አረማውያን ናቸው። አምልኳቸውም እንደ ኦሮሞ በወፍ ባሞራ በድንጋይ በዛጎል መጣል በሙዋርተኝነት ነው። የቀድሞ አባቶቻቸው ከምድረ ግብጽ አስማተኞች እንደተማሩት እስከ ዛሬ ብዙ አስማተኞችና ባለ መድኃኒቶች አሉ።

ጽፈትና መዳፍ ግን አያውቁም፤ የላቸውም። ከዚህ የቀረውን የሽናሾችን ሙሉ ታሪክ በክብረ ነገሥት በገጽ ፻፴፬ እስከ ፻፴፰ ተመልከት።

# ፮ ነገደ ዮቅጣን

እኒህ ነገደ ዮቅጣን የሴም የልጅ ልጆች ናቸው። ሴም ፲፭ ልጆች ወለደ። ከ፲፭ቱ ፫ኛው አርፋክሳድ ነው። አርፋክሳድ ቃይናን ወለደ። ቃይናንን ሳላን ወለደ። ሳላ ዔቦርን ወለደ፤ ዔቦር ፋሌክንና ዮቅጣንን ወለደ። ዮቅጣን በግእዝ ዮቃጢን ባማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ዮቅጣን ዘወዲያ አገር መጽሐፍ ዮቅታን የካታን ይባላል። ዮቅጣን ፲፫ ልጆች ወለደ፤ ስማቸውም አልሞደድ፣ ሣልፍ፣ ሀስረሞት፣ ያራህ፣ ሀዶራም፣ አውዛል፣ ዶቅላ፣ ሁባል፣ ወይም ኑባል አቢማኤል፣ ሳባ፣ አውፊር፣ ሀላዊ፣ እና ዮባባ ናቸው። ዘፍጥ ፲፤ ፳፭ -፳፱ ስፍራውም በእስያ ምድር ከሜሻ እስከ ሥፋር እስከ ምሥራቅ ተራራ ድረስ ነው። ዘፍ ፲ ፴።

ከነዚህ ከ፲፫ቱ የዮቅጣን ልጆች ፮ቱ ሳባ፣ አውፌር፣ ሀላዊ፣ አባል፣ አሚባኤል፣ ቦታ ባነሳቸው ስፍራ በጠበባቸው ጊዜ ከእስያ ተነሥተው ብዙ ሠራዊት ሆነው ሲፈልጉ ሲሄዱ ሲጓዙ የመን ደረሱ። እኒሁ የሴም ዘር ነገደ ዮቅጣን ወደ የመን በገቡ ጊዜ ምንም በፖለቲካ ምክር ባይስማሙ ለኩሳ የመን ይገብሩ ነበር። በኋላ ግን የኩሳ የመንን ደካማነት አይተው በተንኮልም በሌላም ጥበብ እርስ በርሱ አሸፍተው ከወገናቸው ያሮባ የሚባል ብልሀተኛ ጀግና አንግሠው ለየመን ሁሉ ባለቤቶች ሆኑ። ከነዚህ ነገድ በነገደ ካም መንግሥት መጨረሻ በጲኦሪ ፩ኛ ዘመን በነገሠ በ፲ ዓመት በ፫ሺ፭፻፲ ዓመተ ዓለም በሺ፭፻፪ ዓመት ከልደት በፊት አግናዝያን ተባለ። ከነገደ ሴም ዮቅጣን ከየመን ተነሥተው ብዙ ሠራዊት ሆነው በባብ አልመንደብ ተሻግረው ወደ ኢትዮጵያ ገቡ።

በዚያ ዘመን ዮቅጣን በየጊዜው በ፫ ስም ይጠሩ ነበሩ። ሳቦች፣ በደዎች፣ እረኞችም ትግሪዎች፣ አግያዝያን ይባሉ ነበር። በየጊዜው በዚህ ስም የተጠሩበት ምክንያት በክብረ ነገሥት ከገጽ ፫፻፶፫፤ ፫፻፶፪ እይ።

ኢትዮጲስ የአክሁናስ ሁለተኛ ሳባ የተባለው የልጁ ልጅ የቡልቃያ ልጅ ነው። እናቱም የቱት ንጉሥ ልጅ አግለዔ ትባላለች። ክብረ ነገሥት ገጽ ፫፻፷፬፤ ፫፻፷፰ ተመልከት። ኢትዮጲስ ፩ኛ ከ፫ሺ፪፻፵፬ - ፫ሺ፪፻ ዓመተ ዓለም ከ፳፻፶፪ - ሺ፰፻ ዓመት ከልደት በፊት ፶፪ ዓመት ነገሠ። አገሩም በስሙ ኢትዮጵያ ተባለ። ኢትዮጲስ

ወይም ኢትዮጵያ ትርጓሜው ምን እንደሆነ በክብረ ነገሥት ከገጽ ፻፱ -፻፲፪ ተመልከት። ደግሞ ገጽ ፫፻፫ -፫፻፫፩ እይ።

ኢትዮጲስ ፩ኛ ከሞተ በኋላ በመንግሥቱ ልጅ ላከንዱን ሁለተኛ ስሙ ኖወርአር የተባለው ተከተለው። ክብረ ነገሥት ፫፻፯ -፫፻፫፯ እይ።

የኢትዮጲስ ፩ኛ ልጆች ፭ ናቸው። እነርሳቸውም ላከንዱን፣ ሳባ፣ ኖባ፣ በለው እና ከለው ናቸው። የመጀመርያ ልጁ ላከንዱን መንግሥት ወረሰ። ፬ቱ ግን ያገር ርስትን ተካፍለው ያዙ። ሳባ አሁን ትግሬ ተብሎ በሚጠራው አገር የተቀመጡት ሕዝብ አባት ነው። አገሩም በርሱ ስም ሳባ ተብሎ ይጠራ ነበር። የመንግሥት መብቀያና ግንዱ ሆነ የሚሉ አሉ። ሳባ በኢትዮጵያ አያት ነው እንጂ በኢትዮጵያ ልጅ ሳባ አይዶለም። ይህም በዚህ ዝመአን አገሩ እብስሙ ሳባ ይባል የነበረ የኢትዮጲስ አያት የነገደ አግያዝያን መጀመርያ ንጉሥ ነገሥት በታቹ ወንድሞቹንና የወንድሞቹን ልጆች አንግሦ እርሱ ሰባተኛ በላይ ንጉሥ ነገሥት የሆነ ታላቅ ንጉሥ ነው። ክብረ ነገሥት ገጽ ፫፻፳፫ -፫፻፳፰ እይ።

በለው የአንበሳና የባርክ ወንዝ መረብም የሚወርድበት ከሰባ ወደ ሰሜን ባለው ምድር ሁሉ ተቀመጠ። አሁንም በደጭና (ሂርጊጎ) ያሉት ናይቦች ከበለው የወረዱ ዘር ናቸው። ባላባቶችም ናቸው። ባላገሮችም በለዎች በሰገላና በሐማሴን ይቀመጣሉ።

በበለው ምድር የሚነገሩ ቋንቋዎች በደውኛና ትግሬ፣ ሀድ ዓረብ ናቸው። በደውኛ ከግእዝና፣ ከትግሪኛ፣ ከዓረብኛም ጋር ይመሳሰላል። ከዕብራይስጥም ጋራ እንዲሁ በጣም ይመሳሰላል። የበለው አገር እጅግ ባለ ከብት ሰፊ ያንድ ንጉሥ አገር ነበር። ወሰኑ በምዕራብ አትባራ ወይስ ተከዜ ነው።

ኖባ ምድሩ ከበለው ወደ ምዕራብ ከአትባራ ወዲያ ነው። ነጭ አባይና ጥቁር ዓባይ ካገሩ ላይ ይፈስሳሉ። ይህ አገርና ሕዝብ መንግሥቱ ኃይለኛ ነበርና ግብጾችን ያጠቃቸው ነበር። አገሩም እጅግ ፍሬያማ ነው። እስላም ሳያሸንፋቸው በፊት የበለው መንግሥትና የኖባ መንግሥት ለሳባ መንግሥት የታወቁ ነበሩ። የኖባ መንግሥት ዛሬ እስላም ሆነ።

ከለው ከሳባ ወደ ምዕራብና ወደ ደቡብ ያለ የአማራ ወልቃይት የጠገዴ ሕዝብ አባት ነው። ከነዚህም የኢትዮጲስ ልጆች የወንድማማቹ ነገድ ሕዝብ ሁሉ በመልካቸውና በቁርበታቸው ይመሳሰላሉ። ከሌሎች ከአፍሪቃ ሕዝብ ተለይተው በልዩነት የሰው ልጆች ተብለው ይጠራሉ። እኒህም ሕዝብ የያዙት አገር በጥቅሉ ባባታአቸው ስም ኢትዮጵያ ተብሎ ይጠራል።

ከኢትዮጵያ ሕዝብ ዋና ባላባቶች የሴም ዘሮች ፯ ወገን ናቸው። እርሳቸውም አማራ፣ ትግሬ፣ አገው፣ በደው፣ አስገዴ፣ ብቅላ እና ሐባብ ናቸው። በደው፣ አስገዴ፣ ብቅላ ሐባብ እኒህ ፫ቱ በእስላም ሃይማኖት ገብተው ከወንድሞቻቸው ተለይተው ልዩ ወገኖች ሆነዋል።

አማራ፣ ትግሬ፣ አገው ግን በፊት በቀዳማዊ ምኒልክ ጊዜ በሕገ ኦሪት ያመኑ በኋላም በክርስትና ያመንኑ በኢየሱስ ክርስቶስ ሃይማኖት የጸኑ ከጥንት ጀምሮ መንግሥት ያልጠፋባቸው ባዕድ ገዢ ያልገባባቸው የእግዚአብሔር ረድኤት ያልረቀባቸው ሕዝብ ናቸው።

ከዚህም ሁሉ ጋራ አማሮቹ፣ ትግሮቹ፣ ኢትዮጵያ ዓይነተኛ ባላገሮችና ባላባቶች የሆኑ ከሴም ዘር ከነገደ ዮቅጣን ልጆች ከእሥራኤልም ዘሮች እንደሆኑ የሚያስረዳ ብዙ ምስክር አላቸው። እርሱም በ፲፩ ክፍል ይከፈላልና ምስክሩ ይነግራል።

መጀመርያ ምስክር ከሴም ዘር ከእስራኤል ወገን እንደሆኑ የሚያስረዳ ከልዩ ወገን በመብል በመጠጥ በመጋባትም አልመቀላቀላቸው ነው። ሁለተኛ ምስክር አለ ነርሳቸው የሚናገር በዓለም የሚገኝ ታሪክ ነው። ሦስተኛ ከመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢትዮጵያ የተነገረ ትንቢት ነው። አራተኛ አምልኳቸው ነው። አምስተኛ ግዝረታቸው ነው። ስድስተኛ መልካቸው ነው። ሰባተኛ ጠባያቸው ነው። ስምንተኛ ቋንቋቸው ነው። ዘጠነኛ ስማቸው ነው። አስረኛ ስመ ሃገራቸው ነው። አሥራ አንደኛ ልማደ ሃገራቸው ነው።

የእነዚህ የ፲፩ዱን ክፍሎች ምስክሮች ዋና አስረጁን በዚህ አንዳንጽፈው በየክፍሉ እጅግ ብዙ ነውና ነገር እንዳናበዛ በዚህ ተውነው። ሙሉ ክፍሉን ልታይ ብትወድ በክብረ ነገሥት ከገጽ ፶፮ - ፻፹፬ በየክፍሉ እያነበብህ ልብ አድርገህ አስተውለህ ተመልከት።

# ፯ የትግሬ ሕዝብ ታሪክ

በነገደ ኩሳ መንግሥት ጊዜ በዚያ ዘመን የሕንድ ነገሥታት በርትተው ወደ የመን የመጡ በጦር በዘረፋም ባወኳቸው ጊዜ በየመን ከነበሩ ፩ቱ ነገድ ዮቅጣን ሁለት ነገድ አቢማኤልና ነገደ ህላዊ ከዚያው በየመን ቀሩ።

ሦስቱ ነገድ ስባ ነገድ አባል ኦፊር በነገደ ካም በኩሳ ዘር መንግሥት መጨረሻ በጲኦሪ ፩ኛ ዘመን ከየመን ተነሥተው ወደ ኢትዮጵያ መጡ። ጥቂት ጊዜ በአንድ ተቀመጡ። ከዚህ በኋላ ሦስቱ ወንድማማች ነገዶች በምክር ተለይተው አገርን ያዙ

አግያዝያን የተባሉ ነገድ ሳባ በትግሬ ሰፈሩ። ነገደ አባል በአዳል አገር ተቀመጡ። ነገደ አፊር በውጋዲን ተቀመጡ።

ነገደ ሳባ ነጋዶች መስለው ሆነውም ለነገደ ኩሳ መንግሥት ቀረጥና ግብር በመስጠት ጥቂት ዘመን ስለ ተቀመጡበት የዚያን አገር ስም ትግሬ አሉት። ትግሬ ማለት በቋንቋቸው ባረብኛም ነጋዴ ማለት ነው። ከነዚህ ሕዝብ በላይ የኢትዮጲስ ፭ኛ ልጅ ሦስተኛ ሳባ ጉልተኛ ሆኖ ተሠርቶባቸዋል።

ትግሬ አማራ ማለት የግብር ስም ነው እንጂ እንደ ሳባ እንደ ኖባ የተጸውኦ ስም አይደለም። የትግሬ ታሪክ በነገር ምክንያት በክብረ ነገሥት በገጽ ፻፹፪ ተጽፎልሃል እይ። የትግሬ ሕዝብ በጊዜው ፫ ስም ወጥቶለታል ሳባ፣ በደው፣ እረኞች ወይም ዘላን ትግሬ፣ አግአዚ፣ ክብረ ነገሥት ፻፹፬ ከ፫፻፸፱ - ፫፻፵፫ ፻፵፮ - ፻፵፯ እይ።

# ፰ የአማራ ሕዝብ ታሪክ

ስለ አማራ ሕዝብ ታሪክ አቶ አጽሜ ስለ ኦሮሞ በጻፉት ታሪክ በ፷፪ኛውና በ፷፫ኛው ገጽ የሚገኝ እንዲህ ይላል ጨዋና ባለጌ ባላገር ልዩ እንደሆነ ተመልከት። ባለጌ ባለ ርስት ባለ መሬት ነው። ጨዋ የንጉሥ አሽከር ነው። እርሱም በባላገር ላይ የተሠራ ምሪተኛ ነው። በዛሬ ቋንቋ ወታደር ይባላል። ለዚህም ወታደር በየነገሠው ንጉሡ ዘመን በየአለቃው ልዩ ልዩ የጀግንነት የክብረት ስም ያወጡለታል። ደግሞ ያንዱን ነገድ ካንዱ ነገድ ለመደባለቅ የንጉሦች ልማድ አላቸው። ስለዚህም ለወታደሮች መልከኝነት እያሉ ፩ ጭቃ ፫ ጭቃ መሬት እያደረጉ ይሰጧቸዋል። ያም ወታደር በማያውቀው ሕዝብ ላይ ጨዋ ይሆናል። የመጣበት የማይታወቅ ብዙ ዓይነት ጨዋ በኢትዮጵያ ተሠርቷል። በደምብ ጨዋ እየተባለ ሃይማኖት የሌለው ሳይቀር ከጨዋ ተቆጥሮ ከባላገር ላይ ተሠርቷል።

ያማራና የትግሬ አባት የሴም የልጁ ልጅ የኤቦር ልጅ ዮቅጣን ነው። በመልክ በጠባይ በቋንቋ ጥቂት ጥቂት ይለያሉ እንጂ ብዙ ነገር ይዋረሳሉ። አማሮችና ትግሮች ደግሞ እንደ ነገደ እስራኤል ልጆች ሹልዳ ሥጋ አይበሉም። ክብረ ነገሥት ገጽ ፪፻፷፮ ተመልከት ደግሞ ፻፹፮ ገጽ እይ።

ያማራ ሕዝብ የነገደ ሴም ወገኖች የዮቅጣን ልጆች የእስራኤል ዘሮች እንደሆኑ ፈጽሞ የሚያስረዳ ጠባያቸው ልማዳቸው መልካቸው ስማቸው ስመ አገራቸው

ቋንቋቸው። ከብረ ነገሥት ገጽ ፻፶፮ -፻፹፩ ተመልከት። መንግሥቱ ያማራ ስለሆነ አማርኛ ሰለጠነ። ልዩ ልዩ ሕዝብ ቋንቋቸውን እያጠፉ አማርኛ የሚናገሩ ብዙ ወገኖች አሉ። እነህም ደምቢያዎች ቋሮች ጋፋቶች የወሎ ኦሮሞዎች የጀች ወይም ወረሴሆች ናቸው። እንዲሁም የወፍላ ሀሽንጌ ኦሮሞዎች ኦሮምኛን አጥፍተው ትግሪኛ ይናገራሉ። ዳግመኛም እንዲህ ይላል አንድ ጫዋ መዳባይ በቀዳማዊ ምኒልክ ጊዜ የነበረ ነው። በትግሬ በጠለምት በሰሜን በወገራ የተሠራ ወታደር ነው። ከእርሱም በኋላ የነገሡ እንዲሁ አደረጉ።

ሦስተኛው በዚያ የታሪክ መጽሐፍ እንዲህ ይላል፤ ኋላም በ፲፩፻፴ ወይም ፶ ዓመተ ምሕረት በላሊበላ ንጉሥ ዘመን አማራ የተባለ ወታደር በዋድላ፣ በበጌምድር፣ በሳይንት፣ በወለቃ ጨዋ ሆኖ በባላገሩ ላይ ተሠራበት። ሳይንት ባላገሩ አረመኔ ነበር በእባብና በዘንዶ ያመልክ ይታመን ነበረ። መታመኛ ሲሉ ዘንዶውን እባቡንም ተመን አሉ። ይህንኑ ሕዝብ ሕዝቡ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ያስተምሩት የነበሩ ፲፪ ዓእምት በዚያ ወንጌልን ሲሰብኩ ካማሮች ጋር ተዋወቁ ከዛጓ ቤት ወደ ምኒልክ ቤተ መንግሥትን ለመመለስ በዚያ ነው የመከሩ።

አማሮች ጥንቱንም ክርስቲያኖች ናቸው የነበሩ ስለዚህ ኦሮሞ ወይም እስላም ክርስትና ሲነሳ አማራ ሆነ ይባላል። በአገሩ ልማድም አንድ ሰው ከባልንጀራው ጋር ሲጣላ አንተና እኔ ከንግዲህ ወዲህ እስላምና አማራ ነን ይላል። ይህም አንተና እኔ እንደ ክርስቲያንና እንደ እስላም በሃይማኖት በንብረት አንድነት የሌለን ነን ማለት ነው።

አምሃራ ወይም አማራ ማለት አራሽ ማለት ነው። ሳይንት ማለትም ባረቢኛ የእህል መከማቻ ጎተራ ማለት ነው።

አማሮች ይኵኖ አምላክን አንግሠው ከዛጓ ነገድ የሚሆን ይትባረክ ንጉሥን ዋድላ ላይ ገደሉት። ከአማራ ሕዝብ ነገር ታሪክ መርማሪዎች ከኤውሮጵም የመጡ አማራ ከወዴት የመጣ ሕዝብ ነው ሲሉ እጅግ አድርገው ይጨነቃሉ። ሕዝብ ካንድ አገር የወጣበትና የፈለሰበት ይታወቃልና። ከክርስቶስ ልደት በኋላ ከእስያ ፈልሰው ወደ ኤውሮጵ የገቡ ሕዝብ በየነገዳቸው ስማቸው ተለይቶ ይታወቃል። መቸም እስያ የሕዝብ መፍለቅያ ምንጭ ናትና።

አማራ ግን ከወዴትም አልመጣም። ጥሩ የላስታ ወታደር ከያይነቱ ተጠራቀመ፤ ኃይለኛ፣ ግፈኛና አድመኛ፣ እወቀት ያለው ያልተማረ ጨካኝ ጭፍራ ነው።

ብዙ አዋቂዎች ታሪክ መርማሪዎች ግን እንደ መሰላቸውና እንደ አገራቸው ልማድ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል። ንጉሥ ላሊበላ ወንድሙ ባሳደደው ጊዜ ምስር ወረደ፡ ከዚያ

እስላም ያቅባበዛቸውን ክርስቲያኖች ፷ሺ የሚያህሉ ሰብስቦ በአባይ ወንዝ ለወንዝ ይዟቸው ሲመጣ ነጭ አባይና ኒል ዓባይ በሚገኙበት ውሃውን ወደ ሰሃራ ሊመልሰው ቆፈረው ይህንንም ማድረጉ እስላሞች ክርስቲያኖችን ስለ በደሉ ብድር እስላሞች ለመበደል ነው። ያ ስፍራ ዛሬ ካርቱም ይባላል። ካርቱም ማለት በትግሬኛ ቁርጥ ማለት ነው። ከዚያ ወጥቶ ጎጃም ሰፈረ። ይህን ሠራዊት ይዞ ከወንድሙ ከአጤ ጋራ ተዋግቶ መንግሥትን ያዘና ሮሃ ገባ። በሮሃ ያስወቀራቸውን ቤተ ክርስቲያኖች በእነዚህ እጅ ነው ይላሉ።

እኛስ የሰማነው አባቶቻችንም የነገሩን ከጥንት የነበረን ያቆዩን ኢትዮጵያ የአፍሪቃ ሰሜን ምሥራቋ የኢትዮጵያ ልጆች ሳባ ኖባ በለው ከለው የሚባሉ ኢትዮጵያን እንደገዟት ሀምያር የሚባል ዓረብ ሁሉ ጠቅሎ እንደ ነገሠ ከእነሱም የሚሰበሰበው ወታደር ስለ አገልግሎቱ በባላገሩ ላይ ጨዋ መሠራቱን ነገሩን።

አማሮች ግን ይኰኖ አምላክን ካነገሡ በኋላ ሰው ሁሉ አማርኛ ይናገር ጀመር። ይኸውም አማርኛ ካባታቸን ከኢትዮጵያ ልጆች የመጣ ቃል ነው እንጂ እንደ ሌሎች እንደ ኦሮሞዎች ከውጭ ሕዝብ የመጣ ቋንቋ አይደለም። አማርኛ ከዕብራይስጥ ከትግሬ ከዓረብ የመጣ ነው እንጂ በምንም ምንም ከሌላ ቋንቋ የሚገናኝበት ቃል የለም።

አማርኛ ቋንቋ መናገር የጀመሩት ዘመን ግን የተንኮል ዘመን ኖሯል። ፫፻ከ፶ ዓመት የኖረው የላስቶችን መንግሥት አፈረሰ። በብርቱ ግዕዝና ዓረብ ትግርኛ የማያውቅ አማርኛ ቢነግሩት አይሰማም። ከቶውንም አማራው ያማራውን ቃል አይሰማውም። ያመሰገነው መስሎ ቢረግመው ደስ ይለዋል ይስቃል። ይስድበው መስሎ ቢያመሰግነው የረገመው መስሎ ቢመርቀው ያማርኛን ጥልቅ አነጋገር የሚያውቅ ይከፋዋል ይቆጣል።

አዝማሪ በጥሩ አማርኛ ቢዘምር፤ በላይ የሚሰማ አማርኛ አልብሶ በውስጥ ቢሳደብ ወይም ቢያከብርና ቢያመሰግን አማርኛን እጅግ አጥብቀው ካወቁ በቀር ሁሉ አያውቀውም የሚያስተውለው የለም። ጎጃሜ ሲናገር ሸዌ ይቅርና በጌምድር አያውቀውም እገሌኮ እገሌን በአማርኛ ተናገረው ይባላል። አማርኛ ማለት በፈረንጅ ቋንቋ ፖለቲካ ማለት ነው። ስለዚህ አማራ የኢትዮጲስ ልጅ ነው። ቋንቋውን የረዘመውን አሳጥሮ በተንኮል አዛውሮ በመናገሩ ፫፻፶ ዓመት የኖረውን መንግሥት አፈረሰ። እርሱም በባላገር ላይ ጨዋ ሆኖ የተሠራ ሠራዊት ነው። እስከዚህ ከቶ አጽሜ መጽሐፍ የተቀዳ ታሪክ ነው።

የወዲያ አገር ታሪክ ጻፎች ያማራ ሕዝብ ከወዴት እንደ መጣ አይታወቅም፤ ዳግመኛም ንጉሥ ላሊበላ አስቀድሞ ሳይነግሥ ወንድሙ ባሳደደው ጊዜ ምስር ሄዶ

እስላም ያቅበዘበዛቸውን ክርስቲያኖች ፳ሺ የሚያህሉ እነኚህን አማሮች ይዞ ወደ ኢትዮጵያ እንደ መጣ ከወንድሙ ከአጤ ጋር ተዋግቶ ድል አድርጎ መንግሥትን እንደያዘ እኒህም አማሮች በሮሃ አገር የድንጋይ ቤተ ክርስቲያኖች ወቅረው እንደ ሠሩለት ስለሚሉም ይህ ፍጹም ሐሰት እንደሆነ አቶ አጽሜ መልካም አድርገው ምላሽ ሰጥተውበታልና አማራ የኢትዮጵያ ልጅ እንደሆነ ከሌላ ወገን እንዳደለ ቋንቋውም ከአያቱ ከዕብራይስጥ ካባቱ ከግእዝ ከወንድሞቹ ከዓረብ ከትግርኛ የመጣ እንደሆነ አስረድተዋል።

እኛም ስለ ኢትዮጲስና ስለ ኢትዮጵያ በጻፍነው ከሴም ዘር ከዔቦር ልጅ ከነገደ ዮቅጣን ከአግዝያን ዘር እንደሆነ የግእዝ የትግሬ ያማራ ቋንቋም ከዕብራይስጥ የመጣ እንደሆነ በብዙ ምስክር አሳይተን አስረድተናል።

በአጤ ይኵኖ አምላክ ጊዜ አማርኛ ቋንቋ ተጀመረ ማለት ፍጹም ጨዋታና ተረት ተርታ ነገር ነው። በአጤ ይኵኖ አምላክ ጊዜ ያማርኛ ቋንቋ ፈጽሞ ሰለጠነ። ያማረ የተወደደ ጉሮሮ የማያንቅ ለንግግር የሚያውቅ ሆኖ ስለ ተገኘ የቤተ መንግሥት ቋንቋ ሆነ እንጂ ንግግሩስ አስቀድሞ ከዚህ በፊት እጅግ ብዙ ዘመን የነበረ ነው። አጤ ይኵኖ አምላክ የነበሩና የነገሡ አሁን በቅርቡ በ፯ሺ፫፻፹ ዓመተ ዓለም በሺ፰፻፹ ዓመተ ምሕረት ነው ከአጤ ይኵኖ አምላክ መጀመርያ መንግሥት እስካሁን እስከ ዘመናችን እስከ ፲፱፻፲፫ ዓመተ ምሕረት ፯፻፷ ዓመት ነው። አማርኛ ቋንቋ በዚህ ዘመን ብቻ ተነገረ ማለት እንደ ተረት ያለ ጨዋታ ታሪክ ነው። ከዚህ አስቀድሞ ከ፳ሺህ ፳፪ -፯ ሺ፬፻፴፫ ዓመት ከአጤ ይኵኖ አምላክ በፊት ከሺ፯፻፵ ዓመት የሚበልጥ አማርኛ ቋንቋ እንደ ነበረ በፊተኛው ክብረ ነገሥት ተጽፏል። ከዚያ ዘመን ውስጥ ከነገሡት አያሌ የነገሥታቱ ስም በአማርኛ ቋንቋ ነበረ።

ይህም ሊታወቅ ወረደ ነጋሽ አግባ ጉማስጎምጉም ለትም ተላትም ያደ ጎሽ አይዘር መራ ተክለ ሃይማኖት በመባላቸው ይገለጣልና ይታያል። በፊት አማርኛ ቋንቋ ተሌለ ይህ ሁሉ ስም ከምን መጣ። ሁሉ በግእዝና በትግርኛ የሌለ ያማርኛ ስም ነው። ነጋሽ ጎሽ ይህ የዓረቢ ፊደል ያማርኛ ቃል ነው እንጂ በግእዝ ሽ፣ ኛ፣ ጀ፣ እና ጨ የሚል ቃል አድን እንኳን አይገኝም። በግእዝ ነጋሽ ነጋ ጎሽ ሲል ጋሙስ ይላል ዓረቢ ፊደል ምንም የለበትም።

ዳግመኛም ይህ አስቀድሞ በፊት የነበረ በአማርኛ ቋንቋ ስማቸው የተጠራ የነገሥታቱ ስም በንጉሥ ላሊበላ ዘመን አማሮች ከምስር መጡ ብለው ታሪክን የጻፉ ሰዎችን አሳብ ያፈረስባቸዋል። አማራ ሕዝብ ከነገደ ዮቅጣን ከኢትዮጲስ ዘር እንደሆነ

ገልጦ ያሳይባቸዋል። ከዚህ ቀጥለን ስለ ነገደ እስራኤል ወደ ኢትዮጵያ መምጣት እንጽፋለን።

# ፱ የነገደ እሥራኤል መምጣት

በእሥራኤል ንጉሥ በሰለሞን ዘመን መከዳ የኢትዮጵያ ንግሥት በመጽሐፍ ቅዱስ የሳባ የዓዜብ ንግሥት የተባለች (፩ ነገሥት ፲፩ ማቴ ፲፪ ፵፪።) የሰለሞን ጥበብ ወሬውን ሰምታ እሱን ለማየትና ጥበቡን ለመሰማት ከብዙ ጓዝ ጋር ወረደች። ከሰለሞን ቀዳማዊ ምኒልክ ጸንሳ ወዳገርዋ ተመለሰች። ካገርዋ ስትደርስ ወለደችው። ስሙንም የብልሃተኛ ልጅ ስትል እብነ እል ኪም አለችው። ከእናቱ ጋር አድጎ ፳፪ ዓመት ሲሆነው አባቱን ሰሎሞንን ለማየት ወደ ኢየሩሳሌም ወረደ። በዚያ ሕገ ኦሪትን ሕገ መንግሥትን የዕብራይስጥን ቋንቋ እየተማረ ፫ ዓመት ተቀመጠ። ከዚህ በኋላ አባቱ ንጉሥ ሰሎሞን በኢትዮጵያ እንዲነግሥ ከ፲፪ ነገደ እስራኤል ፲፪ ሺህ የበኵር ልጆቻቸውን ብልሆችና አዋቆች የሆኑትን መርጦ፤ ከተማሩት ከካህናት ልጆችና ከመኳንንት ልጆች ፳፪ ታላላቆች አለቆች ሹሞ፣ ልጁ ቀዳማዊ ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሥ ይሆን ዘንድ ልብሰ መንግሥት አሰፍቶ፤ ቅብአ መንግሥት በሊቀ ካህናቱ እጅ አስቀብቶ፤ ሕገ ኦሪትን፣ ሥርዓተ መንግሥት ሰጥቶ፤ ወደ ኢትዮጵያ መልሶ ሰደደው። እኒህ የእስራኤል ነገድ ከእርሱ ጋር ኢትዮጵያ ገቡ። የገቡበት ዘመንም በ፬ሺ፭፻፲፫ ዓመተ ዓለም በ፱፻፹፪ ከልደት በፊት ነው። ከብረ ነገሥት ገጽ ፻፹፫ እና ፻፹፱ እይ።

የእስላሞች ዋና መጽሐፋቸው ፉርቃን ወይም ቁርዓን የሚሉትና የየመን ታሪክ ስለ ንግሥተ መከዳ ወይም ንግሥተ ዓዜብ ሲናገር እንዲህ ይላል፤ የሳባ ንግሥት የተባለች ንግሥተ ዓዜብ የየመን ንግሥት ናት እንጂ የኢትዮጵያ ንግሥት አይደለችም። ስሟም በልቂስ ነው እኒ መከዳ አይደለም። የበልቂስ የእናትዋ አባት የዛር ወይም የጅን ንጉሥ ነበረ ሲሉ ከንቱ የሐሰት ተረትን ይጫወታሉ።

እኛም በኢትዮጵያ ንግሥተ ማከዳን ስምዋን ለውጠው በልቂስ ወይም በልቂሳ ብለው በየመን የተወለደች የየመን ንግሥት ብቻ ናት ብለው በቁርዓንና በየመን ታሪክ የተጻፈውን ሐሰት በእውነት ታሪክምሳር ቆርጠን እንጥላለን። በቁርዓንና በየመን ታሪክ ስለ ንግሥት ማከዳ እንዴት ያለ ሐሰትና ተረት ተጽፏል የሚል ሰው ቢኖር በቁርዓና በየመን ታሪክ ስለ ማከዳ ወይም ስለ ንግሥተ ዓዜብ ስምዋን በልቂስ ያሏት የተጻፈ ታሪክ ፍጹም ተረት የሆነ ፲፫ ሐሰት አለበት።

መጀመርያ ሐሰት የእመቤታችንን የእግዝትእነ ማርያምን አባት ኢልያቄምን ስሙን ለውጠው ማርያም የአምራን ልጅ የሙሴና የአሮን እህት ናት እንዳለ (ዘፀ፤ ፲፤ ፳፣ ፩ዜና ፮፣ ፫) እንዲሁም የንግሥት ማከዳን አባት የዋትስያን ስም ለውጦ የንግሥትን ባለመዋል ሶርሀቢል የምትባለውን ወይዘሮ ስምዋን ወሰደ ጥቂት ዘወር አድርጎ በሰ ሸን አግብቶ ሸርሀቢል አለው።

ሁለተኛ ሐሰት ንግሥት ማከዳን ስምዋን ለውጦ በልቂስ ወይም በልቂሳ አላት።

ሦስተኛ ሐሰት እርስዋም በኢትዮጵያ መንግሥትን ካባትዋ ከተዋስያ ወርሳ ከኢዮጵያ እስከ የመን ከዚያም አልፋ እስከ ማዳጋስካር የገዛቸውን ንግሥት የየመን ንግሥት ብቻ ናት አላት።

የኢትዮጵያ ንግሥት ሆና ማከዳ እስከ የመን ከዚያም አልፋ እስከ ማዳጋስካር እንደ ገዛች ምን ምስክር አለ የሚል ሰው ቢኖር።

ምላሽ ጀምስ ብሩስ የሚባል የእንግሊዝ አገር ሰው በታሪክ መጽሓፉ በ፩ኛው ክፍል በገጽ ፺፭ ስለዚች ንግሥት ሲናገር፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌል እንዲያው ባጭር ቃል ንግሥተ ዓዜብ ብሎ አነሣት፤ የመጣችውም ከዓለም ዳርቻ ነው ይላል። (ማቴ. ፲፪ ፵፪) ግዛትዋ የታወቀ አንድ ክፍል ከአፍሪቃ እስከ ማዳጋስካር ድረስ ነው። ዛሬ ዘመን ሳፍላ እንለዋለን። ይህች ንግሥት የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ኢየሩሳሌም ልትሄድ በተነሳች ጊዜ ሐበሾች፣ በርበር፣ አሕዛብ ያረቦች የሙር ሰዎች ተከተሏት። በዙርያዋ ያለ አገር እርስዋን የማያመሰግን አልነበረም ይባላል። ከዚህ የቀረን በክብረ ነገሥት ገጽ ፬የ፯፩ እይ።

ሞሪያ የፈረንሣዊ ሊቅም ንግሥት ማከዳ በእውነት የኢትዮጵያ ንግሥት እንደ ሆነች ሲያስረዳ ንግሥት ማከዳ በዚች በአክሱም አጠገብ ሳባ ከተማ ተቀበረች። በመቃብሩዋ ፳፬ ሐውልቶች አሉበት። አሁን ግን ተሰባብረዋል ይላል። ስለ ኢትዮጵያ በጻፈው ታሪክ በሁለተኛ መጽሐፉ ፹፬ እና ፹፭ እይ። ዳግመኛም ክብረ ነገሥት ፬የ፹፬ ገጽ ተመልከት።

ዳግመኛም ጀምስ ብሩስ የኢትዮጵያን ታሪክ በጻፈበት መጽሐፉ በ፩ኛው ክፍል ገጽ ፺፫ የሰሎሞንን ጥበብና ሥራውን ሰምታ በኢየሩሳሌም በአይሁድ ሃይማኖት ተጠመቀች። ልጅም ወለደችለት። ስሙንም ምኒልክ ተባለ ይላል። ክብረ ነገሥት ፬የ፰ ተመልከት።

፬ኛ ሐሰት የበልቂሳ የእናትዋ እናት የዛር ወይም የጅን ንጉሥ ናት የናትዋ አባትም የዓረብ ንጉሥ ነው ያለው ሐሰት ነው። የናትዋ ስም በክብረ ነገሥት የታወቀች ኤስሜን ንግሥት የተባለች ናት። እርስዋ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የተዋስያ ምሽት ናት። ክብረ ነገሥት ገጽ ፬፻፴ እይ።

፭ኛ ሐሰት የበልቂሳ የእናትዋ እናት የዛር ወይም የጅን ንጉሥ ልጅ የዓረብ ንጉሥ አደን በሄደ ጊዜ ነጭ ቡሆር ወይም ሌላ የምታምር ነጭ እንስሳ ሆና ታየችው አለ።

፮ኛ ሐሰት ይች የምታምር ነጭ እንስሳ የሆነች የዛር ንጉሥ ልጅ በእንስሳ ተመስላ በታየችው ጊዜ ቢሆን እይዛታለሁ፤ አልያዘኝ ብትልም እንገላታለሁ ብሎ የዓረብ ንጉሥ ለገቻ ገብቶ ፈረሱን በኃይል አስነሥቶ እየጋለበ ሲቀርባት ሩጣ እየሸሸች ወደ ኋላ ሲቀር ቁማ እየቆየች አልያዘው አልገደለው ብላ ብዙ አደከመችው። ከሠራዊቱም ተለይቶ እጅግ ሩቅ መንገድ ወሰደችው። ከዚህ በኋላ ይችው በነጭ እንስሳ የተመሰለች የዛር ንጉሥ ልጅ በደረሰባት ጊዜ ልብስ መንግሥት ለብሳ የምታምር ሴት ወይዘሮ ሆና ታየችው ይላል።

፯ኛ ሐሰት በዚህ ነገር ደንግጦ ሳለ ሜዳው ሁሉ የዛር ንጉሥ ቁም ሰፍሮበት፤ ድንኳን በድንኳኑ ተቆላልፎበት፤ ከሠራዊቱ ጋር ሜዳውን ሞልቶት ተገልጦ ታየው አለ።

፰ኛ ሐሰት ወደ ዛር ንጉሥ አባትዋ ይዛው ገባችና አስትዋወቀችው የሁለቱን ፍቅርና መዋደድ አይቶ ጠይቆ ለዓረብ ንጉሥ ምሽት ትሁንህ ብሎ ሰጠውና የበልቂስን እናት ወለደችለት አለ።

፱ኛ ሐሰት ሰሎሞን ከኢየሩሳሌም ወደ የመን ሁድሁድ በሚባል ወፍ ደብዳቤ አስይዞ ወደ በልቂስ ላከውና አደረሰላት አለ።

፲ኛ ሐሰት ሰሎሞን ለበልቂስ ብዙ ታምራት አሳያት ከብዙው አንዱ ንግድ ያለ መሮ በወፍ አስነድሎ አሳያት አለ።

፲፩ኛ ሐሰት በልቂስ ንግሥት ኢየሩሳሌም ሄዳ ከቤተ መንግሥት አጠገብ በደረሰች ጊዜ እሱዋ ገና ሳትገባ አስቀድሞ የሷን ባገርዋ ከቤቷ ያለውን አልጋዋን ለእሷ መቀመጫ እንዲሆን አሁን ማን ያመጣልኛል ቢል ለሰሎሞን አጋንንት ይታዘዙለት ነበርና የአጋንንት አለቃ እኔ እስተ እኩል ቀን አመጣዋለሁ አለ።

፲፪ኛ ሐሰት ከዚህ የባሰ መጉመድ ይህማ ምን ይሆናል ላሁን እሷ ሳትገባ ነበር እንጂ ቢል፤ አንድ የመጽሐፍ እውቀት ያለው ሰው ነበረና ዓይንህን ከድነህ እስክትከፍተው፤ እኔ አሁን በቅጽበት ዓይን አመጣዋለሁ ብሎ ወዲያው አመጣውና የጠራ ውሃ ባሕር መስሎ እየተብረቀረቀ በተቀመጠበት ስፍራ ላይ ዘረጋው።

፲፫ኛ ሐሰት በልቂስ ንግሥት በገባች ጊዜ ይህን አልጋዋን አይታ ባሕር መስሎዋት ልብስዋ እንዳይነከርባት ልብስዋን ስብስብ አድርጋ ያዘች አለ።

ይህም በዚያ ከቁርዓንና ከየመን ታሪክ ከተጻፈ የሐሰቱ የውዳሴ ከንቱ የተረቱም ሁሉ ፍጻሜና ማሕተም ነው። እንኳን ያልሆነውን ቢሆንስ በቤትዋ ያኖረችው ባሕሪውን ሥፍራውን ያወቀችውና የለመደችውንን የምትቀመጥበትን የምትተኛበትን የገዛ አልጋዋን ጠፋትና ውሃ መስሎዋት ሰበሰበች ማለት ፍጹም ሐሰትና ተረት የልጆች ጨዋታ ነው። ቢጠናስ አልጋዋን ካላሰበችውና ካልጠረጠረችው በዚያ ስታየው፤ ይህ አልጋ በኔ አልጋ ምሳሌ የተሠራ ነው ብላ ትደነቃለች አንጂ አልጋዋን የማታውቀው ይመስል ውሃ ነው ብላ ልብስዋን ሰብሰበች ማለት ሰነፎችን አእምሮ የጎደላቸውን እውቀት የሌላችውን ለማስደነቅና ለማስገረም የተጻፈ ከንቱ ተረት ነው።

ይህንንም የመሰለ ከንቱ የባልቴት ተረት፤ ፉርቃን ወይም ቁርዓን በሚሉት በእስላሞች ዋና መጽሐፍ ተጽፎ ይገኛል። የእስላሞች ነገር ከውነት ይልቅ ሐሰትን ከቁም ነገር ይልቅ ተረትን ይወዳሉና ከወንጌል እውነት ይልቅ የቁርዓንን ሐሰትና ተረት ለማድመጥ ጆሯቸውን ይመልሳሉ። በነሳቸውም የቅዱስ ጳውሎስ ቃል ይፈጸምባቸዋል። እንዲህ የሚል እውነትን ከመስማት ወደ ተረት ይመለሳሉ ፪ ጢሞ ፬ ፫።

የቁርዓንና የየመን ታሪክ በአምልኮት በሃይማኖት በንግሥተ ዓዜብ በሌላም ታሪክ ሁሉ የተጻፈውና የሚመኩበት ፍሬ ይህ ነው።

ከኤውሮጳ ሰዎችም አያሌዎች ከዚህ ፍሬ የተቀዳን ይዘው ንግሥተ ዓዜብ የየመን ንግሥት ናት ሳባ የሚባል በኢትዮጵያ የለምና የኢትዮጵያ ንግሥት አይደለችም ብለው ታሪካቸውን ጽፈው እስከ ዛሬ የየመን ሳባ ንግሥት መሆንዋን ያምናሉ። የኢትዮጵያ ንግሥት መሆንዋን ፈጽመው ይጠራጠራሉና ይክዳሉ።

አንዳንዶች ግን እንደ ጀምስ ብሩስ የእንግሊዝ ሊቅ እንደ ሞሪየ የፈረንሳዊ ሊቅ እንደ ኦሚሮስ እንደ ሔሮዶቱስ ያሉ የግሪክ አገር ሊቃውንት እንደ መልዚ እንደ አኬሊ ዜዘኒ ያሉ የኢጣልያ ሊቃውንት እነርሳቸውንም የመሰሉ ብዙዎች የውኤሮጳ የእስያ ታሪክ በጣም መርማሪዎች የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሴም ዘር እንደሆኑ፤ ንግሥተ ዓዜብ ወይም የሳባ ንግሥት የተባለችው ከተማዋ በትግሬ ሳባ ይባል እንደ ነበረ መርምረው አውቀው የኢትዮጵያ ንግሥት መሆንዋን ከኢትዮጵያ እስከ የመን ከዚያም አልፎ እስከ ማዳጋስካር መግዛትዋን በታሪካቸው ጽፈዋል።

ከዚህም ጋር አስተዋይ ልቡና አደላዳይ ኅሊና ያለው ሰው ስለ ንግሥተ ዓዜብ በቁርዓንና በየመን ታሪክ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ፍጹም ተረት እንደሆነ የኢትዮጵያ ታሪክ ግን እውነተኛ እንደሆነ ፈጽሞ ይረዳዋል።

የሳባ ንግሥት የተባለች የኢትዮጵያ ንግሥት ማከዳ በትግሬ ያለ በአክሱም አጠገብ ቀድሞ በዚያ ዘመን ስባአ ከምትባል ከተማዋ ተነሥታ ኢየሩሳሌም ሄዳ ቀዳማዊ ምኒልክን ወለደች። በእርግጥም የኢትዮጵያ ንግሥት ናት እንጂ የየመን ንግሥት ብቻ አይደለችም። የእርስዋንና የልጅዋን ታሪክ በሞላው ለማየት የሚሻና እውነቱን ሊረዳ የሚወድ በክብረ ነገሥት ገጽ ፬፻፴፩፤ ፮፻፲፪ በየክፍሉ እያወጣ ያንብብና ልብ አድርጎ ይመልከት። ስለ ንግሥት ማከዳና ስለ ቀዳማዊ ምኒልክ ከሚነገር ታሪክ ከረጅም ባጭሩ ከብዙ በጥቂቱ ይህ ይበቃናል። ከዚህ ቀጥለን የነገደ አገውን ታሪክ እንጽፋለን።

# ፲ ነገደ አገው

ነገደ አገው በፊት ነገደ አዲል ይባሉ ነበሩ። አዲል የዳዊት የልጁ ልጁ የይትረሃም ልጅ ነው ይላሉ። ፪ ዜና መ፫ ፫ እሱ ከነሥራዊቱ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋራ መጣ ቀዳማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ሲባል ከእርሱ በታች አገው የላስታ የገነት ዛሬ የጁ የተባለው በዙርያው ላለው አገር ሁሉ ንጉሥ ነበር። የዳዊት የልጁ ልጅ የአምኖን ልጅ ኖን የሚባል ነበር። እርሱም ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋራ መጥቶ ከእርሱ እብታች ከቋራ እስከ መተማ በታች አገር ንጉሥ ነበር ይላሉ። ከተማውን በቋራ አደረገ። አገሪቱንም ቋራ ብሎ ጠራት። በቋራ የሚኖር የእርሱ ዘሮች በኖን ልጅ በሔት ስም ነገደ ሔት ተባሉ። ቋንቋቸውንም ጥንት ልዩ ነበር። አሁን ግን ቋንቋቸውን አጥፍተው በአማራ ቋንቋ ይናገራሉ። በጥንት ቋንቋቸው ኳራ ወይም ቋራ ማለት ፀሐይ ማለት ነው ይላሉ። በቋንቋቸውም ከአገዎች ጋራ ይቃረቡ ነበሩ ይባላል።

አገዎች ግን ከ፫ ተከፍለው ቋንቋቸውም ስሩ አንድ ሲሆን በየክፍላችውና በየአገራቸው ጥቂት ጥቂት ልዩነት ያለው ሆነ። እርሳቸውን በ፫ አገር ስም ይጠራሉ። የላስታ አገው፣ የዳሞት አገው፣ እና የሐሉል በጎስ አገው ይባላሉ። የሁሉ መሠረትና ምንጭ የላስታ አገው ነው።

የዳሞት አገዎች ከላስታ አገው ፯ የሆነ ዝሆንና ጎሽ አደን ብለው ሂዱ። ከዚያ ሰው እንደሌለበት ጠፍ እንደሆነ ተመልከተው ያገሪቱንም ደግነት አይተው በየዳሩ በየዛፉ እጅግ ንብ የበዛበት ብዙ ማር የሚገኝበት አገር ነውና ማርና የዱር እንስሳ ሥጋ ድነው

እየበሉ ፯ ወር አገሪቱን ደህና አድርገው ዞሩና መረመሩ። ከዚህ በኋላ ምሽቶቻቸውንና ልጆቻቸውን ላማቸውን ፍየላቸውን ጓዛቸውን ሁሉ አምጥተው በዚያች አገር ተቀመጡባትና አቀኑዋት። ባላገሮች ባላባቶችም ሆኑባት። አገሩም አገው ምድር ተባለ። በ፯ቱ አባቶችም በየክፍሉ ሲዘረዘር ፯ ቤት አገው ይባላል። በ፯ቱ አባቶቻችው ስም አገራቸውን ሰይመው ፯ ቤት አገው ተብለው በየአገራቸው በየክፍላቸው ይጠራሉ።

የሀልሀል በጎስ አገዎች ግን በአንድ ዘመን በያገሩ ርሃብ በሆነ ጊዜ እንዲሁ በላስታ አገው ፯ ወንድማማች አገዎች ከነሚሽቶታቸውና ከነልጆቻቸው፤ ፯ እህቶታቸውም ከነባሎቻቸው፤ ተሰደው ሀልሀል በጎስ ግቡ። በዚያም ዱሩን መንጥረው፤ እባቡን ገድለው፤ ቤት ሠርተው፤ አገር አቅንተው፤ ተቀመጡ ይባላል።

የላስታ አገዎች በዋግ የሚኖሩ ዋኖች እነርሳቸው ናቸው። በቀዳማዊ ምኒልክ ጊዜ የያዙትን አገር አለቀቁም። እስከዛሬም አልተነቃነቁም። ስለ አገዎች ከሚነገር ታሪክ ከዚህ የቀረን በክብረ ነገስት ከገጽ ፻፹፱ - ፻፺፩ በገጽ ፪፻፬ ከተጻፈው ጋራ አስተያየተህ ተመልከት። ስለ ነገደ አገው ከሚነገር ታሪክ ከረጅም ባጭሩ ከብዙ በጥቂቱ ይህ ይበቃል። ከዚህ ቀጥለን የነገደ አስማክህን ነገር ታሪክ እንጽፋለን።

## ፲፩ ነገደ አስማክህ

ነገደ አስማክህ በ፬ሺ ፳፻፸፫ ዓመተ ዓለም በ፮፻፷፪ ዓመት ከልደት በፊት ከጥሳሜቲክ ፯ኛ ፈርዖን ከምስር ንጉሥ ተጣልተው ፱፻፵ሺ ሠራዊት ከምስር ንጉሥ ከድተው ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ለዊያንኪሂ ፬ኛ ለኢትዮጵያ ንጉሥ ገቡ። እርሱም በናዋታን ስላእ ያላሰባቸውን ረዳቶች በድንገት ስለ አገኘ በታላቅ ደስታ ተቀበላቸው። ከድስታውም ብዛት የተነሳ ፈጥኖ ደስ የሚያሰኝ አገር ሰጣቸው። ለእሱም ጠላቶቹ ይዘውት የነበሩትን አሎ በምዕራብ የነበረውን አገር እንዲያቀኑለት ፈቀደላቸው። ያለ ጥርጥር በዚህ አገር ውስጥ ያለ ሕዝብ በአክሱም መንግሥት ብዙ መንበሩን ትቶ ነበረና ነገደ አስማክህ እንዲህ ሆነው በኢትዮጵያ ቀሩ። በፊት በሰናሒት ነበሩ። በኋላ ግን ነጭ አባይና ጥቁር አባይ የሚገናኑበት ወንዞች መሀል ተቀመጡ። ታላቅ ሕዝብ ሆኑ። የእነሱ ወገን ከ፫፻ ዓመት የሚበልጥ የያዙትን ኤዛር የሚባል ከተማ ሠሩ። ብዙ የምስርን ልማድ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አስተማሩ። አገራቸውም የመጡ የአሎ መንግሥት ዛሬ ሴዩክ ለሚባሉት አለፈ። በአስትራቦን ዘመን አንዲት መንግሥት ነበረች። በጵሊን ጊዜያት ያቆሙት መንግሥት ግን እንዳልነበረ ሆነ።

ይህም የ፻፸፯ሺ ሠራዊት ከዳት ያገሩ ዋና ሠራዊት ነበርና ለምስር መንግሥት እጅግ አጥብቆ ጎዳውና አደከመው። የውጭ ሰዎች በዘመቱበት ጊዜ ሊቃወም አልተቻለውም። የፋርስ ሰዎችም ምስርን በዘንግ ሊገዙት ሆነ። የምስር ፈርዖኖችም በየዘመናቸው ነገደ አስማኪህን ፭ኛ ከሄደበት አሳብ አልተሻለም። የነገደ አስማኪህ ታሪክ ብዙ ነው። ከምስር ምድር ተጣልተው ወደ ኢትዮጵያ ንጉሥ የገቡበትን ምክንያት ሙሉ ታሪኩን ልትሰማ ብትወድ በክብረ ነገሥት ገጽ ፻፺፪ - ፻፺፫ ደግሞ ፮፻፸፩ ተመልከት።

# ፲፪ ነገደ ፈላሻ

ስለ ነገደ ፈላሻ የሚነገር አንድ አንዱን እውነት ያልሆነ ሁለቱ የታመነ ፬ ታሪክ አለ። አንድ ውነት ያልሆነ ያልነው፤ ሞሪያ በመጀመርያ መጽሐፉ ስለ ካም ልጆች ታሪክ ሲናገር የኩስ ወይም የኩሽ ልጅ ረሁም ሁለተኛ ስሙ ሮሙስ የተባለ ሁለት ልጆች ወለደ። እነርሳቸውም ዩዳና ሳቢውስ ናቸው። ዮዳ በኢትዮጵያ ያሉ ፈላሾች አባት ነው ብሎ ፈላሾችን የካም የልጅ ልጆች አድርጎ ዩዳ የሚባል አባት ይሰጣቸዋል። ይህ ግን ላም ያልዋለበት ኩበት ለቀማ፤ ባልተሰረበት ገለባ ሻማ፤ እንደሚሉት ተረት ከንቱ ጨዋታ ነው እንጂ እውነት ነገር አይደለምና የማይታመን እውነት ያልሆነ ነገር ያልነው ስለዚህ ነው።

ስለ ፈላሾች ነገር ታሪክ ፫ የታመነ ነው ያልነው እንዲህ ነው፤ በኢትዮጵያ ያሉ ፈላሻ ሕዝብ ሥራቸውና ምንጫቸው ያለ ጥርጣሬ የእሥራኤል ዘር ናቸው። ከፍልስጥኤም ከእሥራኤል አገር ወደ ኢትዮጵያ የመጡ ግን በየዘመኑ ሦስት ጊዜ ነው።

መጀመርያ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር ከመጡት ከእሥራኤል ሕዝብ አብርወ የመጡ ናቸው። እስከ ዘመነ ወንጌል በአንድ የተቀመጡ ናቸው። በአባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን በወንጌል ቃል አምነው ክርስትና ሊገቡ እነርሳቸው ግን ከወንድድሞቻቸው ከሕዝባቸው ተለይተው በወንጌል ቃል አናምንም አንገባም ሕገ ኦሪትን አንለቅም ብለው የቀሩ የተለዩ ናቸው።

ሁለተኛ አስብያኖስና ጢጦስ የሮም ነገሥታት ኢየሩሳሌም ባፈረሱዋት፤ ቤተ መቅደስ ባቃጠሉት፤ እሥራኤልን በፈጁቸው ጊዜ ከሞት የተረፉ፤ እስራኤል በያገሩ ሲበታተኑ፤ አንድ ክፍል ከፍልስጥኤም ተሰድደው ወደ ኢትዮጵያ ገቡ።

ሦስተኛ በጉዲት ዘመን ከምስር ንጉሥ ሸሽተው ከጉዲት ጋራ ወደ ኢትዮጵያ ገብተው የክርስቲያንን መንግሥት የገለበጡና ያፈረሱ የአክሱምንም ቤተ ክርስቲያን

ያቃጠሉና ክርስቲያንን ያረከሱ ናቸው። እኒህም የፊተኞች ፈላሾች ከኋለኞች ጋራ ተቀላቅለው ለጉዲት ረድተው መንግሥትን ቢያፈርሱ በክርስቲያን ላይም ግፍ እየሠሩ ሃይማኖተ ወንጌል ቢያረክሱ፤ ጉዲት በሞተች፤ የክርስቲያን ንጉሥ አንበሳ ውድም በነገሠ ጊዜ፤ እኒህን ፈላሾች ፈጃቸውና የክርስቲያን ደም ብድሩን መለሰ።

ከዚህ በኋላ ጥቂት ከሞት የተረፉ በዱር በገደል የነበሩ ፈላሾች ሁሉ ማረን ለእግዚአብሔር ብለህ ይቅር በለን ብለው ድንጋይ እየተሸከሙ ገቡና ቢለምኑት ንጉሡም ነፍሳቸውን ምሬያቸዋለሁ፤ ከርስት ከጉልት ግን ነቅያቸኋለሁ ብሎ ነቀላቸው። በዚህም ከጉልት ተነቅለው ስደተኞች የክርስቲያን ዜጎች ጥገኞች ጢሰኞች ሆነው ኖሩ። ስለዚህም ፈላስያን ተባሉ። ፈላስያን ማለትም ስደተኞች ማለት ነው። በዘመን ብዛት ሲለወጥ ፈላሽ ተባሉ። እኒህ ሕዝብ እስከ አጤ ዓምደ ጽዮን ዘመን ከዚያም ወዲህ እስከ ፫፻፷ ዓመተ ምሕረት እስከ አጤ ሠርጸ ድንግል ዘመን ድረስ ከክርስቲያን መንግሥት እየሸፈቱ ያውኩ ነበሩ። በዚይም ምክንያት ነገሥታት ቀጠቀጧቸውና አደከሟቸው። ያለ ምሕረትም አጠፏቸውና አጠቋቸው። ዛሬ ግን ጥቂት በቀሩ በክርስቲያን ላይ ራሳቸውን የማያቀኑ የተጠቁ ሆኑ። በያገሩ ጥቂት ጥቂት አሉ። የሚበዙ ግን በጭልጋ፣ በጋባ፣ በአርማጭሆ፣ በወልቃይት፣ በጠገዴ፣ በቆላ፣ ወገራ፣ በጎንደር ከተማ ዙርያ ይኖራሉ።

እኒህ ሕዝብ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በመስቀል ከገደሉ የእግዚአብሔር ቁጣ በላያቸው ወርዶባቸዋ ደሙ በኛ በልጆቻችንም ላይ ይሁን ያሉት መርገም ደርሶባቸው፤ በዓለም ሁሉ ሕዝብ የተናቁና የተጠሉ የተዋረዱም ናቸው። ስለዚህም የከበሩ የእግዚአብሔር ሕዝብ በተባሉበት ፈንታ ዓመጸኛ ሕዝብ ተብለው፤ በአሕዛብ ሁሉ ተበትነው፤ በተጠሉ የተዋረዱ ሐፍረት የለበሱ ሆኑ። የነቢዩ ሕዝቅኤል ትንቢት በእነርሳቸው ተፈጸመባቸው። ሕዝ ፳፪ ፩ -፲፫። ፳፬ ፮ -፲፬። ፳፫ ፴፮ - ፵፱። ይህ ሁሉ ውርደትና ሐፍረት የደረሰባቸው ለወንጌል ሃይማኖት ባይታዘዙ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ባይገዙ ነው። ሮሜ ፲ ፲፮ - ፳፩ ኢሳ ፶፫ ፩ -፫። ዮሐ ፲፪ ፲፯ - ፲፯ ፳። ስለ እንገደ ፈላሻ ታሪክ በክብረ ነገሥት በገጽ ፻፺፫ - ፻፺፯ ተመልከት።

ስለ ፈላሻ ሕዝብ ደግሞ በዘመነ አጤ ካሌብ ዙዋኑስ ወይም ፊንሐስ የተባለ አይሁዳዊ አገረ ናግራንን በየመን ክፍል የምትሆን ባጠፋ ጊዜ፤ ቤተ ክርስቲያንን አቃጥሎ ክርስቲያኖችን ገድሎ ባበላሸ ጊዜ፤ አጤ ካሌብ ሄደው ይህን ዙዋኑስ ወይም ፍንሐስ የተባለን አይሁድ ንጉሥ ገድለው፤ ከእሱ ጋራ የተባበሩ አይሁድን ፈጁቸውና የክርስቲያንን ደም መለሱ። ከዚያ ከሞት ያመለጡ አይሁድ ወይም ፈላሾች በባብ አልመንደብ ተሻግረው በኢትዮጵያ ከሚኖሩ ፈላሾች ወንድሞቻቸው ተጨመሩ የሚሉም አሉ። ነገር ግን የክርስቲያን ባለደሞች ሆነው ተጠልተዋልና ደፍረው ወደ

ኢትዮጵያ የመጡ አይመስልም። ስለ ነገደ ፈላሻ የሚነገር ታሪክ ይህ ይበቃናል። ከዚህ ቀጥሎ ስለ ነገደ ጋፋት ታሪክ እንጽፋለን።

# ፲፫ ነገደ ጋፋት

ጋፋት ሁለት ወገን ሁለት ክፍል ናቸው። መጀመርያ የኩሳ ወገን ጋፋት ሁለተኛ የእሥራኤል ወገን ጋፋት ይባሉ ነበሩ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን በአንድ መጋባት በንብረትም ተቀላቀሉና አንድ ጋፋት ተባሉ።

የኩሳ ጋፋት አባት ስሙ ጋፋት የተባለ አንድ ታላቅ ሰው ነበረ። ተካም ልጅ ከኩሳ ዘር ነበር። ነገደ ኩሳ የኢትዮጵያን መንግሥት ለቅቀው አግያዝያን የተባሉ ነገደ ዮቅጣን የኢትዮጵያ አገርና መንግሥት በያዙ ጊዜ፤ ይህ ጋፋት ከነልጆቹ ያዘዛችሁትን ሠርቼ ለእናንተ ተገዝቼ እናኦራለሁ ወደማላውቀው አገር አልሰደድ በለመድሁት ልኑር ብሎ ወደ ነገደ ዮቅጣን ላከ። እነርሳቸውም ያዘዝንህን ሠርተህ ለኛ ተገዝተህ ከኖርህ ምረንሃል ግባ አሉት። እሱም መጥቶ ከነልጆቹ ገባ። ከነልጆቹም ያዘዙትን እየሠራ፤ ለእነርሳቸው የተገዛ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ዜጋ ሆኖ ተቀመጠ።

የእስራኤል ወገን ጋፋት የተባሉ በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን ከእሥራኤል ንጉሥ ከሮብዓም ከሰሎሞን ልጅ ከውንድሙ በክፋት ሸፍተ ተዋጉና ድል ሆነው የሸሹ ቢያገኛቸው እንዳያጠፋቸው ፈርተው ወደ ኢትዮጵያ መጡ። በዳሞት ሰፍረው ጋፋት ተባሉ። ጋፋት ማለት ስደተኞች ማለት ነው።

በፊት እንዳልን እኒህ ሁለት ወገን ጋፋት በመጋባት በግብር በሥርዓት አንድ ሆነው ተቀላቀሉ። በአንድ ስምም ጋፋት ተባሉ። ጋፋቶች ግን ስለ ትውልዳቸው ቢጠይቋቸው ከምን ዘር እንደሆኑ አያውቁምና እኛ አባት ቀዳማዊ ምኒልክ ጽላተ ሙሴን ከኢየሩሳሌም ይዞ የመጣ ጊዜ አብሮ የመጣ ነው። ከጉዞ ላይ ከጠባብ ስፍራ አልፋለሁ ሲል ታቦቲቱን ገፋት ገፋት ገፋት እያሉ ተቆጡ በዚህ ምክንያት አባታችን ስሙ ጋፋት ተባለ ብለው ብቻ ይተርካሉ። የተጻፈ ግን የለም። ይህ ከሆነ የፊተኛው ስሙ ምን ይባል ነበረ ቢሏቸው ምንም የለምና ሊመልሱ አይችሉም። ይህ ተረት የሆነ የአፍ ታሪካችው ግን ፍጹም ጨዋታ ነው እንጂ እውነት ነገር አይደለም። ጋፋት ያማርኛ ቋንቋ ነው። በቀዳማዊ ምኒልክ ጊዜ በአማርኛ ቋንቋ መቼ ይናገሩ ነበሩና ጋፋት ብለው በአማርኛ አፍ ተናገሩት ብለን ለመጠየቅ ግድ ነው። ይህንስ አናውቅም ከማለት በቀር ለዚህ የሚበቃ ሌላ ምላሽ የላቸውም።

ጋፋት ፲ ወንዶች ልጆች ወለደ። ስማቸውም እኒህ ናቸው፤ አብድራይ፤ ገምቦ፣ ቢረባቦ፣ የዘምበል፣ ሱህሊ፣ አሽመን፣ ሀርበዋሽ፣ ሀርብአከል፣ ወንገ እና ድን። እኒህም አስሩ የጋፋት ልጆች በየልጆቻቸው በየወገናቸው ደግሞ በ፲ ነገድ ተከፍለው በውስጥና በየአባቶቻቸው ስም ይጠራሉ። በላይ ግን ነገደ ጋፋት በመባል ባያታቸው ስም በአንድ ተጠቅልለው ይጠራሉ።

የብድራይል ልጆች ነገደ አብድራይ ይባላሉ። ሁሉም እንዲሁ በየአባቶቻቸው ስም ነገደ ገምቦ፣ ነገደ ቦረባቦ፣ ነገደ የዘምበል፣ ነገደ የሱብሊ፣ ነገደ አሽመን፣ ነገደ ሀርበዋሽ፣ ነገደ ሀርብ አከል፣ ነገደ ወንጌ እና ነገድ ድን ይባላሉ ፡

እኒህም ሕዝብ ከብዙ ዘመን በኋላ ቀማኞች ሌቦች ግፈኞች ሆኑ። ስለዚህም ነገሥታት በየዘመናቸው ይዘርፏቸው ያጠፏቸው ነበሩ። ይልቁንም በአጤ ሱስንዮስ ዘመን ይዘርፏቸው ይማርኳቸው ያጠቋቸው እንደ ነበሩ፤ አባ ጢኖ በጻፈው በአጤ ሱስንዮስ ታሪክ ይገኛል።

ነገደ ጋፋት በፊት በሸዋ ይኖሩ ነበሩ። በኋላ ግን ከሸዋ ፈልሰው ጎጃም ተሻገሩ። የሚበዙት ቆላውን ያባይን ዳር ለዳር ይዘው እስከ ድን በዳሞት ይኖራሉ። በሸዋ በበጌምድርም ጥቂት ጥቂት አሉ። ስለዚህም በደብረ ታቦር አጠገብ ሰላምኮ አጠገብ የነበሩት አገር በስማቸው ተጠርቶ እስካሁን ጋፋት ይባላል። በእስቴም መካነ ኢየሱስ አጠገብ ያሉበት አገር በስማቸው ጋፋቶች ይባላል። በሸዋም በደብረ ሊባኖስ በጀር መሀከል በል ጋፋት ይባላል።

ነገደ ጋፋት ጥንት አረማውያን ነበሩ። አሁን ግን ክርስቲያኖች ናቸው። በአማራ ሕዝብ መሀከል ስለ ተቀመጡ፤ ቋንቋቸውን አጥፍተው፤ በአማርኛ ቋንቋ ይናገራሉ። አንዳንዶች የጥንት ቋንቋቸውን ያልረሱ እርስ በእርሳቸው የምስጢር ነገር ሲነጋገሩ በጥንት ቋንቋቸው ይነጋገራሉ። እንደ ዋና ቋንቋ ግን አይነጋገሩበትም። ቋንቋቸው ጠፍቶ አማርኛ አሸንፏቸዋልና አማርኛ ብቻ ይናገራሉ።

ዛሬ ክርስቲያን ሆነው በክርስቲያን መሀከል ሲኖሩ ሥራቸው ሸማ፣ ብረት፣ ቆርበት፣ መሰንቆ፣ መምታት፣ አዝማሮች፣ ሀማናወችም ሌላም የጅ ሥራ የሚያቁ ሠራተኞች ዋኖች በዚሁ በሥራቸው የታወቁና የተለዩ ከጋፋትና ከፈላሻ ዘር ናቸው። እኒህም ምን ክርስቲያን ቢሆኑ እርስ በርሳቸው ይጋባሉ እንጂ ጨዋ ከሚባል ክርስቲያን እስከ ዛሬ የሚያጋባቸው የለም።

ስለ ነገደ ጋፍት ታሪክ በአጤ ሱስንዮስ ታሪክ አባ ጢኖ በጻፈው ከምዕራፍ ፳ እስከ ምዕራፍ ፲፩ ብዙ ይገኛልና በዚያ ተመልከት። ስለ ነገደ ጋፋት ከሚናገር ከረጅም ባጭሩ ከብዙ በጥቂቱ ይህ ይበቃናል። ከዚህ ቀጥለን የነገደ ኦሮሞን ታሪክ እንጽፋለን።

# ፲፬ ነገደ ኦሮሞ

ስለ ነገደ ኦሮሞ የሚነገር ቁም ነገርና ሐሰት እውነትና ተረት የሆነ በየዓይነቱ ብዙ ልዩ ልዩ ታሪክ አለ።

አቶ አጽሜ በጻፉት የታሪክ መፅሐፍ ስለ ኦሮሞ ሲናገር እንዲህ ይላል፣ ኦሮሞ የሚሉት ሕዝብ ካገሩ የወጣበት ምክንያት እጅግ አይታወቅም። ባለ ታሪኮች እኒህ ኦሮሞ ሕዝብ ከእስያ ፈልሰው ወደ ማዳጋስካር እንደ ተሻገሩ ከዚያም ፈልሰው ቦባሳ አጠገብ ከባሕር ወደብ ተቀመጡ። ቦባሳ ማለት በኦሮምኛ ለሰውም ለከብትም መሰማሪያ ማለት ነው። ከዚያም ገናሌ የሚባለውን ወንዝ ተከትለው ወደ ኢትዮጵያ ወጡ ይላሉ። ካገራቸው ሲወጡ ግን ሁሉ በአንድ ጊዜ አልወጡም። የወደደ ወጣ ያልወደደ ቀረ እንጂ።

ይህ ኦሮሞ የተባለ ሕዝብ ከዚያ ተነሥቶ መጣና በባሌ ዳር ገላና በሚሉት ወንዝ ተቀመጠ። ላሙንና ፍየሉን በጉን እያረባ እንደ ዘላን ሆኖ ኖረ። ከመጣም ከአጤ ልብነ ድንግል ስመ መንግሥታቸው ወናግ ሰገድ ከእርሳቸው መንግሥት በፊት ፻፪ ዓመት ሆኖት ነበር። ይህም አጤ ይስሐቅ በነገሡ በ፳ ዓመት በ፮ሺ፱፻፬ ዓመተ ዓለም በ፲፬፻፬ ዓመተ ምሕረት ነው የሚሉ። እውነተኛው የኦሮሞዎች ወደ ኢትዮጵያ መውጣት ግን መራ ተክለ ሃይማኖት ስመ መንግሥቱ ዛጓ በነገሠ በ፲ ዓመት በ፱፻፴ ዓመተ ምሕረት ነው።

ፈረንጆች ስለ ኦሮሞ የጻፉት በራስ እውቀትና በምርምር ነው። እኛ ግን ካገሩ ውስጥ የሚገኘውን አዛዥ ጢኖ የጻፈውን ታሪክ አይተን ነው።

ኦሮሞዎች ሲመጡ በገላኔ ወንዝ መጥተው ሆር ውላቦ በሚባል አገር ገቡ። በሆር ውላቦ ዋናተኛ በዋና የሚቆርጣትና የሚሻገራት ትንሽ ኩሬ ባሕር አላት። ኦሮሞዎች አባታችና ፍጥረታችን ከዚህ ወጣን ይላሉ። ስለዚህም ኡሜን ውላቦ ይላሉ። ይህም ከውላቦ ውሃ ወይም ባሕር ፍጥረት ወታ ማለት ነው። ስለዚህ ኦሮሞዎች ለውሃ ይሰግዳሉ። ሰውም እንስሳም ከዝያች ውሃ አጠጣም ክልክል ነው። ኦሮሞ ሁሉ ከዚያ ለውሃዶቱ ይሰግዳል። ከዚያ ብዙ ሰንጋ ፍሪዳ በግ ፍየልም ያርዳሉ። በሆር ውላቦ ልዩ

ቋንቋ ያላቸው ጥቂት ሕዝብ አሉ። ደራስ ይባላሉ። የኦሮሞ ሕዝብ ይመስላሉ። ከሲዳሞ እስከ ውላቡ ፬ ቀን ከውላቦ እስከ ቦረን ፳ ቀን ያስኬዳል።

ስለ ኦሮሞ ትውልድ የኦሮሞ ትውልድ እንዲህ ነው። ኦሮሞዎች ሁለት ነገድ ናቸው። በርቱማ እና ቦረን ይባላሉ። ወንድማማች ናቸው። በርቱማ ፯ ቦረን ፲፩፤ ሁለቱ ወንድማማች ፲፰ ልጆች ወለዱ። የበርቱማ ልጆች እኒህ ናቸው፤ ከረዩ፣ መረዋ፣ ኢቱ፣ አከቹ፣ ወረነሽ ሁበና ናቸው። የከረዩ ልጆች ስምንት ናቸው። ሊበን ሜጫ ትሉማ፣ ወሎም ጅሌ፣ አቦ፣ ሉባ፣ በላአ። የመረዋ ልጆች ፬ ናቸው ወርድያን፣ አሩሲ፣ ኢቱ፣ ጥሙጋ፣ ናችወ። ወርድያን ፫ ይወልዳል እና፣ ኡር አበጢ እኒህ ሁሉ የመረዋ ልጆች በኃይልና በብዛት ከሁሉ ይበልጣሉ። የኢቱ ልጆች ፪ ናቸው። ጅሌ እና ሱባ። የአከቹ ልጆች ፪ ናቸው። ጅንጉር እና ጬፋ የወረነሻ ልጆች ፰ ናችው ሶዶ፣ አቡ፣ ጫቡ፣ ይሉ፣ ጉድሩ፣ ኩታይ፣ አምሩ፣ ሁሮ፣ ናቸው። የሁበና ልጆች ፫ ናቸው ራያ፣ አዘቦ እና ሀሸንጌ ናቸው። ከነዚህ የሜጫ ልጆች ከኦሮሞ ቤት ሜጫ ከታላልቆች ተነስተው በኢትዮጵያ ንጉሥ የጌታ አደሩ። ንጉሡም አጤ ዓምደ ጽዮን ነው። እሩም በመልካም ተቀብሎ በጣና ባሕርና በዳሞት መሀከል አገር ሰጣቸው። እነርሳቸው ያን አገር ተቀብለው ያዙና ስሙን ባባታቸው ስም ሜጫ አሉት። ከዚህ በኋላ ክርስትና ተነስተው አብያተ ክርስቲያናትን በተቀሉት አገር ሁሉ ሠርተው ክርስቲያኖች ሆነው ተቀመጡ። በአማራ ሕዝብ መሀከል ኦሮምኛን ፈጽመው አጥፍተው በአማርኛ ቋንቋ ብቻ ይናገራሉ።

የወሎ ልጆችም የያዙት አገር በአማራ ሕዝብ መካከል ስለሆነ ኦሮምኛን አጥፍተው በአማርኛ ቋንቋ ይናገራሉ። ጥንት ክርስቲያን ሆነው ብዙ አብያተ ክርስቲያናት

የከበሩ አድባራት አትሮንስ ማርያም፣ መካነ ሥላሴ፣ ደብረ ገንት፣ ገነተ ጊዮርጊስ እኒህን የመሳሰሉ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ነበሩባቸው። አገሩ ጥንት ላኮ መልዛ ይባል ነበር። በኋላ የወሎ ልጆች ከያዙት ግን ያገሩን ስም ለውጠው ባባታቸው ስም ወሎ አሉት። ግራኝ ባገራቸው ውስጥ የነበሩ አብያተ ክርስቲያኖችን አጥፍቶ አቃጥሎ መጻሕፍትን ቆነጻጽሎ ባጠፋባቸው የሐረርጌ እስላሞና ፋቅሮች ገብተው የመሐመድን ሃይማኖት በቁርዓን ባስተማራቸው ጊዜ የወሎን ሰዎች ፈጽመው አሰለሙ። አሁን አጤ ዮሐንስ ባዋጅ በግድም ክርስትና ቢያነሱት ካንዳንድ ጥቂቶች በቀር የቀረው የወሎ ሕዝብ በሜዳ ክርስቲያን ቢመስል በውስጥ ግን ምንም እስልምናን አልተወውም ነበር። ስለዚህ አጤ ዮሐንስ ከሞቱ ወዲህ ካንዳንዶች በቀር በክርስትናው የጸና የለም። ሁሉም ፈጽሞ በግልጥ እስላምነቱ ተመለሰ።

ከሁበና ልጆችም ከራያና ካዘቦ ተለይቶ ሀሸንጌ የትግሬ ጎረቤት ስለሆነ የሚበልቱት ክርስትና ተነስተዋል። በስም ክርስቲያኖች ይባላሉ። የሚያንሱት እስላሞች ናቸው።

በስም እስላሞች ይባላሉ። በግብራቸው ግን ክርስቲያኖች እላሞች የሚባሉትም ነፍስ በመግደል ደም በማፍሰስ ፍጹም እንደ ራያና እንድ አዘቦ ኦሮሞዎች ናቸ። የሀሽንጌ ኦሮሞዎች ኦሮምኛን አጥፍተው ትግሪኛ ቋንቋ ይናገራሉ። ከመካከላቸው ጥቂቶቹ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ክርስቲያኖች ይገኛሉ። የቀሩት ግን በስም ክርስቲያኖች ስባሉ ግብራቸው ሁሉ የአረማውያን ሥራ ነው።

# ፲፫ የቦረን ልጆች

ደጨ፣ ጅሌ፣ ከኖ፣ በቸ እነኒህ ቱሉማ ይባላሉ። አካኮ ወቦ ሉባ እነኒህ ሰደቻ ይባላሉ። ጭሌ ሊበን ጉድሩ ሆኮ እነኒህ ሆኮ ይባላሉ። እነኒህ ፲፬ዱ የቦረን ልጆች ፳ ልጆች ወለዱ። የደጨ ልጆች ፪፣ የጅሌ ፪፣ የኮኖ ፫፣ የበቸ የ፪፣ አካኮ ፪፣ የወቦ ፪፣ የጭሌ ፪፣ የሎባ ፪፣ የሊበን ፩፣ የጉድሮ ፩፣ የሆኮ ፩፣ ሁሉም በድምሩ ፳ ይሆናሉ።

ስማቸውም እነኒህ ናቸው። የደጨ ልጆች ፪ ሌቃ እና ጨለባ የጅሌ ልጆች ፪ ወለጋ እና ጉማ። የኮና ልጆች ፫ ሉሙ ጅማ እና ጌራ። የበች ልጆች ፪ አብቹ እና ግምብቹ። ያካኮ ልጆች ፪ ወበሪ እና ገላን። የወቦ ልጆች ፪ ሎሜ እና ሊበን። የሉባ ልጆች ፪ መኢታ እና ዋዩ። የጭሌ ልጆች ፪ ጉለሌ እና ሰላሌ። የሊበን ልጅ ፩ አብቲ። የጉድሩ ልጅ ፩ ደራ። የሆኮ ልጅ ፩ ቦረና። እነኒህ የበርቱማ ፳፯ የቦረን ፳ ድምሩ ፵፯ ዋኖች የገላ አባቶች ናቸው።

እነኒህም በጥቂት ተራቡና እጅግ ብዙ። ከብዛታቸውም የተነሳ እየገፉ ክርስቲያኑን እያጠፉና እያቃጠሉ የክርስቲያን አገር ሁሉ በኢትዮጵያ ወረሱ። በኢትዮጵያ ያ ሁሉ ጉዳትና ጥፋት የሆነ በነገሥታት ቸልተኝነት በመኳንንቱ ትዕቢትና እርስ በርሳቸው ፍቅር በማጣት፤ በሕዝቡም እርስ በርሱ ባለመስማማት በመለያየት፤ መንግሥት ቢደክም፤ አገርም እርስ በርሱ በሁከት ተበላሽቶ አንድነትና መስማማት ብርቱ ኃይል የሚሆን ቢጠፋ ነው።

ዛሬ ኦሮሞ በያዘው አገር ውስጥ ጥንት የክርስቲያን አገር አንደ ነበረ በግልጥ የሚያስረዳ ከሐረር እስከ ባላያ ቦረና ከከፋ እስከ ራያና አዘቦ ባለው ኦሮሞ በያዘው አገር ሁሉ የመንግሥት ቤት፤ የኖራ ግምብ ፍራሽ፤ ከተማ የነበሩ የከበሩ አብያተ ክርስቲያናት፣ የንዋየ ቅድሳት የጻሕል፤ የዓውድ፣ የመስቀል የአክሊል፤ የመቋሚያ የጽናጽል ስባሪና ሌላም ሁሉ ደኅና ተፍራሽ ውስጥ ተቀብሮ የኖረው አፈር በልቶት አሁን በዘመናችን በዳግማዊ ምኒልክ ጊዜ እየተቆፈረ በብዙ ሥፍራ ወጣ። ደግሞ በየዋሻው ኦሮሞ ሲዘርፋቸው ሸሽገው ያኖሩት ብዙ የቤተ ክርስቲያን አልባሳት ከብዙ ዘመን መኖር ብል

ብልቶት የሴት ወፍ ቀዳዶት ንዋየ ቅድሳት መጻሕፍትም እስከ ዛሬ እየተመረመረ ይገኛል።

ስለ ኦሮሞ ታሪክ በእውነትም በሐሰት ተረት የተጻፈ ብዙ ነውና በሙሉ ታሪኩን ልትመረምርና ልታውቅ ብትወድ በክብረ ነገሥት ተጽፎአልና ከገጽ የ፫፱ - ፪የ፵፫ ልብ አድርገህ ተመልከት።

ስለ ኦሮሞ ከሚነገር ታሪክ ከረጅም ባጭሩ ከብዙ በጥቂቱ ይህ ይበቃልና። ከዚህ ቀጥለን የእናሪያን ሕዝብ ታሪክ እንጽፋለን።

# ፲፯ ነገደ እናሪያ

የእናሪያ ሕዝብ ሁሉ የካም ዘር ነው። ነገደ ዮቅጣን መጥተው የነገደ ኩሳን መግንሥት በወሰዱ ሕዝቡንም በጦር አጥፍተው የተረፈውን ባሳደዱ ጊዜ በኢትዮጵያ ደቡብ ዳር ለዳር በወላይታ በሲዳሞ በኩል በኮንታ፣ በአማሮ በዣንጀሮ የሚኖር ሕዝብ ነው። እርሱም ከጦር በኋላ ከነገደ ዮቅጣን ገብቶ ለነእርሳቸው እጅ ነሥቶ ተገዝቶ ታዝዞ ገብሮ የሚኖር ነው። ቀድሞ ኦሮሞዎች ሳዪዙት ሉቅማ፣ ጅማ፣ ሌቃ፣ ትቤ እና ከፋ ይህ ሁሉ የእናሪያ ሕዝብ አገር ነበር ፡

ይህ ሁሉ ከቀድሞ ጀምሮ እስከ ቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን ከዚያም በኋላ እስከ ዘመነ ክርስትና ተያይዞ እንደመጣ አንድ እናሪያ ተብሎ ከንጉሠ ነገሥት በታች አንድ ንጉሥ ይሾምበት፤ ይነግሥበት ነበር።

ይህም ሊታወቅ ስለ ቀዳማዊ ምኒልክ በሚናገረው ዝዋይ በተገኘው ታሪክ እንዲህ ይላል አብሂል ከቢንያም ነገድ አልጋው ዙፋኑ ክብር የተሠራለት ንጉሥ ነበር። ግዛቱም ሉቅማ፣ ጅማ፣ ሌቃ፣ ትቤ፣ ጉማ ከተማውም ከፋ አገር እናሪያ ነው። እሱም ለንጉሠ ነገሥት ይታዘዛል በማለቱ ይታያል።

የእናርያ ከተማ የወላይታ ዳሞት ሀዲያ ኪንዶ ወይም ህንድ የሚባል ነበር። ቀድሞ ተጠቅልሎ በአንድ ንጉሥ ይገዛ ነበር። እንደ ገበዘ አክሱም ሊቀ ካህናት የዣንጅሮ ንጉሥ ነበረ። ባረብኛ ዣን ማለት ባለ ግርማ የሚያንቀጠቅጥ ማለት ነው። ጅሮ ማለት ድሮ ዘመን ይመስላል ስለዚህ ዣንጀሮ ማለት የድሮ ባለ ግርማ ንጉሥ ማለት ይሆናል እርግጡ ግን አልታወቀም።

የእናርያ ሕዝብ በአጤ ያግብአ ጽዮን ዘመን በሺ ፪፻፫ ዓመተ ምሕረት በአቡነ ተክለ ሃይማኖት ስብከት አምኖ ተቀብሎ ክርስቲያን ሆኖ የነበረ፤ የኢትዮጵያ ነገሥታት ኃይል እየደከመ እየጣረ ወደ ኋላ እያለ በሄደ ጊዜ አሮሞ ወረሳ እየመታ አገሩን እየወረረ፤ መምህራኑን ካህናቱን እየገደል፣ መጻሕፍቱን ቤተ ክርቲያኑን እያቃጠለ ቢያጠፋው፤ ከሞት የተረፈው ሕዝቡም የሚያስተምረው ቢያጣ፤ እንደ ገና ተመልሶ አረማዊ ሆነ። የክርስትናን ሃይማኖት አጥፍቶ በዘንዶና በዛር አመለከ። ጥንት የእናሪያን አገር ክርስቲያን እንደ ነበረ ዛሬውን የሚያስረዳ በአገሩ ውስጥ በብዙ ስፍራ ቤተ ክርስቲያን የሕንጻ ፍራሽ የመስቀል የጽና ሌላም የንዋየ ቅድሳት ስባሪና ምልክት የመጻሕፍትም ቁራጭ ይገኛል። በአንዳንድ ስፍራም በእየዋሻው፤ ታቦታቱ፤ መጻሕፍቱ፤ ንዋየ ቅድሳቱ፤ አልብሳቱ ሁሉ ይገኛል።

ክርስትና ከጠፉባቸው ወዲህ የእናሪያ ሕዝብ በዘንዶና በዛር እንዳመለከ የሚያስረዳ ከዚያ ወዲህ የሚነግሥ ዣንጀሮ ንጉሥ ለዘንዶ ይገብራል። ንጉሡም ባለ ብዙ ምሽት ነው። ደግሞ በግዛቱ ውስጥ ያለችውን የጨዋ ወገን የምትባል የባለጌም የድሃም የባለጸጋም ልጅ ብትሆን ሳይለይ ይደርስባታል። ብዙም ይወልዳል። በሞተ ጊዜ ልጆቹን ሁሉ ይሰበስቧቸዋል። ፺ም ፳ም እስከ ፪ም ቢሆኑ ከዘንዶው ቦታ ይወስዷቸዋል። መናገሻው ከዚያ ነውና። ልጆቹም ከዚያ ከአንድ ቦታ ይቀመጣሉ። ያልታወቁም ልጆች በዚያን ዕለት ይመጣሉ። እናቶቻቸው እኛም ከንጉሡ ነው የወለድናቸው እያሉ ያመጧቸዋልና ይቀላቅሏቸዋል። ብዙ ከብትም በየዓይነቱ ይታረዳል። የተሰበሰበው ሕዝብ ፪ ሺህ ክንድ የሚሆን ከልጆቹ ርቆ ቁሞ ከልብ እየጮኸ በልዩ ልዩ ዜማ እየዘፈነ ይጨፍራል። ጩኸቱና ዘፈኑ ማጉራቱም በደመቀ ጊዜ ዘንዶው ከጎሬው መዘዝ ብሎ ይወጣል። ከታረደው ከደሙ ሁሉ ይቀምሳል።

ከዚህ በኋላ ከልጆቹ በአንዱ ላይ ይጠመጠማል። የቀሩቱ ወንድሞቹ ፈጥነው ተነሥተው በግምባራቸው ተደፍተው ይሰግዳሉ። ከሩቅ ያለው ዘፋኙና ጨፋሪው ሕዝብም እየሮጠ ይቀርባል ሰግዶም ይደፋል ቀቢው ዘንዶው ተተርትሮለት ይሄዳል። ከጎሬውም ይገባል።

ይህ የተቀባ ንጉሥ ይነሣል። ሕዝቡንም ተነሣ ይለዋል። ሕዝብም ተነሥቶ ይሰግድለታል። የቀሩቱ ወንድሞቹ ግን ከዚያ ቀን ወዲህ እንደ ሕዝቡ ናቸው እንጂ ከንጉሥ ዘር ቁጥር የላቸውም። የሰጊዱን ሥራት ከፈጸመ በኋላ እንደ ወጉ ግብር ይገባል። ያ የታረደው ሥጋ ቀርቦ ይበላል። የተረፈውንም ከቤት አያገቡትም። ከዚያው ጥለውት ይሄዳሉ። ሥራታቸውና ወጋቸው እንዲሁ ነውና።

የተሰበሰበው ልዩ ልዩ ጎሳ ልዩ ልዩ ነገድ ስለሆነ፤ የሚበላውን እንደ ጠባይ እንደ ጠባዩ ያቀርቡለታል። አሁን አማሮችና ትግሮች የሹልዳ ሥጋ አይበሉም። የእሥራኤል ልጆች ነን ይላሉና ይልቁንም ነገሥታትና የነገሥታት እር አለን የሚሉ ሁሉ አይበሉም። እርማቸው ነው። በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፴፪ ቁጥር ፴፪ እንደ ተጻፈ ስለዚህ የእሥራኤል ልጆች ሹልዳ አይበሉም እስከ ዛሬ ድረስ። እግዚአብሔር የያዕቆብን ጭን (ሹልዳ) ዳሶ አፍዝዞታልና ያለውን ይዘው። በዚህም አማሮችና ትግሮች ይኮሩበታል። ሹልዳ አንበላም በማለት የእሥራኤል ልጆች መሆናቸውን ይመሰክራሉ።

እንዲሁም እኩሉ ቦፋት ወይም ዳሞት የሚባሉት የእናሪያ ሕዝብ ፍየል የማይበሉ አሉ። በግም የማይበሉ ዶሮም ዓሣም ተልባም የማይበሉ አሉ። በየጠባያቸው ያቀርቡላቸዋል የተባለ ስለዚህ ነው። ስለዚህም በየካህናታቸው በየዛር ፈረሱ በየቃልቻው እንደ ወጉ ይቀርብላቸዋል።

ይህን መሥዕዋት ከብሉ ከጠገቡም በኋላ የተረፈውን ከዚያው ጥለው ንጉሡን እያጀቡ እየዘፈኑ ወደ ቤተ መንግሥቱ ያገቡታል። እሱም ከቤቱ ገብቶ ከዝሙት በቀር ሌላ ሥራ የለውም።

ከዚህ በኋላ በዙርያው ያሉ ነገሥታት ወደ እርሱ መልዕክተኞቻቸውን ይልካሉ። ሕያው ንጉሥ ለማለትና ከመንፈሱ እንዲልክላቸው በረከቱም እንዲደርሳቸው በየመንግሥቱ ያለው የዛር አለቃ ሁሉ ይሄዳል። ከንጉሡ ይባረካል። በዘንዶ መጠምጠም የለዘበ ገላውን ይዳስስና እጁን ጨብጦ ከሰው ሳይነጋገር ወዳገሩ ንጉሥ በግስገሳ ይደርሳል። የንጉኑም ገላ በዚያ እጁ ይዳስስና ከእጁ እንዳይቀር በውሃ ከንጉሡ ራስ ላይ ይታጠባል። በዚያ ይባረካል።

ይህ ሥርዓት እስካሁን እስከ ዘመናችን ይደረግ የነበረ፤ እስከ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘመን ድረስ ይሆን የነበር፤ የሚልኩ ነገሥታትም የከፋ፣ የኩሉ፣ የኮንታ፣ የከምባታ፣ የወላይታ፣ የቀሩትም ሁሉ በዙርያው ያሉ አገሮች ነገሥታት ናቸው።

በዚያ ንጉሡ በተዳሰሰበት ቀን ታላቅ በዓል ይደረጋል። የዛር ዘፈን ይዘፈናል። በነዚህ ነገሥታት የሚሾመው የዛር ዓለቃ በሴትና በግዛት እየተቃኑ ከንጉሡ ጋራ እጅግ አይፋቀሩም። ስለዚህ አሁን በኛ ጊዜ የነገሡ የከፋ ንጉሥ ካሞየሮ የሚባል ከዣንጅሮ ከተቀባ በኋላ የዛርንም አለቅነት ጨምሮ ይዞ ንጉሥና የዛር አለቃ ሆነ። ከዚህ በኋላ ልጆቹም እንደዚሁ የቀሩትንም ነገሥታት የዛር አለቅነትን ደርበዋል።

ዛርን የሰደበ የሚፈርድበት ከዣንጅሮ ነው። በተፈረደበትም ጊዜ ለዘንዶው ይሰጣልና ይውጠዋል። ጥንት ነገሥታቱ ክርስቲያኖች ሳሉ ለዚህ ፍርድ አሳልፈው አይሰጡም ነበሩ ፡ አሁን ግን አረማውያን ሆነው የዛር አለቅነት ከደረቡ በኋላ ሰጡ።

አስቀድመን እንደ ጻፍነው በእናሪያ በዘመነ ክርስትና የክርስቲያን ጨዋ ወታደር ተሠራበትና ከክርስቲያን ተቆርጦ የቀረ የቄሱ ልጅ ቄስ፤ የሹም ልጅ ሹም፤ የጨዋው ልጅ ጨዋ፤ እየሆነ በየተሠራበት አገር ይኖር ነበር።

እንደዚሁም ሁሉ ሰንጋ ቦካ በላይ ብለት የምትባል አገር ትንሽ ኮረብታ አለች። ዛሬ ያቡነ ተክለ ሃይማኖት ታቦት ተተክሎበታል። ጥንት በዚያ ስፍራ ታላቅ ቤተ ጣዖት ቤተ ደስክ የሚባል የዛር መቅደስ ነበር። የክርስቲያን ነገሥታት መኳንንቱም ዘመቻ ሲነሱ ከዚያ ይሰፍሩና ከዛሩ አለቃ ምክር ተቀብለው ይዘምቱ ነበር። በአገሩም የነበሩ የጋፋት ሕዝብ አምልኳቸው በዚህ ቤተ ደስክ ነበረ። ይህንንም ቤተ ደስክ በኋላ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አፈረሱት ይባላል።

ስለ ነገደ እናሪያ ከሚናገር ታሪክ ከረጅም ባጭሩ ከብዙ በጥቂቱ ይህ ይበቃል። ከዚህ ቀጥለን እስላምን ታሪክ እንጽፋለን።

## ፲፯ ነገደ እስላም

በ፯፻፳ ዓመተ ምሕረት የእስላሞች የኒይና ንጉሥ በምሥራቅ አገር በእስያ መሐመድ ተነሳ። የምሥራቅን አገር ገለባበጠ። ወደ ሐበሻ ግን አልቀረበም። ነገር ግን በዓረብ አገር የነበረውን እስከ ሱዳን ያለውን የኢትዮጵያን ግዛትዋን እስከ ሀብትዋ ወሰደባት። እንዲሁም በሰሜን በኩል የጎደለባት የሚያስፈራው ከባዳው ሰይፉ ግን አልደረሰባትም በተራራ የታጠረች ኢትዮጵያ በክርስቲያን ጠበቀች ዳነች።

አጤ አምደ ጽዮን በነገሡ በ፲ ዓመት በሺ፫፻፬ ዓመተ ምሕረት ከብዙ ትዕግሥት በኋላ ከረሺን የሚባሉ የእስላም ሕዝብ ዓሚሮች እየሆኑ ከዓረብ አገር ተነሥተው መጥተው የባሕሩን ወደ ዳርዳሩን ይዱዙ ጀመሩ። ነገር ግን ከሐበሻ ንጉሥ በታች ሆነን እንገብራለን ብለው ነበሩ። እንዲህም ማለታቸው እስከንበረታ ብለው ነው እንጂ ቃላቸው እውነት አልነበረም። የመጡትም ዱዋሮን፤ ታሪሂን፣ ገድኤትን፣ አዴልን፣ ይፋትን፣ ባሊን እና ደራን ሌላም አገር ያዙ።

የኢትዮጵያ ነገሥታት በችልተኝነት በመታለል ዝም ባላሏቸው እነዚህ ሳይጠነክሩ ቢወጉዋቸው በኋላ መከራ አይጠነክርባቸውም ነበር። ነገር ግን በዚያ ዘመን በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ሁከትና ሽብር ሆኖ ነበርና ይህ ለእስላሞች ብዙ ጥቅም ሆነላቸው።

በይፋት ያሉ እስላሞች ብዙ ዓይነት ናቸው። አርጎባ ዶባሻጉራ ቃጭኖ የዓሊ ገዳዮች ናቸው። ዓሊ የመሐመድ አማች የፋጢማ የልጁ ባል ነው።

የእስላሞች የመጀመርያ ንጉሥና ነቢይ መሐመድ በመዲና ነገሠ። መዲና ማለት በግእዝና ባረብ ቋንቋ ከተማ ማለት ነው። መሐመድ ፳፫ ዓመት ነግሦ ሞተ። ከእርሱ ቀጥሎ አበጋዝ ዐሚር አቡበከር ሳዲቅ ካሊፋ ሆነ ማለት ነገሠ። ዘመነ መንግሥቱ ፪ ዓእምት ከ፫ ወር ነው። ከእርሱ ቀጥሎ ዑመር እብነ አልሐጣብ ከሊፋ ሆነ። ኢየሩሳሌምን ምስርንም ያዘ። ፲ ዓመት ነገሠ ሞተም። ከእርሱ ቀጥሎ ዑስማን እብነ ሐፉን ከሊፋ ሆነ። እስክንድርያን ያዘ። የኢትዮጵያ አገሮች አስልሞ በነገሠ በ፲፱ ዓመት ሞተ። ከእርሱ ቀጥሎ ዓሊ የፋጢማ ባል ነገሠ። በነሱ ቁጥር በ፴፩ ዓመት እሱም ዓሊ በነገሠ ጊዜ ከነኸርዋን ኸዋርጅን የሚባሉ በእስላሞች የማይጋጠሙ ሽፍቶች ነበሩ። ዓሊ ፈጃቸው። ከ ፬ሺ ፫ ሰዎች ብቻ ሲያመልጡ ሁሉን አረዳቸው። በነኸረዋን ቀጣሚት የምትባል አንዲት ሴት ነበረች። ከኸዋርጀዋን ነበሩና አባትዋን ባሏን ወንድሞቿንም ዓሊ ፈጃቸው።

እነህ ከዓሊ ሰይፍ ያመለጡ ሰዎች እናግባሽ አሏት። አሱዋም እኔን የሚያገባ ዓሊንና መዐውያን አልእስን እኒህን ሦስቱን የገደል ነው ያለዚያ ወንድ አለ ብዬ አላገባም አለቻቸው። እኒህም ሦስቱ የሦስቱን ለመገደ በእጣ ተካፈሉ። አንዱ ወደ መዐውያ ሄደ። መዐውያን ረጅም ነበረና ጉልበቱን አቆሰለው። ሳይገድለው ተያዘና ተደብድቦ ሞተ። መዐውን ግን ካቆስለው በኋላ ጉልበቱ ደከሞአልና አልወለደም። ይህ መዐውያ የመሐመድ ታላቁ አበጋዝ ነው።

ወደ አልአስ የሄደው አሳስቶ ምስለኔውን ገደለና ተያዘ። በምስር ከተማ በካይሮ ተሰቀለ። እበነ እልአስም የመሐመድ ታላቅ አበጋዝ ነው። እሱም ምስርን ይገዛ የነበረው ነው።

ወደ ዓሊ የሄደው በመስጊድ መንገድ ተሸምቆ ቆየውና በመርዛም ጦር ወጋው። በ፫ኛው ቀን ሞተ። ዘመነ መንግሥቱ ፬ ዓእምት ተ፱ ወር ነው። ገዳዩም ስሙ አብድራሕማን ይባል ነበረ። እሱም ተይዞ ተሰቀለ።

በይፋት ያሉ አርጎቦች የዚህ የዓሊ ገዳይ የአብድራሕማን ዘሮች ናቸው። ስለዚህ ከሞተ በኋላ በዓረብ አገር ለመኖር የማይቻላቸው ሆነ።

ዓሊ ከሞተ በኋላ ከፋጢማ የተወለደውን ልጁን ሐሰንን አነገሡት። ሐሰን ግን እኔን ልትገድሉኝ ነውን ብሎ አልነግሥም አለ። ስለዚህ ከሊፋነትን ማለት አልጋን በሻም አበጋዝ ለነበረው ለመዐውያ ሰጡት። እሱም ከሊፋ ሆነ። ስለዚህም አብዱራሕማን ዘሮች የዓሊን ደም በቀል ስለ ፈሩ በይፋት መጡ ማለት በግልጥ ይፋት ማለት ግልጥ ማለት ነው። እኒህ እስላሞች በዓረብ እስላሞች ዘንድ ከእስላም አይቆጠሩም። ስማቸው ወይም አበጋዛቸው ወላስማ ይባላሉ። ወላስማ ማለት ወላ እስላም ማለት ነው። ወላ እስላም ማለት እስላም ያይዶለ ማለት ነው። አባታቸው ዓሊን ስለገደለ ይህን ስም ከዓረቦች ተቀበሉ ይባላል። መልካቸው ዓረቦችን ይመስላሉ። ቀዮች ናቸው። ቋንቋቸውም ዓረብኛ ነው። ግእዝን ይመስላል። መጀመርያ በሐበሻ የገቡ እስላሞች ናቸው። ጥንት በኢትዮጵያ የነበሩ ሕዝብ የኢትዮጲስ ልጆች ሳባ፣ ኖባ፣ በውለ እና ከለው ናቸው። በትግሬ ያሉ ሕዝብ የሳባ ወገኖች ናቸው።

የበለው ልጆች በድሆኖ በሐርንነ በምጥዋ ያሉ ናቸው። አለቃቸው ናይብ ይባላል። እሱም በዓሊ ጊዜ አሰለሙ።

የኖባ አገር ከአትባራ ከተከዜ በመለስ እስከ ነጭ አባይ ድረስ ነው። ቅዱስ ማቴዎስ ወንጌላዊ አጥምቋቸው ክርስቲያኖች ሆነው ነበሩ። በዓሊ ጊዜ ሰለሙ። ከተማቸው ካርቱም ነው።

በኢትዮጵያ የገቡ እስላሞች አራት ዓይነት ናቸው። መጀመርያ ሕምሪያ ወይም ሕምያር ይባላሉ ቀይ ማለት ነው። ሁለተኛ ትግሬ ይባላሉ ነጋዴ ማለት ነው። ሦስተኛ አርጎቦች ናቸው። አራተኛ በመዐውያን ጊዜ ከዓረብ አገር ወደ ኢትዮጵያ ተሰድደው የመጡ ናቸው።

ስለ ነገደ እስላም ከሚነገር ከብዙ በጥቂቱ ከረጅም ባጭሩ ይህ ይበቃል። ከዚህ ቀጥለን የወረሴሆችን ታሪክ እንጽፋለን።

## ፲፰ ነገደ ወረሲህ

የወረሴሆች ነገርና ትውልድ እንዲህ ነው፤ ግራኝ አሕመድ ኢትዮጵያን ባጠፋ ጊዜ በሺ፩፻፲፩ ዓመተ ምሕረት ከባሕር ማዶ ከዓረብ አገር ሼህ ዑመር የሚባል የብር ዘንግ የብር ርከት አሲዞ መጣ። በየጁ ገብቶ ተቀመጠ። ሼህ ዑመር ብዙ ሴቶች አግብቶ ብዙ ልጆች ወለደ። መንደሩ ቢበዛ ወረሺህ ተባለ። አሁን ወረሴህ የሚባሉ የእሱ ዘሮች

ናቸው። ወረሽህ ማለት የሺህ መንደር ማለት ነው። ልጆቹ ከወረሽህ ወረሴህ የመባል ስም ተቀበሉ።

የሼህ ዑመር ልጆች የባሕሩ ወሌ ይባል ነበር። ወሌ አብዬን ወለደ። አብዬ ቢወልድ ባባቱ ስም ወሌ አለው። ወሌ አባ ጎትየን ወለደ። አባ ጎትዮእ አባ ሴሩን ጓንጉልን ወልደ።

አባ ሴሩ ጓንጉል መልኩ እጅግ ያማረ የተዋበ ነበረ። ኃይለኛ ጀግና ፈረሰኛ ሆነ። ጀግንነቱ ኃይሉም በቤተ መንግሥት የታወቀ ሆነ። ክርስትና ተነሥቶ የላስታንና የሰለዋን ባላባትየራስ ፋሪስን እህት ወይዘሮ ገለቡን አገባ። ክርስትናም አልተነሣ በእስልምና እንዳለ ላስታ ሄዶ ዘርፎ አምጥቶ አገባት የሚሉም አሉ። ነገር ግን ይህ እውነት አይዶለም። ሐሰት ነገር ነው። ጓንጉል ክርስትና ተነስቶ ወይዘሮ ገለቡን አግብቶ ከወይዘሮ ገለቡ ራስ ዓሊን ወይዘሮ ከፈይን ራስ አሊጋዝን ወለደ። ራስ ዓሊ ደጃች ፋሪስን ወለዱ። ደጃች ፋሪስ ደጃች አባይን ወለዱ። የደጃች አባይ ልጆች ብዙዎች ናቸው።

ወይዘሮ ከፈይ የኢልማን ዖርማን ባላባት መርሶ በሬንቶን አግብተው ራስ ጉግሳን እና ደጃች አሉላን ወለዱ። ደጃች አሉላ ከወሎ ይማሞች ልጆች ወይዘሮ መነንን፤ በኋላ አጤ ሣህሉን አግብተው እቴጌ የተባሉትን አግብተው ራስ ዓሊን ወለዱ። ራስ ጉግሳ ወይዘሮ ሎሚታን አግብተው ራስ ማርዬን፣ ራስ ይማምን፣ ራስ ዶሪን እና ወይዘሮ ሂሩትን ወለዱ። ወይዘሮ ሂሩት የሰሜኑን ባላባት የራስ ገብሬን ልጅ ደጃች ኃይለ ማርያምን አግብትው ደጃች ብጡልን፣ ደጃች መርሶን እና ወይዘሮ የውብዳርን ወለዱ።

ደጃች ብጡል የሜጫይቱን ወይዘሮ የውብዳርን አግብተው እቴጌ ጣይቱን፣ ፊታውራሪ አሉላን፣ ራስ ወሌን እና ወይዘሮ ደስታን ወለዱ። እቴጌ ጣይቱ የዳግማዊ ምኒልክ ሚስት መካን ናቸው። ፊታውራሪ አሉላ ወይዘሮ የተመኙን ወለዱ። ራስ ወሊ ራስ ጉግሳን፣ ወይዘሮ ከፈይን፣ ደጃች አመዴን እና ደጃች ኃይሌን ወለዱ። ወይዘሮ ደስታ ደጃች ወልደ ሐናን አግብተው ደጃች ገሠሠን እና ወይዘሮ አሰለፈችን ወለዱ። ደጃች መርሶ ደጃች ትኩን እና ወይዘሮ ላቀችን ወለዱ። ራስ አሊጋዝ ደጃች ጎጅን እና ደጃች ብሩን ወለዱ። ደጃች ጎጅ ልጅ ዘለቀን ልጅ ዘለቀ አባ ግርሻን ወለዱ። ደጃች ብሩ ደጃች ዘገየን ወልዱ። ደጃች ጓንጉልን ደጃች ዓሊን፣ ደጃች አሊጋዝን፣ ወይዘሮ ሂሩትን እና ደጃች ኃይሉን ወለዱ። ደጃች ጓንጉል ደጃች ይማምን እና ደጃች ዓሊን ወለዱ።

እነሂ ወረ ሴሆች የጓንጉል ልጆች ከታላቅ ዓሊ እስከ ታናሽ ዓሊ በክርስትና ሃይማኖት ጸንተው ከነየልጅ ልጆቻቸው ፺ መሳፍንት የጁን ላስታን አገውን ዋድላን ደላንታን ወሎን በጌምድርን ስሜንን፣ ጎንደርን፣ ወገራን፣ ደምቢያ፣ ቋራን፣ አገው ምድርን፣ ዳሞትን፣ እና ጎጃምን አንድ አድርገው የጎንደርን መንግሥት አጥፍተው ፷፰

ዓመት ገዙ። ፸፩ ዓመት የሚሉም አሉ። ነገር ግን ቢቆጠር አይሞላም። በእርግጥ የወረ ሲሆች ግዛት የራስ አሥራትንና የራስ ወልደ ገብርኤልን ፲ ዓመት ጨምሮ ፷፰ ነው።

እኒህ ወረ ሲሆች በፊት እንዳልነ ክርስትናቸው በጓንጉል ጊዜ ነው። ልጆቹ ክርስቲያኖች ሆነው፤ ታላቁ ራስ ዓሊ ባገራቸው በየጁ ፯ ደብር ተከለዋል። እርሳቸውም ጉባርጃ ማርያም፣ ጉባላፍቶ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወልያ ገብርኤ፣ ኪበቃሎ ቅዱስ ሚካኤል፣ ዛምል ጊዮርጊስ፣ ገዶ መድኃኒዓለም እና ሾዋና ማርያም ናቸው።

የጁ ጥንት ስምዋ ገነቴ ትባል ነበር። የሁ የተባለችበት ምክንያት እንዲህ ነው ጉባርጃ ማርያም በገነቴ ምድር የከበረች ደብር ናት። በእርስዋ ጳጳሳት ይኖሩባት ነበር። ፯ ጳጳሳት ተቀብረውባታል ይባላል።

በዚያች አገር ጣዖታትን የሚያመልኩ በስማቸው የሚመኩ አስማተኞች ሰዎች ነበሩ። በዚያ ዘመን የነበረ ጳጳስ ንስሓ ግቡ በወንጌል ዕመኑ አስማት ማድረግን ጣዖት ማምለክን ተው ብሎ ቢገሥጻቸውና ቢመክራቸው እጅግ አጥብቀው ጠሉት ቃሉን አልተቀበሉትም። እኒህ አስማተኞች ሲቀሩ የቀሩት ያገር ታላላቆች ወደ ጳጳሱ እየሄዱ የወንጌል ትምህርትና ሃይማኖት እየሰሙ ከዕለት ወደ ዕለት ብዙዎች ወደ ክርስትና ይገቡ ጀመሩ። አስማተኞችም ክብራቸውን እንደ ተገፈፉ በሥራቸው እንደ ተነቀፉ ባዩ ጊዜ እንደ ሕጻን ሰርቀው በስውር አርደው ለጳጳሱ ወጥ ሥራ ይህን ወጥ ሠርተህ ጳጳስ ግብር በሚያበላበት ጊዜ ከጳጳሱ ፊት ይህን አቅርብልን። ይህ ምንድን ነው ቢሉህ የወትሮ ግብርዎ ነው ብልህ በሰው ሁሉ ፊት አሳፍርልን ብለው እጅግ ብዙ ገንዘብ ሰጡት። መማለጃ የፈራጆችን ዓይን ያሳውራል እንዳለ መጽሐፍ ዘፀዓት ፳፫ ፣ ፰ እሱም ብዙ ገንዘብ ተቀብሎ እንዳሉት አደረገ። የወጡ ሰታቴ ድስት በተከፈተ ጊዜ የዚያ ሕጻን ሁለቱ እጆቹ ከሌላው ሥጋው ጋር ወጥ ተሠርቶ አዩ። ጳጵሱም አብርዋቸው የተቀመጠውም ሰው እጅግ አጥብቀው ደነገጡ። አንተ ዛሬ ያደረግኸው ነገር ምንድር ነው ቢሉት እንደ ተመከረው ጌታዬ እኔ ዛሬ አዲስ እንገር አላመጣሁም ያው የወትሮ ግብርዎ ነው አላቸው። ሰውም ሁሉ ደነገጠና ፈራ። ጳጳሱም እጅግ አዘኑና እኔ የሰው ሥጋ ካሁን በፊት ስበላ ታውቃኛለህን ሰው ስጋ ከነእጁ ሠርተህ ያቀረብህልኝ አንተ ከጠላቶቼ በገንዘብ ተገዝተህ ይህን ታላቅ ድፍረትና ክፋት በገንዘብ መውደድ ልብህ ጠፍቶ አድርገሃልና ለዘለዓለም ርጉም ሁን። ንብዘ ልብ ሁን ብለው ረገሙት። ያን ጊዜውውን ልብሱን ጥሎ ሱሪውን ቀዶ ራቁቱን ሆኖ በሰዎች ፊት አብዶ በረረ ገደል ገብቶም ሞተ። ይህንንም ያዩ ሁሉ ሰዎች ከነዚያ ወገን ወደ ክርስትና ገቡ። አገሩንም እንዲህ ሲሉ ረገሙት። የዚህ አገር ሰውም ለኔ ስም ማከፋት ብለው ሰውን ገድሎ እጁን ቆርጦ አናቱን ፈጥፍጦ በሰው እንደ ተጫወተ የእጁን ይስጠው። ሁልጊዜ ደም ይፍሰስበት። እርስ በርሱ ይተላለቅበት።

ጳጳሱም አይቀመጥበት ብለው ረገሙት። ከዚያ ወዲህ ገነቴ መባሉ ቀርቶ አገሩ የጁ ተባለ። እርስ በርሱም በወፋ ውጊያ ሁልጊዜ የሰው ደም የሚፈስበት በከንቱ ነፍስ የሚወድቅበት የተረገመ አገር ሆነ።

የየጁ ሰዎች ይህ መርገም ስለ ጳናባቸው አገር ላትገዙበት ጠጅ ላትጠጡበት ቀሚስ ላትለብሱበት ስም ላታወጡበት ስለምን እርስ በርሳችሁ በከንቱ ትጋደላላችሁና ወገን ከወገኑ ይጋባል ቢሏቸው፤ ቆይሌቱ ደም ትወዳለችና ወፋ ውጊያ ሲቀር ካፋፍ ላይ ዘልቃ እሪ ትላለች። ስለዚህ ሰው ሁሉ ጋሻ ጦሩን እየያዘ ካገሩ ይወጣልና በየመልካው ይወርዳል። በያላ ወንዝ፣ በጥቁር ውሃ፣ በሸሊ እና በሚሌ እየወረደ ወፋ ይዋጋል ይላሉ።

ይህስ ቢሆን ክርስቲያን ከሆናችሁ በክርስቶስ ካመናችሁ ይህን ከንቱና ክፉ ሥራ ብትተውት ምነው ቢሏቸው፤ ያገሩ ቆሌ ሰውም ደም የለመደች ናትና ወፋ ውጊያ ሲቀር ከሰማይ ዝናብ ያንስብናል። ብናርስም እህሉ ይጠፋብናል። አገራችንም ይራብብናል። በሽታም ይነሳብናል። ወፋ በተዋጋነ ጊዜ ግን ዝናብ በበረከት ይወርዳልና እህልም ይወጣልና አገራችንም ጥጋብ ጤናም ይሆናል ይላሉ።

ባጠገባቸውም በዙርያቸው ያሉ ጎረቤቶቻችው አረማውያን በስም ክርስቲያን የሚባሉ ሳይቀሩ ይህን ከንቱ ወሬ እየሰሙ ባገራቸው ዝናብና በረከት የእህል ብዛት ጤናም እንዲሆን አስበው ይህን ወፋ ውጊያ ለመዱ።

ይህም የወፋ ውጊያ እስከ ሽዋ ድምበር እስከ ዶባ እስከ መራቤቴ፣ ተለምዶ እስካሁን እስከ ዳግማዊ ምኒልክ ዘመን ድረስ ይዋጉ ነበሩ። ጃንሆይ አጤ ምኒልክ በመንግሥትዎ አገር ያለን ወፋ ተዋጊን ሁሉ ይህን ከንቱ ጥፋት በአዋጅ አስተዉት። ብዙ ቀንም በስውር ተጣቅሶ ወርዶ እስር በርሱ እየተዋጋ አስቸግሮ ነበር። በገዳይና በሙዋች ቤት ዕዳ እያከፈሉ አስተውት። ይህም ሆኖ በማመስገን ፈንታ ይህን በከንቱ መሞት አስቀሩብን ብሎ ያዝናል። ጃንሆይም ያማል። ልብ ያለውና ያስተዋለ ግን በወፋ ውጊያ መቅረት እግዚአብሔርንና ጃንሆይን ያመሰግናል። ባለፈው በዘመዶቹ በከንቱ ጥፋት እጅግ ያዝናል ይጠጣታል።

ስለ ወረ ሲሆች ትውልድና አመጣጥ ከሚናገር ከብዙ በጥቂቱ ከረጅም ባጭሩ ይህ ይበቃል። ከዚህ ቀጥለን የነገደ ጉራጌን ታሪክ እንጽፋለን።

## ፲፱ ነገደ ጉራጌ

የነገደ ጉራጌ ነገር እንዲህ ነው። በአጤ ዓምደ ጽዮን ዘመን ከትግሬ ጉርዓ ከሚባል አገር አካለ ጉዛይ ክፍል የወጣ ሠራዊት ከአዝማች ስብሐት ጋር መጥቶ በአይመለል ተሠራ። ስለዚህም የዚያ አገር ሕዝብ ጉርዓጌ ይባላል። አጤ ዓምደ ጽዮን የነገሡ ካንድሺ ፫፻፳፯ - ሺ፫፻፶፫ ዓመተ ምሕረት ዘመነ መንግሥታቸው ፴ ዓመት ነው።

የጉርዓጌ ሕዝብ ከጉርዓ ተነሥተው ወደ አይመለል የገቡ በዚያ ዘመን ነው። ጉርዓጌ ማለት የጉርዓ ሰዎች ምድር ወይም አገር ማለት ነው።

ዳግመኛም ከንጉሡ ሠፈር ግራ ስለ ሰፈሩ ግራጌ ተባሉ በቀን ብዛት ግን ግራጌ ተለውጦ ተባሉ ይላሉ።

## ፳ ከምጥዋ እስከ መተማ በኢትዮጵያ ዳር ለዳር በቆላው ስለ አሉ ሕዝብ

ከምጥዋ እስከ መተማ ወይም እስከ ቋራ ጥግ ያሉ ሕዝብ ልዩ ልዩ ወገኖች ናቸው። በፊት እንዳሳየነ የሳባ ልጆች በትግሬ ይኖራሉ። እነዚህ የኢትዮጲስ ልጆች ናቸው። ከነዚህም የተለዩ የበለው ልጆች በደኖና በሐርጊጎ በምጥዋ በምንኩሉ ያሉ ሕዝብ ናቸው። አለቃቸው ናይብ ይባላል።

የከለው ልጆች በፊት እንዳልነ ከሳባ ወደ ምዕራብና ወደ ደቡብ ያለ ያማራ፣ የወልቃይት፣ የጠገዴ፣ የጠለምት፣ ያርማጩሆ፣ የአዋ እና የቋራ አባት ነው።

የኖባ ልጆች ደግለሎች፣ ጃሊሎች እና ምንዓሚሮች ናቸው። ከነዚህም ሌላ በቆላው የሚኖሩ የካም ልጆች ኩናሞች፣ ሱዳኖች፣ ትክሪሮች፣ ግንጃሮች፣ ፌግኖች፣ እና ሻንቅሎች ናቸው።

ከበለው ገለበትና የባርያ ሻጭ (ሻግያ) ባለመከራ የሚባሉ ወገን አሉ። ለምልክት ገላቸውን ይበጣሉ ከአዲያቦ በስተ ሰሜንም ባርያ ተብለው የሚጠሩ ሕዝብ አሉ። ከነእርሱ መሀከልም ኢልግ የሚባሉ ጨዋዎች አሉ። የሰውነታቸው መልክ ሁሉ ከኢትዮጵያ ሕዝብ በምንም አይለዩም። የብቻቸው ቋንቋና ፊደል መጻሕፍትም አሏቸው ይላሉ። ከወገናቸው ያልሆነ ሰው እንዳያውቅባቸው እነዚያን መጻሕፍታቸውን በብዙ

ጥንቃቄ ይጠብቋቸዋል። ይህ ትምህርት እንደ ምስጢር ካባት ወደ ልጅ እየተያያዘ ይወርዳል። ከእነሱም የሚማሩት እጅግ ጥቂት ናቸው። ከምድር በታች እንደ አዳራሽ የሆነ እጅግ ሰፊ ሰፊ ዋሻ አላቸው። በድንገት በሜዳ ሳሉ አደጋ ካልጣሉባችወ ጠላት ሊያገኛቸው አይችልም። አምልኳቸው ከክርስቲያንና ከእስላም የተለየ ነው።

# ፷፭ ከሐረርጌ እስከ ምጥዋ ወሰን ስላሉ ሕዝብ

ከሐረጌ እስከ ምጥዋ ወሰን ቆላ ቆላውን በረሃውን የያዙ ሕዝብ በፊት ከዮቅጣን ልጆች ነገደ አባልና አፌር ነበሩ። ነገደ አባል የአዳልንና የሱማሌን ምድር በነገደ አፌር፤ የኢሳንና የውጋዴን ምድር ይዘው ነበር። የነገደ አፌር ከተማ ዛሬ አፌር የሚባለው በውጋዴን ውስጥ ነበር። ዛሬ ግን ነገደ ኢሳ፣ ነገደ ሱማሊ፣ ነገደ አዳል፣ ነገደ ዳንክሊ፣ ነገደ ሻሆ፣ ነገደ ቶርን፣ ነገደ አሳሁታር እና ነገደ ጥልጣል ከእስያ መጥው ነገደ አባልን አስለቅቀው አገሩን ወረሱ። ነገደ ሱማሊ ነገደ ኢሳ የኦፌርን ሕዝብ አስለቅቀው አገሩን ወረሱ። ከነገደ አባልና ከነገደ ኦፌር ከዚያ የተሰደዱ ከደጋው ኢትዮጵያ ወጥተው ከነገደ ሳባ ከወንድሞቻቸው ተቀላቀሉ። የጥንት አገራችንን አንለቅም ያሉ፤ ለመሰደድ ጉልበትና ኃይል ያጡ ግን ከነዚያ ተመሳስለው ቀሩ። አሰለሙና ተቀላቀሉ። እኒህ ሁሉ ሕዝብ በየጊዘው ከእስያ እየፈለሱ የገቡ ናቸው።

ኢሳ የተባሉ ሕዝብ የኤሳው ዘሮች ናቸው። አዳል፣ ሱማሌ፣ እና ዳንከኔ የካም ልጆች ናቸው። ሻሆ፣ ቶርን፣ አሳሁርታ፣ እና ጥልጣል ከዓረብ ዘር ናቸው። ሻሆ፣ አሳሁርታ እና ቶርን እርስ በእርሳቸው ተቀላቅለዋል። ስለዚህም አገራቸው በቶርን ወይም በአሳሁርታ ስም ይጠራል።

አዳሎችና ጥልጣሎችም ተቀላቅለዋልና እንዲሁም ቋንቋቸው እርስ በርሱ ይመሳሰላል። ሁሉም በዓሊ ዘመን አሰለሙ ይባላል። ወደ ኢትዮጵያ የወጡበት የዘመን ጊዜም አይታወቅም።

# ፷፪ የሐረርጌ ሕዝብ

ከሐረርጌ ግምብ የሚኖሩ ሕዝብ ከሐማሴን የመጡ ሕዝብ ናቸው። በሐማሴን አንድ ኃይለኛ ጀግና ሰው በአጤ ዳዊት ዘመን ነበረ። በኃይለኝነቱ ሰው ጠልቶት ከሰው ተለይቶ ምሽቱንና ልጆቹን ይዞ ለብቻው በችፍግ ዱር ውስጥ ቤት ሠርቶ ተቀመጠ።

ከዕለታት አንድ እን ብዙ ቅቤ ምሽቱ አጠጣችው። እሱም ደከሞ ለብቻው ከቤት ተኝቶ ቀረ። ምሽቱ ግን አዝመራ ለመሰብሰብ ልጆችዋን ሁሉ ሰብስባ ይዛ ወደ ሥራ ሄደች። ማታ ልጆችዋን ይዛ ብትመለስ ባልዋን አንበሳ ጎትቶ ከወለሉ ሞቶ ተንዘራግቶ ቆያት። የጠጣውን ቅቤ ከሆዱ ቀድዳ፤ በዕቃ ቀድታ፤ ለወንዶች ልጆችዋ ሁሉ አቀመሰቻቸው። ይህንንም ማድረግዋ ጠንቋይ ባልሽ ሊሞት ጊዜው ደርሷል፤ በድንገት ሳይታሰብ አንበሳ ይገድለዋልና ቅቤ አጠጪው አንበሳ ከገደለው በኋላ ሆዱን ቀድደሽ ከሆዱ ያለውን ቅቤ በዕቃ ተቀብለሽ ለልጆችሽ አጠጪያቸው። አንደ አንበሳ ባለ ግርማ ይሆናሉ። ጠላትም ከፊታቸው አይቆምም። አሽናፊዎች የሚያስፈሩ ይሆናሉ ብሏት ነበርና ስለዚህ ነው ይላሉ። ይህ ታሪክ በገድለ ማርቆስ ተጽፏልና በዚያ ተመልከት።

ከዚህ በኋላ ጠላቶች ያባታቸውን ሞት ሰምተው እንግዲህ የዚያን የርጉም ልጆች ከምድር እናጥፋቸው ብለው ተነሡባቸው። በተዋጉም ጊዜ እኒህ ልጆች ድል አድርገው ጠላቶቻቸውን ፈጇቸው ጦርም ከፊታቸው የማይቆም ሆነ። አገር እያሴሩ እንደገና ጦር እየሆነ ቢያስቸግራቸው ጓዛቸውን አንሥተው ከብታቸውን ነድተው እየተዋጉና እየተከላከሉ እስከ ሐረርጌ ተሰደዱ በዚያም ተቀመጡ። ከብዙ ዘመን በኋላ በዙርያቸው ያለ ኦሮሞ የሚያኖራቸው ቢሆን ከወንድሞቻቸው አንዱን በላያቸው አለቃ ሹመው ኦሮሞውን እየተዋጉ ድል እያደረጉ በዙርያቸው ያለውን አሸንፈው ገዙት። ሌት አደጋ እየጣለ ቢያስቸግራቸው አገራቸውን ዙርያውን በብርቱ ግምብ አጠሩ። ፭ በርም አደረጉለት። ከዘመን ብዛት ቋንቋቸውን ትግርኛ የነበረ ተለውጦ ሌላ ሆነ። ነገር ግን ዛሬም ቢሆን ከትግርኛ ብዙ ይመሳሰላል። በፊት የኢትዮጵያ መንግሥት ሳትደክም ለኢትዮጵያ መንግሥት ይገዙ ይገብሩ ነበሩ። በኋላ ግን ለቱርክ መንግሥት ተገዙ።

ከዚህ በኋላ በ፲፰፻፸፱ ዓመተ ምሕረት ጃንሆይ አጤ ምኒልክ ሐረርጌን ከፍለው ንጉሡን ድል ነሥተው ያዙ። ራስ መኮንን ሹመው ተመለሱ። የሐረርጌ ቋንቋ ከግምብ ውስጥ ነው እንጂ ከውጭ የለም።

ይህ ሁሉ የተቆጠረ ሕዝብ ጥንት የኢትዮጵያ መንግሥት ዜጋ ነበር። ዛሬ ግን ኢትዮጵያ ከታላቅነትዋ ከስፋትዋ እያነሰች እየጠበበች ሄደችና የዛሬ አገርዋ ፫ ክፍል ብቻ ቀረች። እኒህም ፫ ክፍሎች ቆላ ወይና ደጋ ይባላሉ።

# ፳፫ የኢትዮጵያ ወሰንና ደግ አገር እንደ ነበረች።

የጥንት ድንበሯ ከጅቡቲ ባሕር ዳር ጀምሮ እስከ ስናር እስከ ነጭ አባይ ድረስ ነበር። በሰሜንም ከ፪ተኛው ሃገረ ናግራን ወዲያ በርበር የስምር ወገን ይመስለው ነበር።

በቆላው ብዙ ልዩ ልዩ አትክትና ፍሬ ይገኝበታል። በደቡብ ቆላ፤ ባቢሊ፤ በቦረና እና በጅጅጋ አውራጃ የዕጣን የላስቲክ ዛፍ የሰንደል እንጨት ከርቤ ሌላም ብዙ ቅመምና የሚበላ ፍሬ ይገኝበታል። የከበረ የጠራ ወርቅም ዕንቁም ሉልም በኢትዮጵያ ይገኛል። ዝባድም ልዩ ልዩ ዓይነት ሽቱም አለበት። ኢዮብ ፳፰ ፲፯ -፲፱፤ ፩ነገ ፲ ፲ -፲፫ ፪ዜና ፱፤ ፱ -፲፪ ተመልከት። የኢትዮጵያ መንግሥት ግን ኃይሏ እየደከመ ፍርቅና አንድነት እውቀትም እያደረ ቢግድልባት ይህን የመሰለ አገሩዋን ሁሉ ከውጭ የመጡ ባዕዳን ሕዝብ ያዙባት።

ጥበብንም ከብልሃተኞች የጠየቅን ናቀችን ቸል አለች። በቀድሞው እወቀትዋ እንደ ተሰበረ መኪና ቁማ እኖራለሁ ብላ ተመካች። ነገር ግን ይህ ሳይቀር ደግሞ ከቀድሞው እወቀትዋ እጅግ በረደችና ቀዘቀዘች ብዙም አነሰች።

የቀድሞው ታሪክ ጸፊ ግን ሔሮዶቱስ የሚባል የግሪክ አገር ሰው ፬፻፷፬ ዓመት ከልደት በፊት የነበረ ከእርሱ ዘመን በፊት ምስርን ጨምረው የገዙትን የኢትዮጵያን ነገሥታ ታሪክ ሲናገር ፲፰ ነገሥታት ምስርን ጨምረው ገዙ ሲል በታሪክ መጽሐፉ ጽፏል።

ዳግመኛም ይህ ሔሮዶቱስ ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ደግነት ሲናገር እንዲህ ይላል። በኢትዮጵያ እጅግ ያማሩ ሕዝብ ባለ ደም ግባት ቆንጆዎች ውቦች ሰዎች አሉባት። ርኅራኄያቸውም እንደ እግዚአብሔር ነው። በሰፊ ሜዳ ለመንገድ አላፊ የሚሆን ድግስ እየደገሱ ያሰናዳሉ። ምንም ቢሆን መንገደኛ በመንገድ የሚበላውን አያጣም። እድሜያቸው ከ፻ እስከ ፻፷ እስከ ፻፹ም ይቀመጣሉ። ነውር ክፉ ነገርም ባገራቸው የተጠላ የተጸየፈ ነው። የጤና ምንጮች የሚሆኑ ወሆች አሏቸውና። እሱን በጠጡ ጊዜ ሰውነታችወ ይታደሳል። በሀብትም እጅግ ባለጠጎች ናቸው።

እንዲህ ያለች እጅግ ያማረች በልዩ ወገን ሰው በባዕድ አፍ የተመሰገነች፤ የከበረች አገር፤ ዛሬ ግን ፍቅር በማጣት እርስ በርስዋ ባለመስማማት፤ ያንድነት ኃይሏን አፍርሳ በመለያየት፤ የደም መፍሰስ የግፍ የክፋት ነውር ሁሉ ከተማ ሆነች። ኢሳ ፶፱ ፫ -፲፫ ተመልከት።

ኢትዮጵያ ቆላው፤ የዓመት ሙቀቱን ቢያካፍሉት ከ፳ -፳፫ ዲግሪ (ማዕርግ) ይደርሳል።

ወይና ደጋው እጅግ ጤናማ አገር የሰጡትን ዘር ልዩ ልዩ ዓይነት አትክልትም የሚያበቅል ነው። ሙቀቱም በዓመት ቢያካፍሉት ከከ፲፮ -፲፱ ዲግሪ ይደርሳል።

ደጋው ከደጋው እህልና ዛፍ በቀር ሁሉን አያበቅልም ሙቀቱም ከ፯ -፫ ዲግሪ እስከ ዜሮ ይደርሳል።

ስለ ኢትዮጵያና በውስጧ ስለሚኖሩ ሕዝብ ከሚነገር ከብዙ በጥቂቱ ከረጅም ባጭሩ ይህ ይበቃናል።

# አባሪ ፩

## ከልደት በኋላ በኢትዮጵያ የነገሡ ነገሥታት ዘመነ መንግሥት

| ስም | ዘመን | ዓመተ ምሕረት |
|---|---|---|
| ባዜን ከልደት በፊት ፫ ዓመት ከልደት በኋላ ዘመነ መንግሥቱ ድምር ፲፯ ዓመት ምሕረት | ፰ | ፰ |
| ሥሮጡ ስመ መንግሥቱ ጸንፈ አስገድ | ፳፮ | ፴ |
| ጽንፈ አርእድ | ፱ | ፴፱ |
| ሰጥታህ | ፫ | ፵ |
| ሆር ኤምተኩ | ፱ | ፵፱ |
| ገርስሞት ንግሥት | ፫ | ፶ |
| ሀተዘ ባሕር አስገድ | ፳፫ | ፷፫ |
| ምሲንህ ግርማሶር | ፯ | ፹፫ |
| ስጥዋ ግርማ አስፈር | ፬ | ፺፬ |
| አድገለ ፪ኛ | ፲ ዓ፯ ወ | ፻፬ |

| | | |
|---|---|---|
| አግባ | ፯ | ፻፬ |
| ሰርኣዳ | ፲፯ | ፻፳፩ |
| መሊስ ኣላሚዳ | ፱ | ፻፳፬ |
| ሀቀቢ ኰሉ ጽዮን | ፯ | ፻፴፩ |
| ሀቅሊ ስርጓይ | ፲፪ | ፻፵፫ |
| ድድሜ ዘርኣይ | ፲ | ፻፶፫ |
| አውጥጥ | ፪ | ፻፶፬ |
| አልአይ በጋማይ | ፯ | ፻፷፪ |
| አውዱ ዣን አስገድ | ፴ | ፻፸፪ |
| ዛግን ጽዮን ሓግዝ | ፬ | ፻፸፭ |
| ሬማ ጽዮን ግዛ | ፫ | ፻፪ |
| አዜጋን መኣልባጋድ | ፭ | ፻፭ |
| ገፈሌ ሰብአ አስገድ | ፩ | ፻፷ |
| ጽጋዮን ብእሴ ሰርቅ | ፱ | ፻፲፪ |
| ጋዛ አግዱር | ፰ | ፻፳፩ |
| አግዱር አስጓጓ | ፷ | ፻፳፰ |
| ጸዊዛ | ፩ | ፪፻፴ |
| ዋከና ንግሥጥ | ፪ | |
| ሀውደስ | ፱ ወር | |
| አስላል ሰን ሰገል። | | ፪፻፴፫ |
| አስፍሓ አስፍሓ | ፲፱ | ፪፻፴፭ |

| | | |
|---|---|---|
| አጽገባ ሰይፈ አርእድ | ፯ | ፪፻፷፫ |
| አይባ | ፲፮ | ፪፻፸ |
| ጸሓም ላክንዱን | ፱ | ፪፻፸፱ |
| ጽጋብ | ፲ | ፪፻፹፱ |
| ታዜር ታዚና | ፲ | ፪፻፺፱ |
| አህየዋ ሶፍያ ንግሥት | ፮ | ፫፻፯ |

# አባሪ ፪

## ዘመነ ክርስትና በኢትዮጵያ

| ስም | ዘመን | ዓመተ ምሕረት |
|---|---|---|
| አብርሃና አጽብሓ | ፳፯ | ፫፻፴፪ |
| እኒህ ሁለት ወንድማማች በነገሡ በ፲፭ ዓመት ባባ ሰላማ ከሳቴ ክርስትና በኢትዮጵያ መጣ። | | ፫፻፳፮ |
| አብርሃም ለብቻው | ፲፪ | ፫፻፵፬ |
| አስፍሓ ደልዝ | ፮ | ፫፻፶፭ |
| ሣህል | ፲፬ | ፫፻፷፩ |
| አፍርድ ገብረ መስቀል | ፬ | ፫፻፷፱ |

| | | |
|---|---|---|
| አድሃና ንግሥት | ፫ | ፰፻፸፱ |
| ርትዕ | ፭ | ፰፻፸፫ |
| አስፍሓ ፪ተኛ | ፭ | ፰፻፸፮ |
| አጽብሓ ፪ተኛ | ፫ | ፰፻፹፭ |
| አደሜ ፭ኛ | ፲፫ | ፰፻፺፮ |
| አብርሃ ፪ተኛ | ፯ ወር | |
| እለ ሣህለ | ፪ ወር | |
| እለ ገበዝ | ፪ | ፰፻፺፯ |
| ሣሃል | ፱ | ፱፻፪ |
| አብርሃ | ፲ | ፱፻፲፪ |
| አድሃና ንግሥት | ፮ | ፱፻፲፯ |
| ኢዮአብ | ፲ | ፱፻፳፯ |
| ጸሓም ፪ተኛ | ፪ | ፱፻፵ |
| አሜደ ፪ተኛ | ፭ | ፱፻፵፭ |
| ሣህል ሣህለ አሕዛብ | ፪ | ፱፻፵፰ |
| ጽባህ መሐረነ ክርስቶስ | ፰ | ፱፻፵፮ |
| ጸሓም ፰ተኛ | ፪ | ፱፻፵፯ |

| | | |
|---|---|---|
| አለ ገበዝ ፪ተኛ | ፰ | ፱፻፹፩ |
| አጋቤ | ፭ | ፱፻፹፬ |
| ሌዊ | ፪ | ፱፻፹፬ |
| አሜደ ፫ተኛ ዕቆብ | ፫ | ፱፻፺ |
| አርማህ ዳዊት | ፲፩ | ፱፻፳፩ |
| አምሲ | ፬ | ፱፻፳፱ |
| ሰልአዶባ | ፱ | ፱፻፸፳ |
| አልዓሜዳ | ፳ | ፱፻፹፰ |
| ታዜና ፪ተኛ ስሙ ኤዛና | ፮ | ፱፻፮፫ |
| ካሌብ | ፴ | |
| ዘእሥራኤል | | ፬፻፵፫ |
| ገብሩ | ፭ወር | |
| ገብረ መስቀል | ፲፩ | ፬፻ወ፮ |
| ቆስጠንጢኖስ ሣህል | ፵፳ | ፬፻፳፬ |
| ወሰን ሰገድ መሐረነ ክርስቶስ | ፲፬ | ፬፻፺ |
| ፍሬ ሰናይ | ፵፫ | ፰፻፫ |
| አድርአዝ | ፳ ሙሐመድ ተነሣ | ፰፻፵፫ |

| | | |
|---|---|---|
| አካለ ውድም | ፲ ፤ በ፮፻፳ | ፮፻፴፩ |
| ግርማ አስፈር | ፲፭ | ፮፻፶፮ |
| ዝርጋዝ | ፰ | ፮፻፷፮ |
| ድግና ሚካኤል | ፳፩ | ፮፻፹፪ |
| ባሕር ኤክላ | ፲፱ | ፯፻፪ |
| ጉም | ፳፬ | ፯፻፳፭ |
| አስጎምጉም | ፭ | ፯፻፴ |
| ለትም | ፲፮ | ፯፻፶፮ |
| ተላትም | ፳፩ | ፯፻፸፯ |
| ዖደ ጎሽ | ፲፫ | ፯፻፹ |
| አይዞር እስከ ቀትር ድድም | ፭ | ፯፻፹፭ |
| ውድድም | ፲ | ፯፻፺፭ |
| ውድማ አስፈሬ | ፴ | ፮፻፳፭ |
| አርማህ | ፭ | ፰፻፴ |
| ድግናዡን | ፲፱ ፲ወር | ፰፻፶፱ |
| ግዳዡን | ፲ወር | ፰፻፷ |

# አባሪ ፫

| የዛጓ መንግሥት መራ ተክለ ሃይማኖት | | |
|---|---|---|
| ስም | ዘመን | ዓመተ ምሕረት |
| ጉዲት | ፵ | ፰፻፺ |
| አንበሳ ውድም | ፳ | ፱፻፲ |
| ድል ነኣድ ማዕደይ | ፲ | ፱፻፴ |

# አባሪ ፬

| የዛጓ መንግሥት መራ ተክለ ሃይማኖት | | |
|---|---|---|
| ስም | ዘመን | ዓመተ ምሕረት |
| ስመ መንግሥቱ ዛጌ | ፲፫ | ፱፻፶፫ |
| ጠጠውድም | ፵ | ፱፻፸፫ |
| ጃን ሥዩም | ፵ | ፲፻፲፫ |

| | | |
|---|---|---|
| ግርማ ሥዩም | ፵ | ፲፻፵፫ |
| ይመርሐነ ክርስቶስ | ፵ | ፲፻፷፫ |
| ቅዱስ አርቤ | ፵ | ፲፩፻፴፫ |
| ላሊበላ | ፵ | ፲፩፻፸ |
| ነአኵቶ ለአብ | ፵ | ፲፪፻፲፫ |
| ይትባረክ ወልዱ ለላሊበላ | ፲፯ | ፲፪፻፴፪ |
| መራይሪ | ፲፭ | ፲፪፻፵፭ |
| ሀርበይ | ፮ | ፲፪፻፶፭ |

# አባሪ ፮

| ያጤ ይኵኖ አምላክና የልጃቸው መንግሥት | | |
|---|---|---|
| ስም | ዘመን | ዓመተ ምሕረት |
| ይኵኖ አምላክ | ፲፭ | ፪፻፮፮ |
| ያግብአ ጽዮን | ፱ | ፲፪፻፸፯ |
| ጽንፈ አርእድ | ፩ | ፲፪፻፸፮ |
| ሕዝበ አሰገድ | ፩ | ፲፱፻፸፱ |
| ቅድመ አሰግድ | ፩ | ፲፪፻፹ |

| | | |
|---|---|---|
| ጃን አሰገድ | ፮ | ፲፪፻፹፮ |
| ውድማ አርእድ | ፮ | ፲፪፻፹፱ |
| ዓምደ ጽዮን | ፴ | ፲፫፻፳፪ |
| ሰይፈ አርእድ | ፳፰ | ፲፫፻፵፫ |
| ውዳማ አስፈሬ | ፲ | ፲፫፻፰፫ |
| ዳዊት | ፴ | ፲፫፻፺፫ |
| ቴዎድሮስ | ፬ | ፲፫፻፺፱ |
| ይስሓቅ | ፲፭ | ፲፬፻፲፬ |
| አንድርያስ | ፯ | |
| ሕዝበ ናኝ | ፬ | ፲፬፻፲፰ |
| በድል ናኝ ፯ ከእንድርያስ | ፯ወ፮ | ፲፬፻፲፱ |
| ዓምደ ኢያሱ | ፪ | ፲፬፻፳፯ |
| ዘርአ ያዕቆብ | ፴፬ | ፲፬፻፰ |
| በእደ ማርያም | ፲ | ፲፬፻፷ |
| እስክንድር | ፲፯፥ ፭ ወ | ፲፬፻፹፯ |
| ዓምደ ጽዮን | ፪ወ ፮ | ፲፬፻፹፪ |
| ናዖድ | ፲፫ | ፲፭፻ |
| ልብነ ድንግል | ፴ | ፲፭፻፩ |

| | | |
|---|---|---|
| ገላውዴዎስ | ፲፱ | ፲፭፻፵፱ |
| ሚናስ | ፬ | ፲፭፻፶፫ |
| ሠርጸ ድንግል | ፴፬ | ፲፭፻፹፯ |
| ያዕቆብ | ፯ | ፲፭፻፺፬ |
| ዘድግል | ፩ | ፲፭፻፺፭ |
| ሱስንዮስ | ፳፰ | ፲፮፻፳፫ |
| ፋሲል ጎንደርን የሠራ | ፴፮ | ፲፮፻፶፱ |
| ደጎ ዮሐንስ | ፲፭ | ፲፮፻፸፬ |
| አድያም ሰገድ ኢያሱ | ፳፬ | ፲፮፻፺፰ |
| ተክለ ሃይማኖት | ፪ | ፲፯፻ |
| ቴዎፍሎስ | ፫ | ፲፯፻፫ |
| ዮስጦስ | ፭ | ፲፯፻፰ |
| ዳዊት | ፭ | ፲፯፻፲፫ |
| በካፋ | ፱ | ፲፯፻፳፪ |
| ዓለም ሰገድ ኢያሱ | ፳፭ | ፲፯፻፵፯ |
| ኢዮኣስ | ፲፭ | ፲፯፻፷፰ |
| ዮሐንስ | ፭ወር | |
| ተክለ ሃይማኖት | ፯ወር ፯ | ፲፯፻፸ |

| | | |
|---|---|---|
| ሰሎሞን | ፪ | ፲፯፻፸፪ |
| ተክለ ጊዮርጊስ | ፭ | ፲፯፻፸፯ |

# አባሪ ፮

| የወረሴሆች ምስፍና በጎንደር | | |
|---|---|---|
| ስም | ዘመን | ዓመተ ምሕረት |
| ታላቅ ዓሊ | ፬ | ፲፯፻፹፩ |
| ራስ አሊጋዝ | ፫ | ፲፯፻፹፮ |
| ራስ አሥራትና ራስ ወልደ ገብርኤል | ፮ | ፲፯፻፺፪ |
| ራስ ጉግሳ | ፳፮ | ፲፰፻፲፰ |
| ራስ ይማም | ፪ | ፲፰፻፳ |
| ራስ ማርዬ | ፫ | ፲፰፻፳፫ |
| ራስ ዶሪ | ፫ወር | |
| ራስ ዓሊ | ፳፪ | ፲፰፻፵፭ |
| አጤ ቴዎድሮስ | ፲፭ | ፲፰፻፷ |
| አጤ ተክለ ጊዮርጊስ | ፫ | ፲፰፻፷፫ |
| አጤ ዮሐንስ | ፲፰ | ፲፰፻፹፩ |

# አባሪ ፯

| የአቤቶ ያዕቆብ ዘር መንግሥት በሸዋ | | |
|---|---|---|
| ስም | ዘመን | ዓመተ ምሕረት |
| ነጋሢ | ፯ | ከ፲፮፻፹፯ - ፲፮፻፺፫ |
| ስብስትያኖስ ልጁ | ፲፭ | ፲፯፻፰ |
| አብየ ልጁ | ፳፭ | ፲፯፻፴፫ |
| አምሃ ኢየሱስ ልጁ | ፴፬ | ፲፮፻፰፯ |
| አስፋ ወሰን ልጁ | ፴፫ | ፲፰፻ |
| ወሰን ሰገድ ልጁ | ፬ | ፲፰፻፬ |
| ሣህለ ሥላሴ ልጁ | ፴፬ | ፲፰፻፴፰ |
| ኃይለ መለኮት ልጁ | ፰ | ፲፰፻፵፮ |

ዳግማዊ ምኒልክ የኃይለ መለኮት ልጅ ከ፯ ሺ፫፻፵፯ - ፯ሺ፫፻፹፩፤ ፳ ዓመት በሸዋ ብቻ ነገሡ በ ፯ሺ፫፻፵፯ ዓመተ ዓለም በ ፲፰፻፵፯ ዓመተ ምሕረት በዘመነ ማርቆስ ወንጌላዊ በጥቅምት ፳፬ ቀን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ተብለው በእንጦጦ ማርያም በአቡነ ማቴዎስ ተቀብለው ነገሡ። በንጉሠ ነገሥትነት ፳፬ በንጉሥነት ሸዋን ብቻ ፳፫ ድምሩ ፵፯ ዓመት ገዙ።

| | | |
|---|---|---|
| ዳግማዊ ምኒልክ | ፳፬ | ከ፲፰፻፵፯ - ፲፱፻፮ |
| ኢያሱ | ፫ | ፲፱፻፱ |

ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ በ፯ሺ ፬፻፱ ዓመተ ዓለም በ፲፱፻፱ ዓመተ ምሕረት በመስከረም ፳፪ ቀን በአባትዎ አልጋ ተቀመጡ። በየካቲት ፬ ቀን በደብረ ጊዮርጊስ በአቡነ ማቴዎስ እጅ በእለተ እሁድ ቅባ መንግሥትን ተቀብለው ንግሥተ ነገሥታት ተባሉ።

# የስሞች መጠቁም

## ሀ

ሀርበዋሽ 58፤ 59

ሀርብ እከል 59

ሀርቦይ 111

ሀስረሞት 23

ሀሸንጌ 32፣ 64፣ 65፣ 66

ሀቃቢ ኲሉ ጽዮን 101

ሀቅሊ 101

ሀተዘ ባሕር አስገድ 100

ሀንድ 71

ሀውደስ 23፣ 29

ሀድ 26 አረብኛን እይ

ሀድ - አረብኛ 26

ሀድያ 71

ሀዶራም 23

ሁሮ 64

ሁበና 64፣ 65

ሁባል 23

ሁድሁድ 44

ሂሩት፣ ወሮ. 83፣ 84

ሃምቡርግ ፫

ሆላንድ ፫

ሆር ኤምተኩ 100

ሆር ውላቦ 63

ሆኮ 67

# ለ

ለትም 19፣ 38፣ 108

ለትም፣ ንጉሥ 19፣ 108

ሉንደሃል ፩፣ ፪

ሉቃስ ፩

ሉቅማ 70

ሉባ 64፣ 67

ሉዶልፍ፣ ኢዮብ 6

ሊሙ 67

ሊበን 64፣ 67

ሊዝቦን፣ ፫

ላሊበላ 32፣ 34፣ 36፣ 111

ላስታ 34፣ 50፣ 82

አገው 48፣ 49፣ 84

ላቀች፣ ወሮ. 84

ላክድኑን 25፣ 103

ላኮመልዛ 65

ሌቃ 67

ሌዊ 106

ልብነ ድንግል፣ አጤ 62፣ 113

ሎሚታ፣ ወር. 83

ሎሜ 67

## ሐ

ሐሉል በጎስ (አገው) 49

ሐማሴን 26፣ 94

ሐማቲ 11፣ 20

ሐረርጌ 4፣ 94፣ 95

ሐር 14

ሐርጊጎ 90

ሐሰን 80

ሐበሻ 77፣ 80

ሐባብ 27

ሐድያ ፮

ሔሮዶቱስ 6፣ 46፣ 98

ሔት 48

ሕምያር 81

ሕንድ ፩፣ 29

ሕዝቅኤል 5፣ 55

ሕዝበ ናኝ 113

ሕዝበ አስገድ 112

**መ**

መሊስ አላሚዳ 101

መልዚ 46

መሐመድ 19፣ 77፣ 78፣ 79

መረብ ወንዝ 25

መረዋ 64

መራቤቴ 88

መራ ተክለ ሃማኖት 38፣ 63

መርሶ 83፣ 84

መርሶ፣ ደጃች 84

መርዌ 78

መሾሻ ወርቁ፣ ፬

መተማ፣ 48፣ 90

መነን፣ ወሮ. 83

መንገሻ አቲከም፣ ፪፣ ፬

መዐውያ 79፣ 80፣ 81

መካነ ሥላሴ 65

መካነ ኢየሱስ፣ ፫፣ 59

መኮንን፣ ራስ 95

መዝሙረ ዳዊት 5

መይራሪ 111

መዲና 78

መዳባይ 32

መጽሐፍ ቅዱስ 5፣ 14፣ 23፣ 28፣ 39

ሙርታድ6

ሙሴ 40፣ 58

ሚሌ 87

ሚናስ 113

ማርሴይ፣ ፩

ማርያም ፩፣ ፬፣ 40፣ 65፣ 84፣ 85፣ 117

ማርቆስ፣ ቅዱስ 94፣  ወንጌላዊ 117

ማርዬ፣ ራስ 83

ማቢቢል 22

ማቴዎስ፣ ቅዱስ 81

ማቴዎስም አቡነ 117፣ 118

ማከዳ 40፣ 41፣ 42፣ 47

ማዳጋስካር 41፣ 47፣ 62

ሜሻ 23

ሜታ 67

ሜጫ 64፣ 83

ምሲንህ ግርማሶር 100

ምኒልክ፣ ፪፣ ፫፣ ፬፣ ፭፣ ፮፣ 15፣ 27፣ 32፣ 33፣ 39፣ 42፣

47፣ 48፣ 50፣ 53፣ 57፣ 58፣ 68፣ 70፣ 74፣ 83፣ 88፣ 95፣ 117

ምንኩሉ 90

ምንዓሚሮች 90

ምጥዋ (ምፅዋ) ፩፣ ፫፣ 80፣ 90፣ 92

ሞሪየ 6፣ 42፣ 53

ሞሰንጀር፣ ዌነር 6

## ሠ

ሠርጸ ድንግል፣ አጤ 55፣ 114

ሠሮጡ 100

ሣሃል 105

ሳህለ ሥላሴ117

ሣህሉ፣ አጤ 83

ሣህል 104

ሣህል ሣህላ አሕዛብ 105

ሳልፍ 23

ሥፋር 23

# ረ

ረሁም 53

ራያ 64፣ 65፣ 66፣ 58

ሬማ ጽዮን ግዛ 101

ርትዕ 104

ሮሃ 34፣ 36

ሮሙስ 53

ሮም 54

# ሰ

ሰሃራ 34

ሰለሞን 15፣ 39

ሰለዋ 82

ሰላማ 53፣ 104

ሰላምኮ 59

ሰልአዶባ 106

ሰራክ ሰገር 17

ሰርኣዳ 101

ሰርጓይ 101

ሰባ ፩ኛ 108

ሰባት ቤት አገው 49

ሰባዊስ

ሰብአ አስገድ 112

ስናሒት 51

ሰንጋ 63፣ 75

ሰይፈ አርእድ 112

ሰደቻ 67

ሰገላ 26

ሰጥታህ 100

ሰፎንያስ 5

ሱማሌ 92

ሱስንዮስ፣ አጤ 59፣ 60

ሱባ 64

ሱዳን 12፣ 18 19፣ 77

ሲኒ 11፣ 12

ሲዳሞ 63፣ 70

ሳላ 23

ሳምሪ፣ የሴም ልጅ 11፣ 12

ሳምኒ ኤሊ 6

ሳባ 23-26፣ 29፣ 30፣ 34፣ 39፣ 40፣

42፣ 46፣ 47፣ 80፣ 90፣ 92

ሳባ፣ ፪ኛ 24

ሳባ፣ ፫ኛ፣ 29

ሳይንት 32፣ 33

ሳፍላ 41

ሴም 9፣ 11፣ 13፣ 23፣ 24፣ 27፣

27፣ 31፣ 32፣ 37፣ 26

ሴሩ ጓንጉል 82

ሴዩክ 51

ስብሐት፣ አዝማች 89

ስብስትያኖስ 116

ስናር 96

ስዊዘርላንድ ፳

ስዊዝ ፫

ስዊድን ፩፣ ፯

ስጥዋ ግርማ አስፈር 100

ሶሊማን ታጊ፣ ንጉሥ 10

ሶርሀቢል 40

ሶርያ 11

ሶዶ 64

# ሸ

ሸሊ 87

ሸመኒ 17

ሸርሀቢል 41

ሸናሽ 20

ሸዋ ፩፣ 59፣ 60፣ 88፣ 115፣ 116

ሻሆ 92

ሻንቅላ 11፣ 21

ሻንፖሊዎን 6

ሻጉራ 78

ሾዋና ማርያም 85

# ቀ

ቀጣሚት 78

ቁርዓን፣ 40 ምርቃንን እይ

ቃሮዳ ፩፣ ፪

ቃጭኖ 78

ቅማንት 11፣ 16

ቅድመ አሰገድ 112

ቆስጠንጢኖስ ሣህል 107

ቋራ 48፣ 84፣ 90

# በ

በለው 25፣ 26፣ 34፣ 78፣ 80፣ 90

በላአ 64

በላያ ቦረና 68

በልቂስ 40፣ 41፣ 43-45

በል ጋፋት 60

በሬንቶ 83

በርሊን ፫

በርቱማ 63፣ 64፣ 67

በሽሎ፣ ወንዝ 12

በቾ 67

በእቲ 16፣ 17

በእደ ማርያም 113

በካፋ 115

በደው 26፣ 27፣ 30

በድል ናኝ 113

በጌምድር 32፣ 59

ቡልቃያ 24

ቢረባቦ 58፣ 59

ቢንያም 70

ባሊ 77፣ 97

ባሕር 18፣ 19፣ 44፣ 45፣ 62-64፣ 82፣ 97፣ 100

ባሞሩ 20

ባሞን ፯

ባርካ፣ ወንዝ 25

ባርያ 21፣ 90

ባቢሎን 10

ባብ አልመንደብ 24፣ 56

ባዜን (ባዚን) 100

ቤቴል ፩፣ ፪

በጌምድር ፩፣ ፪፣ ፫

ብለት 75

ብሩ፣ ደጃች 84

ብሩስ፣ ጀምስ 6፣ 41፣ 42፣ 46፣

ብሪታኒያ ፯

ብጡል፣ ደጃች 83

ቦምቤይ ፩

ቦረና 67፣ 68፣ 97

ቦረን 63፣ 64፣ 67

ቦባ 15

ቦባሳ 62

ቦፋት 73

# ተ

ተላትም 38፣ 108

ተከዜ 26፣ 81

ተክለ ሃይማኖት አቡነ 71፣ 75፣ 76

ተክለ ጊዮርጊስ፣ አጤ 116

ተዋስያ 40 – 42

ተፈሪ ፬

ቱርክ መንግሥት 95

ቱት 24

ታሪሂ 77

ታዜር ታዚና 103

ታየ ገብረ ማርያም ፩፣ ፪፣ ፫፣ ፬፣ ፭፣ ፮

ታደሰ ታምራት፣፩

ቴዎድሮስ፣ አጤ፣ ፩፣ ፮ 116

ቴዎፍሎስ 114

ትሎማ 64

ትቤ 70

ትንክበሊ 17

ትኩ፣ ደጃች 84

ትክሪሮች 90

ትግሪ 24

ትግሪኛ 26፣ 32፣ 34፣ 37፣ 46፣

47፣ 65፣ 80፣ 81፣ 89፣ 90

ቶርን 92፣ 93

# ኀ

ኃይለ መለኮት 116

ኃይለ ማርያም፣ ደጃች 83

ኃይለ ከበደ ፩

ኃይሉም ደጃች 84

ኃይሌ፣ ደጃች 83

# ነ

ነሲቡ ዛማኔል ፳

ነአኩቶ ለአብ 110

ነኽርዋን 78

ነዚ 16፣ 17

ነገሥት 1 እና 2 5

ነጋሢ 116

ነጭ አባይ 26፣ 34፣ 51፣ 81፣ 97

ኑቢያ 12

ኑባል 23

ኒማልጊን 16

ናሆም 5

ናዋታን 51

ናያድ 113

ናግራን 56፣ 97

ኔፐልስ፣ ፫

ኖሕ 10

ኖባ 25፣ 26፣ 30፣ 34፣ 80፣ 81፣ 90

ኖን 48

ኖወርኦሪ 25

# አ

አህወያ ሶፍያ፣ ንግሥት 103

አሉላ፣ ደጃች 83

አሉላ፣ ፊታውራሪ 83

አልአስ79

አልአይ በጋማይ 101

አልዓሜዳ 23

አልሞደድ 23

አሎ 51

አሕመድ ግራኝ 665፣ 82

አመሃ ኢየሱስ 117

አማራ 21፣ 26፣ 27፣ 30 -36

38፣ 48፣ 60፣ 64፣ 65፣ 73

አማርኛ ፪፣ ፫፣ ፳፣ ፺፣ 23፣ 32፣ 35- 38፣

58፣ 60፣ 64፣ 665

አማሮ 70

አሜሪካ ፮

አሜደ ፩ኛ 105

አሜደ ፫ኛ ያዕቆብ 106

አምሩ 64

አምራ 40

አምሲ 106

አምኖን 48

አሥራት፣ ራስ 84

አሰለፈች ወሮ. 83

አረብ 6

አረብኛ 71

አሩሲ 64

አራም 10

አርማን 109

አርማህ ዳዊት 106

አርማጮሆ 55፣ 90

አርቤ፣ ቅዱስ 111

አርዋዲ 11፣ 12፣ 14

አርጎባ 78

አርፋክሳድ 23

አርፍድ ገብረ መስቀል 104

አሮን 40

አሳሁርታ 92፣ 93

አስላል ሰን ሰገል 103

አስብያኖስ፣ ንጉሥ 45

አስማከህ 50-52

አስትራቦን 6፣ 51

አጽገባ ሰይፈ አርእድ 102

አስገደ ብቅላ 27

አስጎምጉም 38፣ 108

አስፋወሰን 117

አስፍሓ 2ኛ 104

አስፍሓ አስፍሓ 102

አስፍሓ ደልዝ 104

አሸመን 58፣ 59

አበጋዝ አሚር አቡበከር፣ ሰዲቅ 78

አበጢ 64

አቡ 64

አብሂል 70

አቢማኤል 23፣ 29

አብዩ 82

አባል 23፣ 29፣ 92

አባይ፣ ደጃች 83

አቤቶ ያዕቆብ 116

አቤናኪ ፺

አብርሃ 105

አብቲ 67

አብድራሕማን 80

አብድራይ 58፣ 59

አቦ 64

አትሮነስ ማርያም 65

አትባራ፣ ወንዝ 26፣ 81

አና 64

አንሰባ ወንዝ 25

አንበሳ ውድም፣ ንጉሥ 54፣ 110

አንግሢ 16፣ 17

አካለ ውድም 108

አካለ ጉዛይ

አካኮ 67

አክሁናስ ሳባ ፪ኛ 24

አክሱም 42፣ 47፣ 51፣ 54፣ 71

አክቹ 64

አውዛል 23

አውዱ ዣን አሰገድ 102

አውጥጥ 101

አውፊር 23

አዘቦ 64፣ 66፣ 68

አዜጋን መአባጋድ 102

ዓዝርቅይ (አል አዝርቅይ) 6

አይሁድ 42፣ 56፣ ፈላሻን እይ

አይመለል 89

አይባ 103

አይባ ሰቢ ፪ኛ 20

አይነር 14፣ 16

አይዞር 108

አይደርኪ 17

አደሃና፣ ንግሥት 104

አዲል 48

አዲያቦ 91

አዳል 29፣ 92፣ 108

አድገለ 100

አገው 21፣ 27፣ 47-50 49፣ 84

ኢጋቤ 106

አግያዝያን 24፣ 25፣ 29፣ 37፣ 57

አግለዔ 24

አግባ 101

አግዱር አስጓጓ 102

አጽሜ፣ አቶ 31፣ 36፣ 62

አጽብሓ ፪ኛ 104

አፈልፈረግ (አቡል ፈረግ) 6

አፍሪቃ 12፣ 26፣ 41

ኡር 64

ኢልማን ዖርማን 83

ኢልያቄም 40

ኢልግ 91

ኢሳ 92

ኢሳይያስ 5፣ 56፣ 98

ኢቱ 64

ኢትዮጲስ 24-26፣ 29፣ 36-38፣ 81፣ 90

ኢትዮጵያ ፩፣ ፫፣ ፳፣ ፯፣ 5፣ 6፣ 9-14፣ 27-29፣

31፣ 34-42፣ 46፣ 47፣ 51-58፣ 62፣ 64፣ 68፣

70፣ 71፣ 77-79፣ 81፣ 82፣ 90-93፣ 95-99፣ 13፣ 117

ኢዘንበርግ 6፣

ኢየሩሳሌም 39-42፣ 44፣ 47፣ 54፣ 58፣ 78

ኢየሱስ 117

ኢየሱስ ክርስቶስ 11፣ 27፣ 41፣ 55፣ 56፣ 59

ኢያሱ፣ ልጅ 117

ኢያሱ ወልደ ነዌ

ኢይብኮ ይስሐቅ (እብነ ይስሐቅ) 6

ኢዮብ 97

ኢዮአብ 105

ኢዮኣስ 115

ኤሊ ቢዞኒ 6

ኤሌሲ ቪንኪፊስት ፫

ኢሜሊ ሉንደሃልን ፪

ኤርሚያስ 5

ኤስሜኒ 42

ኤቦር 31

ኤዛና 106

እለ ሣህለ 104

እለ ገበዝ 104

እለ ገበዝ ፪ኛ 105

እሥራኤል 9፣ 14፣ 15፣ 27፣ 31፣ 32፣

38፣ 39፣ 53፣ 54፣ 57፣ 73፣

እረኞች 24፣ 30

እስቴ 59

እስከንድር 112

እስከንድር፣ መጽሐፍ 6፣

እስያ 9-12፣ 14፣ 23፣ 33፣ 46

77፣ 92

እበነ እልእስም 79

እብነ እል ኪም 39

እቲቱ 16

እናሪያ 69-72 74፣ 76፣

እንተለ 14

እንድርያስ 113

እንጦጦ ማርያም 117

ኦሚሮስ 46

ኦሪ 10

ኦሪት 9፣ 10፣ 73

ሕግ 27፣ 39፣ 54

ኦርቶዶክስ ፬

ኦሮሞ 15፣ 17፣ 18፣ 19፣ 22፣ 31-33፣

35፣ 61-64፣ 66፣ 68-71፣ 95

ኦባል 29፣ 92

ኦነሲሞስ ነሲብ ፪

ኦፊር 29፣ 92

# ከ

ከለው 25፣ 26፣ 34፣ 78፣ 80፣ 90

ከመከም ፩

ከምባታ 74

ከረሺት 77

ከረክር 14፣ 15፣ 17

ከረዩ 64

ከሳቴ ብርሃን፣ አባ 53

ከነኸርዋን ኸዋርጅን 78፣ 79

ከንዓን 14

ከደሴቲ 16፣ 17

ከይፈ፣ ወሮ. 83

ከፋ 18፣ 19፣ 68፣ 70፣ 74፣ 75፣

ኩሳ 9፣ 11፣ 13፣ 18፣ 23፣ 29,57፣ 70

ኩስ (ኩሽ) 53

ኩታይ 20፣ 64

ኩናማ 90

ኩግ 11

ኪንዶ 71

ኪበቃሎ፣ ቅዱስ ሚካኤል 85

ካሌብ፣ አጤ 56፣ 107

ካም 9-11፣ 24፣ 29፣ 53፣ 57፣ 70፣ 90፣ 92

ካሞየሮ 75

ካርል ሰደርኪቪስት ፫

ካሩም 34፣ 81

ካሲዮኒ 12

ካቶሊኮች ፬

ካይቶ 79

ክርስቶስ - ኢየሱስን እይ

ክብረ ነገሥት 6፣ 10፣ 17፣ 19፣22፣ 24፣

28፣ 30፣ 37፣ 42፣ 50፣ 52፣ 56፣ 68

ክብርዋ፣ 16፣ 17

ኮሌ 22

ኮሶጌ 15

ኮንታ 70፣ 74

ኮኖ 67

ኮፈር 92

## ወ

ወሂጦ 19

ወለቃ 32

ወለጋ 67

ወላስማ 80

ወላይታ 70፣ 71፣ 74

ወሌ 82

ወሌ፣ ራስ 83

ወልቃይት 26፣ 55፣ 90

ወልያ ገብርኤል 85

ወልደ ሐና፣ ደጃች 83

ወልደ ገብርኤል፣ ራስ 84፣ 116

ወልደ ጊዮርጊስ አቦዬ ፫

ወሎ 64፣ 65፣ 83፣ 84

ኦሮሞ 32

ወረሴህ 82፣ 84፣ 88

ወረነሻ 64

ወረደ ነጋሽ አግባ 38

ወርድያን 64

ወሰን ሰገድ 117

ወሰን ሰገድ መሐረነ ክርስቶስ 107

ወበሪ 67

ወናግ ሰገድ 62

ወንጌ 59

ወንጌል 33፣ 41፣ 45፣ 53፣ 54፣ 56፣ 85

ወይጦ 11፣ 12፣ 18፣ 19

ወገራ 32፣ 55፣ 84

ወፋ ፯

ወፍላ አሸንጌ 32

ዊያንኪሂ ፬ኛ 51

ዋታ 18፣ 19

ዋቶ 18፣ 19

ዋከና፣ ንግሥት 102

ዋዩ 67

ዋድላ 32፣ 33፣ 84

ዋግ 50

ውላቦ 63

ውሽን 16

ውድማ አርእድ 112

ውድማ አስፈሬ 108

ውድማ አስፈሬ 2ኛ 112

# ዐ

ዑመር፣ ሼህ 82

ዑመር እብነ አልሐጣብ 78

ዑስማን እብነ ሐሩን 78

ዑጋዴን 92

ዓለም ሰገድ ኢያሱ 115

ዓለሜ እሸቴ፣ ፩

ዓሊ 78-81፣ 93

ዓሊ ራስ 83፣ 84

ዓሊ ታላቁ 84

ዓሊ ታናሹ 84

ዓሊ ደጃች 84

ዓምደ ኢያሱ 113

ዓምደ ጽዮን 55፣ 64፣ 77፣ 89

ዓምደ ጽዮን ፪ኛ 113

ዓዜብ 39-41፣ 46፣ 47

ዖደ ጎሽ 38፣ 108

## ዘ

ዘለቀ፣ ልጅ 84

ዘላን 30፣ 62

ዘርኣ ያዕቆብ፣ ፯ 113

ዘጐልቆ 5

ዘእሥራኤል 107

ዘውዲቱ፣ ንግሥት ፬፣ 119

ዘንድንግል 114

ዘገየ፣ ደጃች 84

ዘፀዓት፣ 40፣ 85

ዘዋኑስ 56

ዛምል ጊዮርጊስ 85

ዛጌ 110

ዛግን ጽዮን ሓግዝ 101

ዛጓ 33፣ 63፣ 110

ዜና ፩ 40

ዜና ፪ 5፣ 48፣ 97

ዝርጋዝ 107

ዝዋይ 6፣ 70

## ዠ

ዝገት 20፣ 21

ዣንጀሮ 71፣ 75

# የ

የሐዋርያት ሥራ (ሐዋ.) 6

የመናዊ ኩሳ 23

የመን- የየመን ታሪክ 6፣ 22፣ 23፣ 28፣ 39፣ 4043፣ 44፣ 45፣ 46፣ 55

የምሥራች ድምፅ ፳

የሱብሊ 59

የተመኙ፣ ወሮ. 83

የውብዳር፣ ወሮ. 83

የዘምበል 58፣ 59

የጁ 48፣ 82፣ 84፣ 85፣ 86፣ 87፣

ያላ ወንዝ 87

ያራህ 23

ያሮባ 24

ያዕቆብ 20፣ 73

ያግብአ ጽዮን፣ አጤ 71

ይሉ 64

ይማም፣ ራስ 116

ይማም ደጃች 84

ይምርሐነ ክርስቶስ 111

ይስሐቅ 6

ይስሐቅ፣ አጤ 62

ይባዕስ 16

ይትረሃም 48

ይትባረክ፣ ንጉሥ 33

ይትባረክ የላሊበላ ልጅ 111

ይኵኖ አምላክ፣ አቴ 33፣ 35፣ 37፣ 111

ይፋት 77፣ 78፣ 80

ይግፋ ፩፣ ፫

ዮሐንስ ፱፣ ፭ 115

ዮሐንስ መደብር 5

ዮሐንስ፣ አጤ 65፣ 116

ዮሐንስ፣ ደጉ 114

ዮስጦስ 114

ዮቅጣን 13፣ 18፣ 23፣ 24፣ 27፣

29፣ 31፣ 32፣ 37፣ 38፣ 57፣ 70፣ 92

ዮባብ 23

ዮዳ 53

## ደ

ደላንታ 84

ደማርቲኒስ 6

ደምቢያ 32፣ 84

ደራስ 63

ደስታ ሽምፐር፣ ፳

ደስታ፣ ወሮ. 83

ደስክ 75፣ 76

ደብረ ሊባኖስ 60

ደብረ ታቦር 59

ደብረ ገነት 65

ደኖኖ 90

ደግለሎች 90

ደጨ 67

ደጭና (ሂርጊሳ) 25

ዱራ 20-22

ዱዋሮ 77

ዲዮን 17

ዳሞት 20-22፣ 58፣ 59፣ 64፣ 71፣

73፣ 84፣ አገው -48፣ 49

ዳንኤል 5

ዳኢት (1395 ዓ/ም) 112

ዳዊት (1713 ዓ/ም) 115

ዳዊት፣ አጤ 94

ዳዊት (የመጽሐፍ ቅዱሱ) 48

ዳዋ 90

ድል ነኣድ ማዕደይ 110

ድን 59

ድድሜ ዘርኣይ 101

ድድም 108

ድግና ሚካኤል 108

ድግናዥን 109

ዶሪ፣ ራስ 83፣ 116

ዶቅላ 23

ዶባ 88

## ጀ

ጀር 60

ጀርመን ፫፣ ፯

ጃሊሎች 90

ጃኒ (ጃኒ ፊንቀራ) 17

ጃን ሥዩም 110

ጃን አሰገድ 112

ጅሌ 64፣ 67

ጅማ 67፣ 70

ጅቡቲ 97

ጅንጉር 64

ጅጅጋ 98

# ገ

ገለቡ፣ ወሮ. 82፣ 83

ገላና 62

ገላኔ፣ ወንዝ 63

ገላውዴዎስ 113

ገምቦ 58፣ 59

ገሡሡ፣ ደጃች 83

ገርስሞት፣ ንግሥት 100

ገባዖን 15

ገብረ መስቀል 107

ገብሬ፣ ራስ 83

ገነተ ጊዮርጊስ 65

ገነቴ 85፣ 86

ገነት 48፣ 65

ገናሌ 62 ገላናን እይ

ገድኤት 77

ገዶ መድኃኔዓለም 85

ገፈሌ ሰብአ አስገድ 102

ጉለሌ 67

ጉመር 22

ጉማ 20፣ 21፣ 67፣ 70

ጉም 108

ጉራጌ 88፣ 89

ጉርዓ 89

ጉስታብ አረን ፩፣ ፪

ጉባላፍቶ አቡነ ተክለ ሃይማኖት 84

ጉባርጃ ማርያም 84፣ 85

ጉኢዲ ኢግናጥዮስ 6

ጉድሩ 64፣ 67

ጉግሳ፣ ራስ 83፣ 116

ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ 6

ጋባ 17፣ 55

ጋዛ አግዱር 102

ጋፋት 56-61፣ 76

ጌራ 67

ግምብቹ 67

ግራኝ 65 አሕመድ ግራኝን እይ

ግርማ አስፈረ 107

ግርሻ አባ 84

ግብጽ 6፣ 14፣ 20፣ 22

ግንጃሮ 90

ግዳዣን 109

ጎትየ አባ 82

ጎንደር ፩፣ 15፣ 16፣ 55፣ 84፣ 115

ጎንጋ 20፣ 21

ጎጃሜ 36

ጎጃም 34፣ 59፣ 84

ጎጅ፣ ደጃች 84

ጓንጉል 82

ጓንጉል. ደጃች 84

## ጠ

ጠለምት 32፣ 90

ጠገዴ 26፣ 55፣ 90

ጠጠውድም 110

ጢሞቴዎስ ፪ (ጢሞ.) 46

ጢኖ፣ አባ 59፣ 60

ጢኖ አዛዥ 63

ጢጦስ 54

ጣልያን ፫

ጣና ባሕር 18፣ 19. 64

ጣይቱ፣ እቴጌኤ ፬፣ 83

ጥልጣል 92

ጥሙጋ 64

ጥሩነሽ ፓርኪንስ ፮

ጥሳሜቲክ ፩ኛ 51

ጥቁር ዓባይ 26፣ 51

ጥቁር ውሃ 87

## ጨ

ጨለባ 67

ጨፋ 64

ጫቡ 64

ጭሌ 67

ጭልጋ 12፣ 15፣ 17፣ 55

## ጸ

ጺኦሪ ፩ኛ 24፣ 29

ጳውሎስ፣ ቅዱስ 46

ጴጥሮስ ፯

ጴጥሮስ ወ ጳውሎስ፣ ፬

ጵሊን 51

## ጸ

ጸሓም ፪ኛ 105

ጸሓም ፫ኛ 1-6

ጸሓም ላከንዱን 103

ጸንፈ አሰገድ 100

ጸዊዛ 102

ጽባህ መሐረነ ክርስቶስ 106

ጽንፈ አርእድ 100

ጽንፈ አርእድ ፪ኛ፣ 111

ጽጋብ 103

ጽጋዮን ብእሴ ሰርቅ 102

## ፀ

ፀሐይቱ ፬

## ፈ

ፈላሽ 53፣ 56፣ 60

ፈረንሣይ ፫፣ ፮

ፋርቃን 45

ፊንሐስ 56

ፉሌክ 23

ፋሪስ፣ ራስ 82

ፋሪስ፣ ደጃች 83

ፋሲል፣ አጤ 15፣ 16

ፋጢማ 78፣ 80

ፌግኖች 90

ፍሬ ሰናይ 107

ፍርዳቀ 16

# ፐ

ፖለቲካ 23፣ 36

ፖርቺጋል ፲



## ስለደራሲው በጥቂቱ

የአለቃ ታየ ገብረማርያም ልደት በዘመነ ወንጌላዊ ሉቃስ፣ ኅዳር ፳፩ ቀን ፲፰፻፵፫ ዓ/ም። ይህም አፄ ቴዎድሮስ በነገሡ በሰባተኛው ዓመት መሆኑ ነው።

በጣና ሐይቅ በስተምስራቅ በምትገኘው ልዩ ስሟ ይፋግ ተብላ በምትታወቀው መንደር የተወለዱት አለቃ ታየ በልጅነታቸው ወራት ወላጆቻቸውን በማጣታቸው፣ የእናታቸው ወንድም ትግራይ ይኖሩ ስለነበር አጎታቸውን ፍለጋ ወደ ትግራይ ያመራሉ። እዚያም እንደደረሱ አጎታቸውን ስላጡዋቸው ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ አቅደው ምፅዋ ደረሱ። ምፅዋ ይገኝ በነበረው የስዊድናውያን ሚሲዮን ትምህርት ቤት ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት የጀመሩትም ያኔ ነበር።

በዚያው ትምህርት ቤት ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስን ለመጀመርያ ጊዜ ወደ ኦሮምኛ የተረጎሙት ኦኔሲሞስም ይማሩ ነበር። እምኩሉ በተባለው በዚህ ትምህርት ቤት ለብዙ ዓመታት የወንጌልን ቃል ከተማሩ በኋላ ወደ ትውልድ አገራቸው ጎጃም ተመለሱና የግዕዝ ቅኔ ትምህርት ቤት ገቡ። ቅኔውን ከሙሉ አገባቡ ጋር አሳምረው ከዘረፉ በኋላ አለቃ የሚለውን ከፍተኛ ማዕረግ አግኝተው እንደገና ምፅዋ በመመለስ በተማሩበት እምኩሉ ትምህርት ቤት በመምህርነት አገለገሉ ።

በዚህ ጊዜም "መጽሐፈ ሰዋሰው " የተሰኘውን የመጀመርያ መፅሐፋቸውን ፅፈዋል። አለቃ በሕይወት ዘመናቸው ከደረሷቸው መፅሐፍቶቻቸው ዋና ዋናዎቹ እስካሁን ድረስ የሚገኘው በስዊድንኛ ቋንቋ የጻፉት en Teologisk strid infor Ras Mengescha" ( A theological debate before Ras Mengesha....ወይም ነገረ መለኮታዊ ክርክር በራስ መንገሻ ችሎት ) እና በእጅ ፅሑፋቸው የተዘጋጀውና አብዛኛው ማጣቀሻው በግዕዝ የሆነው የአማርኛ መዝገበ ቃላት ወይም የፅንሰ-ሐሣብ መዝገብ ናቸው ።

<u>የደራሲው ሥራዎች</u>

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY